DISTRICT OF COLUMBIA
OFFICE OF THE STATE SUPERINTENDENT OF
EDUCATION

# ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ

# የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ሕግ (IDEA)

# ክፍል ቢ

# የፕሮሲጀራል ሴፍራጋርድስ ማሳወቂያ

## የአካል ጉዳተኞች ወላጆች መብቶች

**በኦገስት 2018 የተከለሰ**

**መግቢያ**

# ዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ የፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ (የመብት ማስጠበቂያ ሥነ-ሥርዓት) ማሳወቂያ

## በአካል ጉዳተኞች ትምህርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ሥር የልዩ ትምህርት ፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ መስፈርቶች

**በኦገስት 2018 የተከለሰ**

"የአካል ጉዳተኝነት በሰው ልጅ ላይ ሊደርሱ ከሚችሉ ተፈጥሯዊ ክስተቶች መካከል አንዱ ሲሆን፣ የአካል ጉዳተኝነት በማናቸውም መልኩ ሰዎች በሕብረተሰቡ ውስጥ የሚኖራቸውን ተሳትፎም ሆነ ለሕብረተሱ የሚያበረክቱትን አስተዋጽዖ ሊያቀጭጭ አይችልም። ለአካል ጉዳተኛ ሕጻናት የትምህርት ውጤቶችን ማሻሻል፣ የመልካም ዕድሎች እኩል ተደራሽነት፣ ሙሉ ተሳትፎ፣ ራስን ችሎ መኖር እና የአካል ጉዳተኞች በኢኮኖሚ ራስን መቻል ብሔራዊ ብሔራዊ ፖሊሲያችን ወሳኝ አካል ነው።" **የአካል ጉዳተኞች ትምህርት ሕግ (IDEA) መግቢያ**

የአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) የፌዴራል መንግሥት ሕግ ሲሆን፣ የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸው ተማሪዎች ትምሕርት የማግኘት መብት እንዳላቸው የሚደነግግ ነው፤ ትምሕርት ቤቶችም የአካል ጉዳተኝነት ላለባቸው ልጆች ወላጆች ሁሉ አግባብነት ያላቸውን የፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ (የመብት ማስጠበቂያ ሥነ-ሥርዓት) አጠቃላይ ማሳወቂያዎች መስጠት አለባቸው ይላል። የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE)፣ የክፍለ ግዛቱ የትምሕርት ኤጀንሲ (SEA) እንደመሆኑ መጠን፣ እነዚህን ፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ማሳወቂያ መስጠት ይጠበቅበታል።
የዚህ ማሳወቂያ ቅጂ በእያንዳንዱ የትምሕርት ዘመን በትምሕርት ቤቶች ለወላጆች መሰጠት አለበት፤ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች የማሳወቂያው ቅጂ መሰጠት ይኖርበታል፦

- በመጀመሪያው ምደባ ወይም ምዘና እንዲካሄድ ጥያቄ ሲያቀርቡ፤
- በአንድ የትምሕርት ዘመን ከ34 CFR §§300.151 እስከ 300.153 በተደነገገው ሥር ለክፍለ ግዛቱ አቤቱታ ያቀረቡ እንደሆነ ወይም በ34 CFR §300.507 ስር የዳኝነት አቤቱታ ያቀረቡ እንደሆነ[1]፤
- የምደባ ለውጥን የሚያካትት የሥነ-ሥርዓት እርምጃ በልጅዎ ላይ የተወሰደ እንደሆነ፣ <u>እና</u>
- እርስዎ ጥያቄ ሲያቀርቡ፤

ይህ ሰነድ በአካል ጉዳተኞች ትምሕርት ሕግ በክፍል ቢ (20 USC § 1400 *et seq.*) እና በዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ ሕግ (5-E DCMR §3000 *et seq.* እና ርዕስ 38 ዲ.ሲ. ሕግ ከምዕራፍ 25 እስከ 25C.) የተቀመጡትን የፕሮሲጀራል ሴፍጋርድ ደንቦች ያካተተ ነው። ይህ ሰነድ ከዩናይትድ ስቴትስ ዲፓትርመንት ኦፍ ኤዱኬሽን ሞዴል የፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ማሳወቂያ ጋር የሚጣጣም ሲሆን፣ እንዲህ ባለው ማሳወቂያ ውስጥ ሊካተቱ የሚገባቸውን የዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ መስፈርቶች የያዘ ነው።

<u>ይህንን ሰነድ አስመክቶ ሚኖሯችሁን ጥያቄዎች ከዚህ በታች ባለው አድራሻ ይላኩ፦</u>

**Office of the State Superintendent of Education**
**Division of Systems and Supports, K-12**
1050 First Street NE, 5th Floor
Washington, DC 20002
(202) 741-0273

ይህ ሰነድ ከዚህ በሚተከለው የድረ-ገጽ አድራሻ ሊገኝ ይችላል፦ http://www.osse.dc.gov

[1]በአንድ የትምሕርት ዘመን ውስጥ በ34 CFR §§300.151 እስከ 300.153 ስር ለመጀመሪያ ጊዜ በክፍለ ግዛቱ አቤቱታ ሲያቀርቡ ወይም በ34 CFR §300.507 ሥር የዳኝነት አቤቱታ ያቀረቡ እንደሆነ ትምሕርት ቤቶች የፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ቅጂ መስጠት ይኖርባቸዋል፤ ሆኖም ግን በተመሳሳይ የትምሕርት ዘመን ውስጥ የክፍለ ግዛት ወይም የዳኝነት አቤቱታ የቀረበ እንደሆነ የፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ቅጂ የመስጠት ግዴታ የለባቸውም፡፡

**ማውጫ**


**ክፍል ቢ የፐሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ማሳወቂያ ............ 5**

**ጠቅላላ መረጃ............ 5**

ምደባ እና የምዘና ሂደትን የማስጀመር ዕድል
ቅድመ የጽሁፍ ማሳወቂያ
ዋነኛ ቋንቋ
ኤሌክትሮኒክ ሜል
በወላጅ ስለሚሰጥ ፈቃድ
ገለልተኛ የትምሕርት ምዘና
የግላዊ ትምሕርት ፕሮግራም ስብሰባዎች ከተካሄዱ በኋላ ሰነዶችን ስለመስጠት
የወላጅ ምልከታ

**የመረጃዎች ምስጢራዊነት ............ 15**

ትርጓሜዎች
ለወላጆች የሚሰጥ ማሳወቂያ
የተደራሽነት መብቶች
የመረጃ ተደራሽነት ሪከርድ
ከአንድ በላይ የሆኑ ልጆች ሪከርዶች
የመረጃዎች ዓይነቶች እና መገኛዎች ዝርዝር
ክፍያዎች
በወላጅ በሚቀርብ ጥያቄ በሪከርዶች ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ
የአቤቱታ መሰማት ዕድል
የአቤቱታ መሰማት ሂደት
የአቤቱታ መሰማት ውጤት
ግላዊ ማንነትን የሚመለከቱ መረጃዎች እንዲገለጹ ስለሚሰጥ ፈቃድ
ሴፍጋርድስ
መረጃን ስለማስወገድ

**የአቤቱታ አቀራረብ ስነ ስርዓት ............ 19**

የዳኝነት አቤቱታ መሰማት እና በክፍለ ግዛት የአቤታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት መካከል ያለው ልዩነት የክፍለ ግዛት አቤቱታ ሥነ-ሥርዓትን ተግባራዊ ስለማድረግ
ለክፍለ ግዛት የአቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት ተፈጻሚ መደረግ ያለባቸው አነስተኛዎቹ ሁኔታዎች
የክፍለ ግዛት አቤቱታ ስለማቅረብ

**የዳኝነት አቤቱታ አቀራረብ ሥነ -ሥርዓት............ 22**

የዳኝነት አቤቱታ ስለማቅረብ
የዳኝነት አቤቱታ
ሞዴል ቅጾች
ዳኝነት እንዲታይ ስለመጠየቅ
ሽምግልና
አለመግባባትን የመፍታት ሂደት

**የዳኝነት አቤቱታ መሰማት ሂደት ............ 28**

ገለልተኛ የዳኝነት አቤቱታ
የዳኝነት ሂደት መብቶች
የዳኝነት ውሳኔዎች

**ይግባኞች ............ 31**

የውሳኔ መጨረሻ መሆን፤ ይግባኝ
የዳኝነት ሂደት የጊዜ ሰሌዳ እና የችሎቱ አሰያየም
የፍትሐ ብሔር ክስ እና ክሱ የሚመሰረትበት የጊዜ ገደብ
የዳኝነት አቤቱታ እና የአቤቱታ መሰማት ሂደት በመካሄድ ላይ ሳለ የልጅዎ ምደባ
ለጠበቃ እና ለሙያተኛ ምሥክሮች ስለሚከፈል ክፍያ

**የአካል ጉዳት ላለባቸው ልጆች ሥነ-ሥርዓት ለማስጠበቅ ሥራ ላይ የሚውል አካሄድ............ 35**

የትምሕርት ቤት ሠራተኞች ሥልጣን
በስነ ስርዓት ጉድለት ምክንያት ስለሚሆን የምደባ ለውጥ
የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ አወሳሰን
ይግባኝ
በይግባኝ ወቅት ስለሚኖር ምደባ
ለልዩ ትምህርት እና ተያያዥ ለሆኑ አገልግሎቶች ለጊዜው ብቁ ላልሆኑ ልጆች ስለሚደረግ ጥበቃ

ጉዳዩን ለሕግ አስከባሪ እና ለፍርድ ቤት አካላት መላክ እና በእነርሱ የሚወሰዱ እርምጃዎች

**በመንግስት ወጪ ልጆችን በራሳቸው ውሳኔ በግል ትምህርት ቤቶች ለማስገባት ተፈፃሚነት ያላቸው መስፈርቶች....42**

ጠቅላላ

**ተጨማሪ መረጃ ....................................................................................................................................44**



1050 First Street NE, Fifth Floor, Washington, DC 20002 • Phone: (202) 727-6436 TTY: 711 • osse.dc.gov

## ምልከታ:- ክፍል ቢ የፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ማሳወቂያ

እንደ ወላጅ *ፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ* በመባል የሚታወቅ መብት አለዎት፤ ይህም መብት በሁሉም የልዩ ትምሕርት ሂደት ውስጥ ተፈጻሚነት ያለው ነው። የፌዴራል እና የክፍለ ግዛት ሕግጋት እና ደንቦች የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸው ልጆች በግላዊ የትምሕርት ፕሮግራም (IEP) (IEP) ነጻ አግባብነት ያለውን ሕዝባዊ ትምሕርት (FAPE) የሚያገኙባቸውን ፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ (የመብት ማስጠበቂያ *ሥነ-ሥርዓት*) የተባሉ ደንቦች ያወጣሉ።

ይህ ሰነድ በፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ማሳወቂነት የሚያገለግልዎ እና እርስዎ እና ልጅዎ በአካል ጉዳተኞች ትምሕርግ ሕግ (IDEA) እና በሌሎች በዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ ስለ ልዩ ትምሕርት በሚደነግጉ ሕግጋት ሥር ያሏችሁን መብቶች እንዲገነዘቡ የሚረዳዎ ነው። በፌዴራል ሬጉሌሽንስ ኮድ (CFR) በርዕስ 34፣ በክፍል 300፤ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ ኮድ በምዕራፎች 25B and 25C፤ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ ማኑሲፓል ሬጉሌሽንስ (5E DCMR) ርዕስ 5፣ ንዑስ ርዕስ E፣ ምዕራፍ 30 ስር የእነዚህ ፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ደንቦች ሙሉ ጽሁፍ ይገኛል።

ይህ የፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ማሳወቂያ በ§300.148 ስር (በመንግሥት ወጪ በአንድ ወገን ውሳኔ አንድን/አንዲትን ልጅ በግል ትምሕርት ቤት መመደብ) ተፈጻሚነት ያላቸው ፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ፣ §§300.151 እስከ 300.153 (የክፍለ ግዛት የአቤቱታ አቀራረብ አካሄድ)፣ §300.300 (የወላጅ ፈቃድ)፣ §300.502 (ገለልተኛ የትምሕርት ምዘና)፣ §300.503 (ቅድመ የጽሁፍ ማሳወቂያ)፣ §§300.505 እስከ 300.518 (ሌሎች ፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ፣ ለምሳሌ ሽምግልና፣ የዳኝነት አቤቱታ ሂደት፣ አለመግባባትን መፍታት እና ገለልተኛ የዳኝነት አቤቱታዎች ስለመሰማት)፣ §§300.530 through 300.536 (በክፍል ቢ ደንቦች ስር በንዑስ ክፍል ኢ ስለፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ የሥነ-ሥርዓት እርምጃ አወሳሰድ) እንዲሁም §§300.610 እስከ 300.625 (በንዑስ ክፍል ኢ የምሥጢራዊ መረጃዎች ድንጋጌ) ሙሉ ማብራሪያ ተሰጥቷል።

በዚህ ጽሁፍ ውስጥ በተሰጡ ማብራሪያዎች ላይ ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት ጥያቄዎን በአካባቢዎ ለሚገኘው ትምሕርት ቤት፤ ለአካባቢው ዲስትሪክት ወይም በሌላ ስሙ ለአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA)፣ ወይም በዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኤጀንሲ ለሆነው ለክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ያቅርቡ።

**[ማስታወሻ:- ልጅዎ ባለበት/ባለችበት ትምሕርት ቤት ውስጥ ለሚማሩ ተማሪዎች ተግባራዊ የሚሆኑ ተጨማሪ የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ሊኖሩ ይችላሉ። የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ይህንን መረጃ ለእርስዎ የመስጠት ግዴታ አለበት። ስለእንደዚህ አይነቶቹ ተጨማሪ ሴፍጋርድስ መረጃ ለማግኘት ለአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።]**

## ጠቅላላ መረጃ

### ምደባ እና የምዘና ሂደትን የማስጀመር ዕድል

### 34 CFR §§300.301፣ 300.304፣ እና 300.305፤ ዲ.ሲ. ኦፊሺያል ኮድ § 38-2561.02፤ 5E DCMR §§ 5-3004 እና 5-3005.2

ምዘና ማለት በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) እና በዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ ሕግ መሠረት ከዚህ የሚከተሉትን ለመወሰን ተፈጻሚ የሚሆን የአሠራር ሂደት እና/ወይም ምዘና ማለት ነው:- (1) አንድ ልጅ የአካል ጉዳት ያለበት/ባት መሆኑን፣ ካለበት/ካለባት ደግሞ (2) የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት ልዩ ትምሕርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ባሕርይ እና መጠን በዚህ ሒደት ይወሰናል። የእርስዎ ልጅ የአካል ጉዳተኝነት ያለበት/ያለባት መሆኑን ለማረጋገጥ ምዘና እንዲካሄድ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ወይም እርስዎ ጥያቄ ማቅረብ ትችላላችሁ። እንዲህ ያለው ጥያቄ በቃል ወይም በጽሁፍ ሊቀርብ ይችላል። የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ጥያቄ በቀረበለት በሦስት (3) የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ በቃል የተደረገን ምደባ በሰነድ ማስደገፍ አለበት።

ምዘናውን በሚያካሂድ ጊዜ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ልዩ ልዩ የምዘና ዘዴዎች እና ስልቶች በመጠቀም ስለልጅዎ አግባብነት ያላቸውን የብቃት፣ የዕድገት እና ትምሕርታዊ መረጃዎች መሰብሰብ አለበት፤ ከሚሰበሰቡትም መረጃዎች መካከል በወላጅ የሚሰጡ መረጃዎች ይካተታሉ። በተጨማሪም፣ የአካባቢዎ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ልጅዎ የአካል ጉዳት ያለበት/ያለባት መሆኑን ለመወሰን እና የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት አግባብ የሆነ የትምሕርት ፕሮግራም እንዴት ያለው ነው የሚለውን ለመወሰን አንድ ነጠላ መለኪያ ወይም ምዘና ከመጠቀም መቆጠብ አለበት። የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ከአካላዊ ወይም ዕድገት ነክ ነገሮች በተጨማሪ ከግንዛቤ እና ባሕርይ ጋር ተያያዥ የሆኑትን ለመመዘን የሚያስችሉ ብቁ ቴክኒካዊ ዘዴዎች መጠቀም ይኖርበታል።

እያንዳንዱ የአካባቢ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በዘር ወይም በብሔር ላይ ተመስርቶ መድልዖ እንዳይደረግ፣ ምዘናዎች የተመረጡ እና ክትትል የሚደረግባቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት። ከዚህም በተጨማሪ፣ ሁሉም ምዘናዎች መሰጠት ያለባቸው በልጅዎ ዋነኛ ቋንቋ ሊሆን ይገባል። ለልጅዎ ምዘና ከማድረግ አንጻር ዋነኛ ቋንቋ ማለት ልጅዎ በቤት ውስጥ በመደበኛነት የሚጠቀምበት/የምትጠቀምበት ወይም የትምሕርት ቋንቋ ማለት ይሆናል (በሁለት ቋንቋዎች መካከል ልዩነት ያለ እንደሆነ፣ ዋነኛ ቋንቋ የሚባለው እርስዎ የሚጠቀሙበት ቋንቋ አይደለም)።

ምዘናው መካሄድ ያለበት በምዘናው አዘጋጅ በተቀመጡት ማናቸውም መመሪያዎች መሠረት በሰለጠኑ እና ዕውቀቱ ባላቸው ሠራኞች ነው፤ ምዘናው ጥቅም ላይ መዋል ያለበት በምዘናዎቹ የተገኙት ውጤቶች ዋጋ ለሚሰጡበት እና እምነት ለሚጣልባቸው ዓላማ ብቻ ሊሆን ይገባል።

የምዘና ተጨማሪ ሂደቶች ከዚህ የሚከተሉት ናቸው፡-

- የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA)፣ ምዘናዎቹ ግልጽ ከሆኑ ትምሕርታዊ ፍላጎቶች አንጻር የተቃኙ መሆናቸውን እና የልጅዎን ኢንተሊጀንስ ኮሸንት (IQ) ለመለካት ብቻ የተነደፉ አለመሆናቸውን ማረጋገጥ አለበት፤
- የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA)፣ የምዘናዎቹ ውጤቶች የልጅዎን ተፈጥሯዊ ችሎታ ወይም የብቃት ደረጃ ወይም ሌሎች በምዘናው እንዲለኩ የታሰቡ ሁኔታዎች ከሁሉ በተሻለ አኳኋን ለማንጸባረቅ እንዲችሉ እንጂ የልጅዎን የስሜት፣ የአካላዊ ወይም የንግግር ችሎታ ጉድለት መለኪያ አለመሆናቸውን ለማረጋገጥ ምዘናዎቹ በአግባቡ የተመረጡ እና በውጤታማነት ተግባራዊ መደረጋቸውን ማረጋገጥ አለበት፤
- የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA)፣ ልጅዎ በሁሉም የአካል ጉዳተኝነት አለበት/አለባት ተብለው በሚጠረጠሩ ጉዳዮች ላይ ምዘና መካሄዱን ማረጋገጥ አለበት፤
- ልጅዎ በተመሳሳይ የትምሕርት ዘመን ከአንድ የአካባቢ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ወደ ሌላ የተዘዋወረ/ች እንደሆነ፣ ሁለቱ የአካባቢ የትምሕርት ኤጀንሲዎች በተቻለ ፍጥነት በመተባበር ምዘናው በተገቢው ጊዜ እንዲጠናቀቅ ማድረግ አለባቸው፤
- የአካባቢዎ የትምህርት ኤጀንሲ፣ የልጅዎን የልዩ ትምሕርት እና ተያያዥ የአገልግሎት ፍላጎቶች ሁሉ ለይቶ ለማወቅ በበቂ ሁኔታ አጠቃላይ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፤ እንዲሁም
- የአካባቢዎ የትምህርት ኤጀንሲ፣ የልጅዎን ትምሕርታዊ ፍላጎት የመወሰን ኃላፊነት የተሰጣቸው ሰዎች አግባብነት ያለውን መረጃ የሚሰጥ የምዘና ዘዴዎች ወይም መሣሪያዎች እና ስልቶች ያሏቸው መሆኑን ማረጋገጥ አለባቸው።

## የመጀመሪያው ምዘና የጊዜ ሰሌዳ

በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሕግ መሠረት፣ የአካባቢዎ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) የአካል ጉዳተኝነት አለበት ተብሎ ለተጠረጠረ አንድ ልጅ የመጀመሪያ ምዘና በሠላሳ (30) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ለማከናወን የወላጅ ፈቃድ ማግኘት እና የወላጅ ፈቃድ ባገኘ በስልሳ (60) ቀናት ውስጥ የልጁን ብቁ መሆን አለመሆን በተመለከተ ለመወሰን አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ማድረግ አለበት። ሆኖም ግን ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች የመጀመሪያው ምዘና ማከናወኛ የጊዜ ሰሌዳ ገደቡ በአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡-

- ልጅዎን ወደ ምዘና በተደጋጋሚ ሳያመጡ የቀሩ እንደሆነ ወይም ፈቃደኛ ካልሆኑ፤
- ምዘናው እንዲካሄድ በተደጋጋሚ ተጠይቀው ፈቃድ ሳይሰጡ የቀሩ እንደሆነ ወይም ፈቃድ ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ፤ ወይም
- የመጀመሪያው ምዘና የሚደረግበት የጊዜ ሰሌዳ መቁጠር ከጀመረ በኋላ የቀድሞው የአካባቢ ትምሕርት ኤጀንሲ ልጅዎ የአካል ጉዳት ያለበት/ባት ስለመሆኑ ውሳኔ ከመስጠቱ በፊት ልጅዎን በሌላ የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ ስር በሚገኝ ትምሕርት ቤት ያስገቡ እንደሆነ የጊዜ ሰሌዳው ተፈጻሚ አይሆንም። ይህ ልዩ ሁኔታ ተፈጻሚ የሚሆነው ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቻ ነው፡-
  - አዲሱ የአካባቢ የትምሕርት ኤጀንሲ ምዘናው በተገቢው ጊዜ እንዲጠናቀቅ በቂ ሥራ እየሠራ ከሆነ፣ <u>**እና**</u>
  - እርስዎ እና የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ምዘናው ስለሚጠናቀቅበት ጊዜ የተለየ የጊዜ ስምምነት ያደረጋችሁ እንደሆነ።

## ዳግም ምዘና

ዳግም ምዘና ማለት የመጀመሪያው ምዘና ከተካሄደ በኋላ የሚካሄድ ምዘና ሲሆን፣ ዓላማውም የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ አሁንም በተመሳሳይ የአካል ጉዳት ሁኔታ ላይ እንደሚገኝ ለማረጋገጥ ነው። የዳግም ምዘና ዓላማ፡-

- የልጅዎን ወቅታዊ የትምሕርት ብቃት እና ተያያዥ ዕድገት ነክ ፍላጎቶች ለይቶ ማወቅ፤
- ልጅዎ ልዩ ትምሕርት እና ተያያዥ አገልግሎት በቀጣይነት የሚያስፈልገው/የሚያስፈልጋት መሆኑን መፈተሽ፤ <u>**እና**</u>
- ይህ ከሆነ፣ በእነዚህ አገልግሎቶች ላይ ማንኛውም ጭማሪ ወይም ማሻሻያ ማድረግ አስፈላጊ ስለመሆኑ መወሰን።

እርስዎ እና የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ዳግም ምዘና አስፈላጊ አይደለም ብላችሁ ካልወሰናችሁ በስተቀር ዳግም ምዘና ቢያንስ በየሦስት ዓመቱ አንድ ጊዜ መካሄድ አለበት። እንደአግባብነቱ ወይም እርስዎ ወይም የልጅዎ መምሕር በምትጠይቁ ጊዜ ዳግም ምዘና ከዚህም ይልቅ በተቀራረበ ድግግሞሽ ሊካሄድ ይችላል። እርስዎ እና የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በሌላ አኳኋን ካልተስማማችሁ በስተቀር ዳግም ምዘና በዓመት ከአንድ ጊዜ በላይ መካሄድ የለበትም።

**34 CFR §300.503፤ የዲ.ሲ. ኦፊሺያል ኮድ § 38-2571.03፤ እና 5E DCMR §3024 እና 3025**

የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ከዚህ ከሚከተሉት አስቀድሞ ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ማሳወቂያ (በጽሁፍ ግልጽ የመሆኑ መረጃዎችን) ለእርስዎ መስጠት አለበት፡-

- የልጅዎን ትምሕርታዊ ምደባ ወይም የአገልግሎት ቦታ ለመለየት፣ ለመገምገም ወይም ለልጅዎ ነጻ አግባብነት ያለው ሕዝባዊ ትምሕርት ለመጀመር ወይም ለመለወጥ ሃሳብ ከማቅረብ በፊት፤ **ወይም**
- የልጅዎን ትምሕርታዊ ምደባ ወይም የአገልግሎት ቦታ መለየት፣ መገምገም ወይም ልጅዎ ነጻ አግባብነት ያለው ሕዝባዊ ትምሕርት ለመጀመር ወይም ለመለወጥ እምቢተኛ ከመሆኑ በፊት።

**የቅድመ የጽሁፍ ማሳወቂያ ይዘት**

*ቅድመ የጽሁፍ ማሳወቂያው* ከዚህ የሚከለተው ይዘት ሊኖረው ይገባል፡-

- የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ለመውሰድ ያሰበውን ወይም ፈቃደኛ ያልሆበትን እርምጃ ማብራራት፤
- የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) እርምጃውን ለመውሰድ ኃሳብ ያቀረበበትን ወይም ፈቃደኛ ያልሆነበትን ምክንያት ማብራራት፤
- የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) እንዲህ ያለው እርምጃ እንዲወሰድ ሃሳብ ለማቀርብ ወይም እርምጃውን ለመውሰድ ፈቃደኛ ላለመሆን ሲወስን መሠረት ያደረገውን የእያንዳንዱን ምዘና ሂደት፣ ምዘና፣ ሪከርድ ወይም ሪፖርት ማብራራት፤
- በአካል ጉዳተኞች ትምሕርት ሕግ በክፍል ቢ የፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ድንጋጌዎች መሠረት የሕግ ጥበቃ ያለዎት መሆኑን መግለጽ፤
- የእነዚህ ፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ድንጋጌዎች ቅጂ ማግኘት ስለሚችሉበት ሁኔታ መረጃ ማካተት፤
- በአካል ጉዳተኞች ትምሕርት ሕግ በክፍል ቢ የፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ድንጋጌዎች ሥር ጥበቃ የሚደረግልዎ መሆኑን መግለጽ እና ስለሚደረግልዎ ጥበቃ የሚገልጸውን ፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ማሳወቂያ ቅጂ በራስዎ ፍላጎት ሊያገኙ ስለሚችልበት ሁኔታ መግለጽ አለበት (ሆኖም ግን የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ያቀረበው የውሳኔ ሃሳብ ወይም ፈቃደኛ አለመሆኑን የገለጸው በመጀመሪያው የምዘና ምደባ በሚሆን ጊዜ፣ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) የፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ማሳወቂያ የመስጠት **ግዴታ** አለበት።)
- በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ የተገለጸውን ለመረዳት ድጋፍ ካስፈለገዎ፣ ድጋፉን ከየት ማግኘት እንደሚችሉ እና ከዚህ የሚከተሉትን ተጠሪዎች አድራሻዎች መግለጽ አለበት፡-

  ሀ. በአካል ጉዳተኞች ትምሕርት ሕግ ሥር የተቋቋመው የወላጅ ሥልጠና እና መረጃ ማዕከል፤

  ለ. የዲሲ የሕዝብ ትምሕርት እንባ ጠባቂ መሥሪያ ቤት፤ እና

  ሐ. የዲሲ የተማሪ ሙብት ተከራካሪ መሥሪያ ቤት

- የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ከግምት ውስጥ ያስገባቸውን ማናቸውንም ሌሎች አማራጮች ማብራራት እና እንዲህ ያሉት አማራጮች ተቀባይነት ያላገኙበትን ምክንያት፤ እንዲሁም
- የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ካቀረበው ሃሳብ እና ፈቃደኛ ካለመሆኑ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን የሌሎች ጉዳዮች ማብራሪያ ማካተት አለበት።

**ማሳወቂያው መዘጋጀት ያለበት በቀላሉ ለመረዳት በሚቻል አገላለጽ ሊሆን የሚገባው ስለመሆኑ**

ማሳወቂያው፡-

- ጠቅላላው ሕዝብ ሊረዳው በሚችለው አገላለጽ ሊጻፍ ገባል፤ እንዲሁም
- የማይቻል መሆኑ ግልጽ ካልሆነ በቀር በምትጠቀሙበት ዋነኛ ቋንቋ ወይም ሌላ የሃሳብ ልውውጥ ዘዴ ሊሰጥ ይገባል።

የምትጠቀሙበት ዋነኛ ቋንቋ ወይም ሌላ የሃሳብ ልውውጥ ዘዴ መጻፍ የማይችል ቋንቋ በሚሆንበት ጊዜ፣ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ማሳወቂያው፡-

- ለእርስዎ በቃል ወይም በእርስዎ ቋንቋ ወይም በሌላ የሃሳብ ልውውጥ ዘዴ በሌላ መልኩ እንዲተረጎምልዎ ማድረግ አለበት፤
- የማሳወቂያው ይዘት እንደገባዎ ማረጋገጥ፤ እንዲሁም
- እነዚህ ሁለት መስፈርቶች መሟላታቸውን ለማረጋገጥ የጽሁፍ ማስረጃ መኖሩን ማረጋገጥ አለበት።

## ዋነኛ ቋንቋ

**34 CFR §300.29**

*ዋነኛ ቋንቋ፣* አነስተኛ የእንግሊዝኛ ቋንቋ ችሎታ ላለው ሰው ጥቅም ላይ በሚውል ጊዜ፣ ከዚህ የሚከተሉትን ማለት ነው፡-

- ግለሰቡ በመደበኛነት የሚጠቀምበት፣ ወይም ሕጻን ከሆነ ደግሞ፣ ወላጆቹ በመደበኛነት የሚጠቀሙበት ቋንቋ፤ እንዲሁም

- ከሕጻኑ ጋር በሚደረግ ቀጥተኛ ግንኙነት (ሕጻኑ በሚገመገምበትም ጊዜ)፣ ሕጻኑ በመደበኛነት በቤት ውስጥ ወይም ትምሕርት በሚሰጥበት ቦታ የሚጠቀምበት ቋንቋ፤ መስማት ወይም ማየት ለተሳነው ሰው፣ ወይም የሚጻፍ ቋንቋ የሌለው ሰው ከሆነ ደግሞ፣ እንዲህ ያለው ሰው የሚጠቀምበት የመግባቢያ ቋንቋ (ለምሳሌ የምልክት ቋንቋ፣ ብሬል ወይም የቃል ንግግር) ማለት ነው።

## ኤሌክትሮኒክ ሜል

**34 CFR §300.505**

የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ወላጆች ሰነዶችን በኢሜል እንዲደርሳቸው አማራጭ የሚሰጥ ከሆነ፣ ከዚህ የሚከተሉት በኢሜል እንዲደርሱዎ ማድረግ ይችላሉ፡-

- ቅድመ የጽሁፍ ማሳወቂያ፤
- የፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ማሳወቂያ፤ <u>እና</u>
- ለዳኝነት ከሚቀርቡ አቤቱታዎች ጋር የተያያዙ ማሳወቂያዎች/ማስጠንቀቂያዎች።

## በወላጅ ስለሚሰጥ ፈቃድ

**34 CFR §§300.9 እና 300.300፤ 5E DCMR §§3026.1 እና 3005.2**

**የወላጅ ትርጓሜ (34 CFR §300.30 እና 5E DCMR §3001.1)**

"*ወላጅ*" ማለት (ሀ) የተፈጥሮ ወይም የጉዲፈቻ ወላጅ፤ (ለ) አሳዳጊ ወላጅ (ሆኖም ግን የተፈጥሮ ወይም የጉዲፈቻ ወላጅ በሕጻኑ/ኗ የትምሕርት ጉዳዮች ላይ ለመወሰን ያላቸው ሥልጣን አግባብነት ባለው ሕግ መሠረት የተሰረዘ ሊሆን ይገባል፤ አሳዳጊው ወላጅ ከልጅ ጋር ቀጣይነት ያለው እና የረጅም ጊዜ የወላጅ እና የልጅ ግንኙነት ያላቸው፣ በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) ሥር ትምሕርት ነክ ውሳኔ ለመስጠት ፈቃደኛ የሆኑ እንዲሁም ከሕጻኑ ጥቅሞች ጋር ምንም ዓይነት የጥቅም ግጭት የሌላቸው ሊሆኑ ይገባል)፤ (ሐ) ለሕጻኑ/ኗ እንደ ወላጅ ለመሆን ወይም በሕጻኑ/ኗ ትምሕርት ጉዳዮች ላይ ውሳኔ ለመስጠት ሥልጣን የተሰጣቸው ሞግዚት፤ (መ) ከሕጻኑ/ኗ ጋር አብሮ የሚኖር፣ በወላጅ ቦታ ሆኖ ኃላፊነት የወሰደ ሰው (ለምሳሌ አያት፣ የእንጀራ አባት ወይም እናት ወይም ሌላ ዘመድ) ወይም ለሕጻኑ/ኗ ደሕንነት በሕግ ኃላፊነት የወሰደ ሰው፤ ወይም (ሠ) በአካል ጉዳተኞች ትምሕርት ሕግ ወይም በኮሎምቢያ ሕግ መሠረት የተሾመ የትምሕርት አባት/እናት ማለት ነው። በዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ ኃላፊነት ሥር በማደግ ላይ ላለ ልጅ ይህ አገላለጽ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያን የሚያካትት አይደለም።

**የፈቃደኝነት ትርጓሜ**

*ፈቃድ* መስጠት ማለት፡-

- ፈቃድ ስለሚሰጡበት ጉዳይ በዋነኛ ቋንቋዎ ወይም በሌላ መግባቢያ ዘዴ (ለምሳሌ በምልክት ቋንቋ፣ በብሬል ወይም በንግግር ቋንቋ) ሙሉ መረጃ ተሰጥቶዎታል፤

- ግንዛቤ ወስደዋል፣ እንዲህ ያለው ተግባር እንዲከናወን በጽሁፍ ስምምነትዎን ገልጸዋል እንዲሁም ፈቃዱ የሚከናወነውን ተግባር ይገልጻል፤ እንዲህ ባለውም ጽሁፍ ውስጥ የሚገለጹ ሪከርዶች (ካሉ) እና ለማን እንደሚገለጹ ተነግሯል፤ <u>እንዲሁም</u>

- በእርስዎ በኩል ፈቃድዎን የሰጡት በፍላጎትዎ መሆኑን ተገንዝበዋል፤ በማንኛውም ጊዜ ፈቃድዎን ሊያነሱ እንደሚችሉ ያውቃሉ ማለት ነው።

ልጅዎ ልዩ ትምሕርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ማግኘት ከጀመረ/ች በኋላ የሰጡትን ፈቃድ መሰረዝ ከፈለጉ፣ ፈቃድዎን ማንሳት ያለብዎ በጽሁፍ ነው። ነገር ግን ፈቃድዎን ማንሳትዎ፣ እርስዎ ፈቃድዎን ከሰጡ በኋላ እና ፈቃድዎን ከመሰረዝዎ በፊት የተከናወነውን አያስቀርም (እንዳልተከናወነ አያደርግም)። ከዚህም ሌላ፣ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA)፣ እርስዎ ፈቃድዎን ከሰረዙ በኋላ ከዚህ ቀደም ልጅዎ ልዩ ትምሕርት ያገኘ/ች ስለመሆኑ በትምሕርት መረጃው/ዋ የተመዘገበውን ማናቸውንም መሰረዝ አይጠበቅበትም።



1050 First Street NE, Fifth Floor, Washington, DC 20002 • Phone: (202) 727-6436 TTY: 711 • osse.dc.gov

***የመጀመሪያ ምዘና እንዲካሄድ በወላጅ የተሰጠ ፈቃድ***

ከዚህ የሚከተሉት ከመፈጸማቸው በፊት፣ የአካባቢዎ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ልጅዎ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ሥር ልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎት ለማግኘት ብቁ መሆኑን/ኗን መወሰን አይችልም፡-

- ሊከናወን ይገባዋል ላለው ተግባር ቅድመ የጽሁፍ ማሳወቂያ ሳይሰጥዎ፤ <u>እንዲሁም</u>
- ***ቅድመ የጽሁፍ ማሳወቂያ*** እና ***የወላጅ ፈቃድ*** በሚሉት አርዕስት ሥር የተጠቀሱትን የወላጅ ፈቃድ ሳያገኝ።

የአካባቢዎ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ልጅዎ የአካል ጉዳት ያለበት /ያለባት መሆኑን ለመወሰን የመጀመሪያ ምዘና ለማድረግ የእርስዎን በመረጃ ላይ የተመሠረተ ፈቃድ ለማግኘት ምክንያታዊ የሆነውን ጥረት ሁሉ ማድረግ አለበት። ለመጀመሪያ ምዘና ፈቃድ ሰጥተዋል ማለት የአካባቢዎ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ለልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች እንዲሰጥ ፈቃድዎን ሰጥተውታል ማለት አይደለም።

በክፍል ቢ የተካተተ ሌላ መስፈርት የሚጠይቅ ካልሆነ በስተቀር፣ እርስዎ ከመጀመሪያ ምዘና ጋር ተያያዥ ለሆነ አንድ አገልግሎት ወይም ተግባር ፈቃደኛ አለመሆንዎ የአካባቢዎ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) እርስዎ ወይም ልጅዎ ሌላ አገልግሎት፣ ጥቅማ ጥቅም ወይም ተግባር ውስጥ ተሳትፎ እንዳይኖራችሁ ለማድረግ እንደመነሻ መጠቀም አለበት ማለት አይደለም።

ልጅዎ በሕዝብ ትምህርት ቤት ውስጥ በመማር ላይ የሚገኝ/የምትገኝ ከሆነ ወይም ልጅዎ በሕዝብ ትምህርት ቤት እንዲገባ/እንድትገባ ከፈለጉ እና ለመጀመሪያ ምዘና ፈቃድ ለመስጠት እምቢተኛ ከሆኑ ወይም ፈቃድዎን እንዲሰጡ ለቀረበልዎ ጥያቄ ምላሽ ያልሰጡ እንደሆነ፣ የአካባቢዎ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የአካል ጉዳተኞች የትምህርት ሕግ (IDEA) የደነገጋቸውን የሽምግልና ወይም የዳኝነት አቤቱታ፣ አለመግባባትን የመፍታት ውይይት እንዲሁም ከመድልዎ ነጻ የሆነ የዳኝነት አሠራሮችን በመጠቀም ለልጅዎ የመጀመሪያ ምዘና ለማድረግ ሙከራዎች ሊያደርግ ይችላል፤ ሆኖም ግን ይህ በኤጀንሲው ላይ እንደተጣለ ግዴታ የሚቆጠር አይደለም። የአካባቢዎ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) እንዲህ ባለው ሁኔታ ለልጅዎ ምዘና ለማድረግ አለመንቀሳቀሱ የእርስዎን ልጅ ለማግኘት፣ ለመለየት እና ለመገምገም የተጣለበትን ግዴታ እንዳልተወጣ አያስቆጥርበትም።

***በመንግሥት አሳዳጊነት ሥር ያሉ ልጆች የመጀመሪያ ምዘና ልዩ ደንቦች***

በአካል ጉዳተኞች ትምህርት ሕግ ሥር ባለው አገባብ፣ *በመንግሥት አሳዳጊነት ሥር ያሉ ልጆች* ማለት ልጁ በሚኖርበት ክፍለ ግዛት መንግሥት በተሰጠው ትርጓሜ መሠረት፡-

- በአሳዳጊ ቤተሰብ ዘንድ የሚገኝ/የምትገኝ ልጅ፤
- በክፍለ ግዛት ሕግ መሠረት በመንግሥት አሳዳጊነት ሥር ያለ/ች ልጅ፤
- በመንግሥት የሕጻናት ማሳደጊያ ውስጥ የሚገኝ/የምትገኝ ልጅ።

ሊያውቁት የሚገባ አንድ ልዩ ሁኔታ አለ። ይህ ትርጓሜ በአካል ጉዳተኞች የትምህርት ሕግ (IDEA) እና በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ሕግ ሥር የተሰጠውን የወላጅነት ትርጓሜ የሚያሟላ አሳዳጊ ቤተሰብ ባለው ልጅ ላይ ይህ ትርጓሜ ተፈጻሚነት የለውም።

አንድ ልጅ በመንግሥት አሳዳጊነት ሥር ያለ/ች እና ከወላጆቹ/ቿ ጋር የማይኖር/የማትኖር ከሆነ፣ ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች፣ የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ይህ/ች ልጅ የአካል ጉዳት ያለበት/ያለባት ስለመሆኑ ለመወሰን የመጀመሪያ ምዘና ለማድረግ የወላጅ ፈቃድ አያስፈልገውም፡-

- ምክንያታዊ ጥረት ቢያደርግም የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) የልጁን/የልጅቷን ወላጆች ለማግኘት ያልቻለ እንደሆነ፤
- በክፍለ ግዛት ሕግጋት መሠረት የወላጆች መብት የተቋረጠ እንደሆነ፤ <u>ወይም</u>
- የፍርድ ቤት ዳኛ ትምህርት ነክ ውሳኔዎችን ከወላጅ ይልቅ ሌላ ሰው እንዲወስን የመደቡ እንደሆነ እና እንዲህ ያለው ሰው የመጀመሪያ ምዘና እንዲካሄድ ፈቃዱን የሰጠ እንደሆነ።

**ለአገልግሎቶች የሚሰጥ የወላጅ ፈቃድ**

የአካባቢዎ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ለመጀመሪያ ጊዜ ለልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልገሎቶችን ከመስጠቱ እንዲሁም በልጅዎ ምደባ ላይ ማናቸውንም ዓይነት ለውጥ ከማድረጉ በፊት ከእርስዎ በመረጃ ላይ የተመሠረተ ፈቃድ ማግኘት አለበት።

የአካባቢዎ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ለልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልገሎቶችን ከመስጠቱ በፊት የእርስዎን በመረጃ ላይ የተመሠረተ ፈቃድ ለማግኘት የሚችለውን ምክንያታዊ ጥረት ሁሉ ማድረግ አለበት።

ልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች እንዲያገኝ/እንድታገኝ ፈቃድዎን እንዲሰጡ ለቀረበልዎ ጥያቄ ምላሽ ያልሰጡ እንደሆነ ወይም ፈቃድዎን ለመስጠት ካልፈለጉ ወይም ከጊዜ በኋላ ፈቃድዎን በጽሁፍ ያነሱ (የሰረዙ) እንደሆነ፣ የእርስዎን ፈቃድ ለማግኘት ወይም የእርስዎ ፈቃድ ሳያስፈልግ ልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች (የልጅዎ ግላዊ ትምህርት ቡድን በሚያቀርበው የውሳኔ ሃሳብ መሠረት) ለልጅዎ እንዲሰጥ ይወሰን ዘንድ የአካባቢዎ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ፕሮሲጀራል

ሴፍጋርድስ በመባል የሚታወቁትን ዘዴዎች (የሽምግልና፣ የዳኝነት አቤቱታ፣ አለመግባባትን የመፍታት ውይይት ወይም ከመድልዖ ነጻ ዳኝነት) ላይጠቀም ይችላል።

ልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ ትምሕርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች እንዲያገኝ/እንድታገኝ ፈቃድዎን ለመስጠት ካልፈለጉ፣ ወይም እንዲህ ያለውን ፈቃድ እንዲሰጡ ለቀረበልዎት ጥያቄ ምላሽ ያልሰጡ እንደሆነ፣ ወይም ፈቃድዎን ከሰጡ በኋላ ቆየት ብለው ፈቃድዎን በጽሁፍ ያነሱ (የሰረዙ) ከሆነ እና የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ፈቃድዎ የተጠየቀበትን ልዩ ትምሕርት እና ተያያዥ አገልግሎቶችን ለልጅዎ ያልሰጡ እንደሆነ፣ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA)፦

- እነዚህን አገልግሎቶች ለልጅዎ ሳይሰጥ በመቅረቱ፣ ነጻ አግባብነት ያለው የሕዝብ ትምሕርት (FAPE) ለልጅዎ የመስጠት ግዴታውን ጥሷል አያስብልም፤ **እንዲሁም**
- እርስዎ ፈቃድ እንዲሰጡ የተጠየቁበትን ልዩ ትምሕርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ለመስጠት የግላዊ ትምሕርት ፕሮግራም ስብሰባ ማካሄድ ወይም የግላዊ ትምሕርት ፕሮግራም የማጎልበት ግዴታ አይኖርበትም።

ልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ ትምሕርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ካገኘ/ች በኋላ ፈቃድዎን በማናቸውም ጊዜ በጽሁፍ ያነሱ እንደሆነ፣ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) እንዲህ ያሉትን አገልግሎቶች መስጠቱን ላይቀጥልበት ይችላል፤ ሆኖም ግን እነዚህን አገልግሎቶች ከማቋረጡ በፊት ***ቅድመ የጽሁፍ ማሳወቂያ*** በሚለው ርዕስ ስር ለእርስዎ አስቀድሞ የጽሁፍ ማሳወቂያ መስጠት አለበት።

**ለዳግም ምዘና የሚሰጥ የወላጅ ፈቃድ**

የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ከዚህ የሚከተሉትን ማስረዳት ካልቻለ በቀር፣ ለልጅዎ ዳግም ምዘና ከማካሄዱ በፊት የእርስዎን በመረጃ ላይ የተመሠረተ ፈቃድ ማግኘት አለበት፦

- ለልጅዎ ዳግም ምዘና የእርስዎን ፈቃድ ለማግኘት ምክንያታዊ እርምጃዎች የወሰደ መሆኑን፣ **እና**
- እርስዎ ምላሽ ያልሰጡ መሆኑን።

ለልጅዎ ዳግም ምዘና እንዲካሄድ ፈቃድዎን ለመስጠት ፈቃደኛ ካልሆኑ፣ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) እርስዎ ፈቃድዎን ባይሰጡ እንኳን ለልጅዎ ዳግም ምዘና ለማካሄድ የሽምግልና፣ የዳኝነት አቤቱታ፣ አለመግባባትን የመፍታት ውይይት ወይም ከመድልዖ ነጻ የሆነ የዳኝነት ዘዴዎችን ሊጠቀም ይችላል፤ ሆኖም ግን እነዚህን ዘዴዎች መጠቀም በኤጀንሲው ላይ እንደግዴታ የተጣለ አይደለም። እንደመጀመሪያ ምዘናዎች ሁሉ፣ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በዚህ መልኩ ዳግም ምዘናውን ለማድረግ ጥረት ባያደርግ እንኳን በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ሥር ግዴታዎቹን እንደጣሰ አይቆጠርም።

**የወላጅን ፈቃድ ለማግኘት ምክንያታዊ ጥረቶች መደረጋቸውን የሚያሳዩ ሰነዶች**

የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ለልጅዎ ልዩ ለመጀመሪያ ጊዜ ትምሕርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ለመስጠት፣ ለልጅዎ ዳግም ምዘና ለማድረግ የእርስዎን ፈቃድ ለማግኘት እና ለመጀመሪያ ምዘናዎች በመንግሥት የተሾሙ አሳዳጊዎችን አፈላልጎ ለማግኘት ምክንያታዊ ጥረቶች ያደረገ መሆኑን የሚያረጋግጡ ሰነዶችን መያዝ አለበት። ምክንያታዊ ጥረት የሚለው አገላለጽ ከዚህ በታች ከተዘረዘሩት የግንኙነት ዘዴዎች መካከል ቢያንስ 2 (ሁለቱን) በመጠቀም የተለያዩ ሦስት (3) ሙከራዎችን ለሦስት (3) ጊዜያት ሙከራ ማድረግን ያካትታል፦

- የተደረጉ ወይም የተሞከሩ የስልክ ጥሪዎች ዝርዝር መረጃዎች እና የእነዚህ የሥልክ ጥሪዎች ውጤቶች፤
- የተላኩ ደብዳቤዎች እና የደረሱ ምላሾች፤ ወይም
- ወደ እርስዎ ቤት ወይም ወደ ሥራ ቦታዎ የተደረጉ ጉብኝቶች እና እንዲህ ያሉ ጉብኝቶች ውጤቶች።

ለመጀመሪያ ምዘትና የእርስዎን ፈቃድ ለማግኘት በቂ የሆነ ጥረት ለማድረግ ሲባል ሪፌራል በተሰጠ በዐሥር (10) ቀናት ውስጥ ጥረቶች መደረግ መጀመር አለባቸው።

**ሌሎች ፈቃድ የመስጠት መስፈርቶች**

ከዚህ የሚከተሉት የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ከመደረጋቸው በፊት የዕርስዎን ፈቃድ መጠየቅ አስላጊ አይሆንም፦

- የእርስዎ ልጅ ምዘና ወይም ዳግም ምዘና አካል በሆነ መልኩ በወቅቱ ያሉ መረጃዎችን መፈተሽ፤ ወይም
- ለሌሎች ልጆች ሁሉ የሚሰጥ ፈተና ለልጅዎም መስጠት፤ ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው እንዲህ ያለው ፈተና ከመሰጠቱ ወይም ምዘናው ከመካሄዱ በፊት ለሁሉም ልጆች ከሁሉም ወላጆች ፈቃድ መጠየቅ የሚያስፈልግ ካልሆነ በቀር ነው።

ልጅዎ በራስዎ ወጪ በግል ትምሕርት ቤት ውስጥ የሚማር/የምትማር ከሆነ/ች ወይም ልጅዎን በቤት ውስጥ የሚያስተምሩ ከሆነ፣ ለልጅዎ የመጀመሪያ ምዘና ወይም ለዳግም ምዘና ፈቃድዎን ያልሰጡ እንደሆነ፣ ወይም ፈቃድዎን እንዲሰጡ ለቀረበልዎ ጥያቄ ምላሽ ያልሰጡ እንደሆነ፣ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) አለመግባባትን ለመፍታት የተቀመጡትን ሂደቶች (ማለትም የሽምግልና፣ የዳኝነት አቤቱታ፣ አለመግባባትን የመፍታት ውይይት ወይም ከመድልዖ ነጻ የሆነ ዳኝነት) ላይጠቀም ይችላል፤ በዚህም መልኩ ልጅዎ ተመጣጣኝ አገልግሎቶችን (የአካል ጉዳት ያለባቸው እና ወላጆቻቸው ወደ ግል ትምሕርት ቤት ያስገቧቸው ልጆች የሚያገኟቸው አገልግሎቶች) ለማግኘት ብቁ ነው/ናት የሚል ድምዳሜ ላይ የመድረስ ግዴታ የለበትም።

**34 CFR §300.502**

**ትርጓሜዎች**

*ገለልተኛ የትምሕርት ምዘና* (IEE) ማለት ለእርስዎ ልጅ ትምሕርት ለመስጠት ኃላፊነት ባለበት የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ያልተቀጠረ፣ ብቃት ያለው ፈታኝ ማለት ነው። ከዚህ በታች እንደተብራራው፣ ለልጅዎ በአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ በተካሄደው ምዘና ውጤት ካልተስማሙ፣ ልጅዎ በገለልተኛ መዛኝ እንዲፈተን/እንድትፈተን ማድረግ ይችላሉ። ገለልተኛ የትምሕርት ምዘና ከጠየቁ፣ የሚመለከተው የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ገለልተኛ የትምሕርት ምዘና የት እንደሚገኝ እና እንዲህ ባለው ገለልተኛ መዛኝ ላይ ተፈጻሚነት ስላላቸው የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) መስፈርቶች መረጃ ሊሰጥዎ ይገባል።

*የመንግሥት ወጪ* የሚለው አገላለጽ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) የምዘናውን ሙሉ ወጪ እንደሚሸፍን ወይም ምዘናው በእርስዎ ላይ ምንም ዓይነት ወጪ በማያስከትል መልኩ መካሄዱን እንደሚያረጋግጥ የሚያሳይ ነው። ይህ ድንጋጌ ከአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) ጋር የተጣጣመ ነው፤ ይህ ሕግ እያንዳንዱ ክፍለ ግዛት በሕጉ በክፍል ቢ የተቀመጡትን መስፈርቶች ለማሟላት ማናቸውንም የክፍለ ግዛት፣ የአካባቢ፣ የፌዴራል ወይም የግል ምንጮችን እንዲጠቀም ይፈቅዳል።

**ወላጆች በመንግሥት ወጪ ምዘና እንዲካሄድ ስላላቸው መብት**

በሚመለከተው አካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ ለልጅዎ ባካሄደው ምዘና በተገኘው ውጤት የማይስማሙ ከሆነ፣ በመንግሥት ወጪ ገለልተኛ የትምሕርት ምዘና የመጠየቅ መብት ያለዎ ሲሆን፣ ይህም ተፈጻሚ የሚሆነው በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው:-

- ለልጅዎ በመንግሥት ወጪ ገለልተኛ የትምሕርት ምዘና እንዲካሄድ ከጠየቁ፣ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ያለአንዳች አላስፈላጊ መዘግየት <u>ከሚከተሉት አንዱን መፈጸም አለበት</u>:- (ሀ) ለልጅዎ የተካሄደው ግምገማ አግባብነት ያለው መሆኑን ለማሳየት የዳኝነት አቤቱታ ማቅረብ፤ <u>ወይም</u> (ለ) እርስዎ ያቀረቡት የልጅዎት የምዘና ውጤት የአካባቢዎን የትምሕርት ኤጀንሲ መስፈርቶች የሚያሟላ አለመሆኑን በችሎት ለማስረዳት ካልቻለ በቀር በመንግሥት ወጪ ገለልተኛ የትምሕርት ምዘና ማቅረብ አለበት።
- የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ጉዳዩ በችሎት እንዲታይ ከጠየቀ እና የዚህም ውሳኔ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ለልጅዎ ያካሄደው ምዘና አግባብነት ያለው የሚል ከሆነ፣ በራስዎ ወጪ ገለልተኛ የትምሕርት ምዘና ማድረግ ይችላሉ።
- ለልጅዎ ገለልተኛ የትምሕርት ምዘና እንዲካሄድ ከጠየቁ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በኤጀንሲው የተካሄደውን ምዘና የተቃወሙበት ምክንያት ምን እንደሆነ ሊጠይቅዎ ይችላል። ሆኖም ግን የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ለልጅዎ ያካሄደውን ምዘና ለመከላከል ሲል ማብራሪያ መጠየቅ ወይም በመንግሥት ወጪ የሚካሄውን ገለልተኛ ምዘና ወይም ጉዳዩ በዳኝነት እንዲታይ አቤቱታ ማቅረብን ማዘግየት አይችልም።

የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ለልጅዎ ላካሄደው እና እርስዎ ለማይስማሙበት ለእያንዳንዱ ምዘና በመንግሥት ወጪ ገለልተኛ ምዘና ማግኘት የሚችሉት አንድ ጊዜ ብቻ ነው።

**በወላጅ ጥያቄ ስለሚካሄዱ ምዘናዎች**

ለልጅዎ በመንግሥት ወጪ ገለልተኛ የትምሕርት ምዘና ከተካሄደ ወይም በራስዎ ወጪ የተካሄደን የገለልተኛ ምዘና ውጤት ለአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ ካቀረቡ፣ ከዚህ የሚከተሉት ተፈጻሚ ይሆናሉ:-

- የልጅዎ ምዘና የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ለገለልተኛ ትምሕርታዊ ምዘናዎች ያስቀመጠውን መስፈርት የሚያሟላ ሆኖ ከተገኘ፣ ለልጅዎ ነጻ አግባብነት ያለውን የሕዝብ ትምሕርት ከመስጠት ጋር በተያያዘ ለሚወሰነው ማንኛውም ውሳኔ እንደግብዓት መጠቀም ይኖርበታል፤ <u>እንዲሁም</u>
- እርስዎ ወይም የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ልጅዎን በማስመልከት በዳኝነት ሂደት እንደማስጃ ልታቀርቡት ትችላላችሁ።

**በአቤቱታ ሰሚ አካላት ስለሚነሳ የምዘና ጥያቄ**

አቤቱታ ሰሚው በዳኝነት መሰማት ሂደት ለልጅዎ ገለልተኛ ትምሕርታዊ ምዘና እንዲካሄድ የጠየቀ እንደሆነ፣ የምዘናው ወጪ በመንግሥት መሸፈን አለበት።

**የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) መስፈርት**

ገለልተኛ የትምሕርት ምዘና በመንግሥት ወጪ የሚካሄድ ከሆነ፣ ምዘናው የሚገኝበት መስፈርት፣ የምዘናውን ቦታ እና ምዘናውን የሚያካሂደውን ፈታኝ የትምርት ደረጃ አካትቶ፣ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) አንድን ምዘና በሚጀምርበት ጊዜ ከሚጠቀምበት መስፈርት ጋር ተመሳሳይ ሊሆን ይገባል (ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው መስፈርቶቹ ገለልተኛ የትምሕርት ምዘና እንዲካሄድ ለማድረግ ካለዎት መብት ጋር አብረው የሚሄዱ እስከሆኑ ድረስ ነው)።

ከላይ ከተገለጸው መስፈርት ውጪ፣ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በመንግሥት ወጪ በሚካሄድ ገለልተኛ ትምሕርታዊ ምዘና ላይ ሁኔታዎች እና የጊዜ ሰሌዳዎች መጣል የለበትም።

## የግላዊ ትምሕርት ፕሮግራም ስብሰባዎች ከተካሄዱ በኋላ ሰነዶችን ስለመስጠት

### የዲ.ሲ. ኦፊሺያል ኮድ § 38-2571.03

የግላዊ ትምሕርት ፕሮግራም ቡድን ስብሰባዎች ከመካሄዳቸው በፊት እና ከተካሄዱ በኃላ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) አንዳንድ ሰነዶችን ሊሰጥዎ ይገባል። ቡድኑ ስለግላዊ ትምሕርት ፕሮግራም ወይም ለልዩ ትምሕርት ብቁ ስለመሆን የሚወያይበት ስብሰባ ከመካሄዱ ቢያንስ ከ5 የሥራ ቀናት በፊት የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በስብሰባው ላይ ውይይት የሚደረግበትን ክልከላ ያልተጣለበት ማናቸውንም ምዘና፣ ግምገማ፣ ሪፖርት፣ የመረጃ ቻርት ወይም ሌላ ሰነድ ሊሰጥዎ ይገባል። ስብሰባው የሚካሄደው ከ5 ቀናት በአጠረ ጊዜ ከሆነ፣ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) የግላዊ ትምሕርት ፕሮግራም ስብሰባው ከመካሄዱ ቢያንስ ከ24 ሰዓታት አስቀድሞ ሰነዶቹን ለእርስዎ መስጠት አለበት።

አዲስ ወይም የተሻሻለ ግላዊ የትምሕርት ፕሮግራም (IEP) ላይ ስምምነት የተደረሰበት ስብሰባ ከተካሄደ በኋላ 5 የሥራ ቀናት ሳያልፉ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) የግላዊ ትምሕርቱን ፕሮግራም ቅጂ ሊሰጥዎ ይገባል። የግላዊ ትምሕርት ፕሮግራሙ በ5ኛው የሥራ ቀን ያልተጠናቀቀ እንደሆነ ወይም የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በዲ.ሲ. የቋንቋ ተደራሽነት ሕግ (የዲ.ሲ ኮድ § 2-1931 *et seq.*) መሠረት ሰነዱን ወደ እርስዎ ቋንቋ ለማስተርጎም ተጨማሪ ጊዜ የሚያስፈልገው ከሆነ፣ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ለጊዜው ሊያገኝ የቻለውን የግላዊ ትምሕርት ፕሮግራም ረቂቅ፣ ሲጠናቀቅ ደግሞ የመጨረሻውን ቅጂ ሊሰጥዎ ይገባል። የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ስምምነት የተደረሰበትን ግላዊ የትምሕርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባው ከተካሄደበት ቀን አንስቶ በ15 የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ለእርስዎ መስጠት አለበት።

## የወላጅ ምልከታ

### የዲ.ሲ. ኦፊሺያል ኮድ § 38-2571.03

በእርስዎ ጥያቄ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) እርስዎ ወይም የእርስዎ ተወካይ የልጅዎን ወቅታዊ ወይም የወደፊት ፕሮግራም በተገቢው ጊዜ እንድትመለከቱ ዕድል መስጠት አለበት። የእርስዎ ተወካይ፡-

- ምልከታው በሚደረግበት ልዩ የትምሕርት መስክ ሙያዊ ልምድ ያለው ሊሆን ይገባል፤ ወይም
- የአካል ጉዳት ካለብዎ ወይም የቋንቋ ትርጉም እገዛ ካስፈለገዎ እስዎን ለመርዳት የእርሱ መገኘት አስፈላጊ ሊሆን ይገባል።

የእርስዎ ተወካይ ከዚህ የሚከተሉትን መሆን **የለበትም**፡-

- ነጻ አግባብነት ያለው የሕዝብ ትምሕርት (FAPE) ለልጅዎ ከመስጠት ጋር በተያያዘ በሕግ በክርክር ወቀት እርስዎን የሚወክል መሆን የለበትም፤
- በክርክሩ ውጤት የገንዘብ ጥቅም የሚያገኝ ሰው ሊሆን አይገባም።

እርስዎም ሆኑ የእርስዎ ተወካይ በምልከታው ወቅት የተገኘን መረጃ መግለጽ ወይም በዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ ወይም በአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ ላይ ለሚከፈት ክርክር ደንበኞችን ለመፈለግ ወይም በክርክር ላይ እንዲሳተፉ ለማድረግ መጠቀም አይፈቀድም።

እርስዎ ወይም የእርስዎ ወኪል አሁን ባለው ፕሮግራም የልጅዎን አፈጻጸም ወይም እንቅስቃሴ ለመመዘን ወይም በሃሳብነት የቀረበ ፕሮግራም ልጅዎን በምን መልኩ ሊደገፍ እንደሚችል ለመገምገም የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በቂ የምልከታ በቂ ጊዜ ሊሰጣችሁ ይገባል። የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ትምሕርቱ በሚሰጥበት ሁኔታ የልጅዎን የትምሕርት አሰጣጥ ሁኔታ ወይም በሃሳብነት በቀረበው ፕሮግራም ልጅዎ ተሳታፊ የሚሆን/ የምትሆን ከሆነ ፕሮግራሙ በመደበኛነት የሚካሄድበትን ሁኔታ እርስዎ ወይም የእርስዎ ወኪል ለማየት እንድትችሉ ማስቻል አለበት።

የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ምልከታውን ማድረግ እንደምትፈልጉ አስቀድማችሁ እንድታሳውቁ፣ እና ወኪልዎን በጽሁፍ እንዲወክሉ ሊጠይቅ ይችላል። ከዚህ እንደሚከተለው አስፈላጊ ከሆኑት በስተቀር የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ሌሎች ሁኔታዎችን ወይም ክልከላዎችን ማስቀመጥ አይችልም፡-

- በፕሮግራሙ ያሉ ሌሎች ልጆችን ደሕንነት ለመጠበቅ፤
- ተመልካቹ ሰው የሌሎችን ልጆች ምስጢራዊ መረጃ እንዳይገልጽ ለመጠበቅ፤ ወይም
- በትምሕርት ክፍል ውስጥ በርካታ ተመልካቾች በተመሳሳይ ጊዜ በመኖራቸው ምክንያት ይህ ሁኔታ ማስተጓጎል እንዳይፈጥር ለማድረግ።

የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) የምልከታ ፖሊሲውን ይፋ ማድረግ አለበት።

ከላይ በተገለጸው መልኩ ምልከታ ለማድረግ ያለዎት መብት በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) ወይም በሌሎች አግባብነት ባላቸው ሕግጋት መሠረት ያለዎትን ማናቸውም መብት የሚገድብ አይደለም።

## ትርጓሜዎች

### 34 CFR §§300.611 and 300.32

በየመረጃዎች ምስጢራዊነት በሚለው ርዕስ ሥር፡-

- *ማውደም* ማለት ቁስ አካላዊ ውድመት ወይም ከመረጃው ላይ ግለሰቦችን የሚለዩ ቃላትን በማስወገድ መረጃው አንድን ግለሰብ የሚለይ እንዳይሆን ማድረግ ነው።
- *የትምሕርት ሪከርድ* ማለት በ34 CFR ክፍል 99 (የቤተሰብ ትምሕርት መብቶችን እና የግል መረጃ ጥበቃ ሕግ የ1974፣ 20 U.S.C. 1232g (FERPA) ማስፈጸሚያ ደንቦች) ውስጥ "በትምርት ሪከርዶች" ትርጓሜ ስር የተሸፈኑ የሪከርድ አይነቶች ነው።
- *ተሳታፊ ኤጀንሲ* ማለት በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA)፣ በክፍል ቢ ሥር ማናቸውም ማንነትን የሚገልጹ ወይም ማንነትን ለመለየት የሚያስችሉ መረጃዎች ሊገኙባቸው የሚችሉ መረጃዎችን የሚሰበስብ፣ የሚይዝ ወይም የሚጠቀም የትምሕርት ቤቶች ዲስትሪክት፣ ኤጀንሲ ወይም ተቋም ነው።
- *ግላዊ ማንነትን የሚገልጹ መረጃዎች* ማለት ከዚህ የሚከተሉትን መረጃዎች የሚያካትት ነው፡-
    - ሀ. የልጅዎ ሥም፣ እንደወላጅ የእርስዎ ሥም፣ ወይም የሌላ የቤተሰብ አባል ሥም፤
    - ለ. የልጅዎ አድራሻ፤
    - ሐ. ግላዊ ማንነትን የሚገልጽ መረጃ፣ ለምሳሌ የልጅዎ ማሕበራዊ ዋስትና ቁጥር ወይም የተማሪ መለያ ቁጥር፤ **<u>ወይም</u>**
    - መ. ልጅዎን በምክንያታዊ እርግጠኝነት ለመለየት የሚያስችሉ ግላዊ ባሕርያት ወይም ሌሎች መረጃዎች ዝርዝር።

## ለወላጆች የሚሰጥ ማሳወቂያ

### 34 CFR §300.612

የክፍለ ግዛቱ የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE)፣ የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኤጀንሲ እንደመሆኑ መጠን ከዚህ የሚከተሉትን አካትቶ ግላዊ ማንነትን የሚገልጹ መረጃዎች ምስጢራዊ መሆናቸውን ለእርስዎ ሙሉ በሙሉ ለመግለጽ በቂ የሆነ ማሳወቂያ መስጠት አለበት፡-

- ማሳወቂያው በዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ በሚገኙ የተለያዩ ሕዝቦች የተለያዩ ቋንቋዎች ስለሚሰጥበት ሁኔታ የሚገልጽ ማብራሪያ፤
- ግላዊ ማንነትን የሚገለጹ መረጃዎች የሚያዙላቸው ልጆች የትኞቹ መሆናቸውን፣ የሚፈለጉት መረጃዎች እንዴት ዓይነት ያሉት መሆናቸውን፣ ዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ እንዲህ ያሉትን መረጃዎች የሚሰበስባቸውን ዘዴዎች (መረጃዎቹ የሚሰበሰቡት ከየትኞቹ ምንጮች እንደሆነ)፣ እንዲሁም መረጃዎቹ በምን መልኩ ጥቅም ላይ እንደሚውሉ ማብራራት አለበት፤
- ተሳታፊ ኤጀንሲዎች ግላዊ ማንነትን የሚገልጹ መረጃዎችን ሲያስቀምጡ፣ ለሦስተኛ ወገን ሲገልጹ፣ ይዘው ሲያቆዩ እና መረጃዎቹን በሚያስወግዱበት ጊዜ ስለሚከተሏቸው ፖሊሲዎች እና የአሰራር ሂደቶች ማጠቃለያ፤ <u>እንዲሁም</u>
- በቤተሰብ የትምሕርት እና የግላዊ መረጃ ጥበቃ ሕግ (FERPA) እና በ34 CFR Part 99 በሕጉ ማስፈጸሚያ ደንቦች ሥር ወላጆች እና ልጆች እነዚህን መረጃዎች አስመልክቶ ያሏቸው መብቶች ሁሉ መብራራት አለባቸው።

ልዩ ትምሕርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች የሚያስፈልጓቸውን ልጆች ለመለየት፣ ለመመደብ እና ለመመዘን (በተጨማሪም *ቻይድ ፋይንድ* በመባል የሚታወቅ) ዋነኛ የሚባል ማናቸውም ተግባር ከመፈጸሙ በፊት፣ በመላው ዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ የሚገኙ ወላጆች ዘንድ ለመድረስ በቂ ስርጭት ባላቸው ጋዜጦች እና/ወይም ሌላ ሚዲያ ማሳወቂያው መታተም አለበት።

## የተደራሽነት መብቶች

### 34 CFR §300.613 እና 5E DCMR §2600.2

ተሳታፊው ኤጀንሲ፣ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) ሥር ከልጅዎ ጋር በተያያዘ የሚሰበስባቸውን፣ የሚይዛቸውን እና የሚጠቀምባቸውን ማናቸውም ትምሕርት ነክ መረጃዎች እንዲያዩ እና እንዲፈትሹ መፍቀድ አለበት። ተሳታፊው ኤጀንሲ ያልምንም አላስፈላጊ መዘግየት እና የግላዊ ትምሕርት ፕሮግራም ስብሰባ ከመካሄዱ በፊት ወይም ማናቸውም ከመድልዖ ነጻ የሆነ የዳኝነት ችሎት (አለመግባባትን የመፍታት ወይም ሥነ-ሥርዓትን አስመልክቶ ሚካሄድ የችሎት መሰማት ሂደትን አካትቶ) ከመካሄዱ በፊት የልጅዎን ማናቸውንም ትምሕርት ነክ መረጃዎች ለማየት እና ለመፈተሽ የሚያቀርቡትን

ጥያቄ መቀበል እና ማስተናገድ አለበት፤ በማናቸውም ሁኔታ ጥያቄ ካቀረቡ ከአርባ አምስት (45) ተከታታይ ቀናት በላይ ሊዘገይ አይችልም።

የትምሕርት ሪከርዶችን የማየት እና የመፈተሽ መብትዎ ከዚህ የሚከተሉትን ያካተተ ነው፦

- በሪከርዶች ላይ የማብራሪያ እና የሪከርዶቹን ትርጓሜ አስመልክቶ ለሚያቀርቧቸው ምክንያታዊ ጥያቄዎች ከተሳታፊው ኤጀንሲ ምላሽ የማግኘት መብት አለዎት፤
- የልጅዎን ትምሕርት ነክ ሪከርዶች የማየት እና የመገምገም መብትዎ፣ ***ክፍያዎች*** በሚለው ንዑስ ርዕስ ሥር የተጠቀሰውን ምክንያታዊ የሆነ ክፍያ ከፍለው የሪከርዱን ቅጂ የማግኘት መብትን ያካተተ ነው፤ <u>እንዲሁም</u>
- ሕጋዊ ወኪልዎ ሪከርዶቹን እንዲያይ እና እንዲፈትሽ የማድረግ መብት አለዎት።

በኮሎምቢያ ሕግጋት ስሞግዚትነት፣ መለያየት እና/ወይም ፍቺ በሚደነግጉት ሕግጋት ሥር እርስዎ ሥልጣን የለዎትም የሚል መረጃ ካልደረሰው በስተቀር ተሳታፊው ኤጀንሲ እርስዎ የልጅዎን ሪከርዶች የማየት እና የመፈተሽ ሥልጣን አለዎት የሚል ግምት መውሰድ አለበት።

## የመረጃ ተደራሽነት ሪከርድ

**34 CFR §300.614**

እያንዳንዱ ተሳታፊ ኤጀንሲ በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ሥር (ወላጆች እና የተሳታፊው ኤጀንሲ ሠራተኞች መረጃዎቹን ሊያገኙ የሚችሉ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ እነርሱን ሳያካትት) በእርሱ የተሰበሰቡ ፣ እርሱ ዘንድ የሚገኙ እና ሥራ ላይ የሚውሉ መረጃዎችን ለማግኘት የሚችሉ አካላትን ዝርዝር መያዝ አለበት፤ በዚህም ሪከርድ ሥር፣ መረጃውን የሚያይ ወይም የሚያገኝ አካል ሥም፣ መረጃውን እንዲያገኝ ፈቃድ ያገኘበት ቀን እና መረጃዎቹን ለምን እንደሚፈልጋቸው መካተት አለባቸው።

## ከአንድ በላይ የሆኑ ልጆች ሪከርዶች

**34 CFR §300.615**

ማንኛውን የትምሕርት ሪከርድ ከአንድ በላይ የሆኑ ልጆችን የሚመለከት በሚሆን ጊዜ፣ መረጃውን የመፈተሽ፣ የማየት እና እርሱንም አስመልክቶ መረጃ ወይም ማሳወቂያ የማግኘት መብትዎ ተፈጻሚነት የሚኖረው የእርስዎን ልጅ መረጃዎች በተመለከተ ብቻ ነው።

## የመረጃዎች ዓይነቶች እና መገኛዎች ዝርዝር

**34 CFR §300.616**

ጥያቄ በሚያቀርቡለት ጊዜ እያንዳንዱ ተሳታፊ ኤጀንሲ በእርሱ የተሰበሰቡ፣ በኤጀንሲው የሚገኙ እና ሥራ ላይ የሚውሉ መረጃዎች ዓይነት እና መገኛቸውን የሚገልጽ ዝርዝር ሊሰጥዎ ይገባል።

## ክፍያዎች

**34 CFR §300.617**

እያንዳንዱ ተሳታፊ ኤጀንሲ በአካል ጉዳተኞች ትምሕርት ሕግ በክፍል ቢ ሥር ለእርስዎ ለተዘጋጁ የሪከርዶች ቅጂዎች ምክንያታዊ የሆነ ክፍያ ሊያስከፍል ይችላል፤ ይህ ተፈጻሚ የሚሆነው ክፍያው እነዚህን ሪከርዶች ለማየት እና ለመፈተሽ ያለዎትን መብት ሙሉ በሙሉ የማያስቀር ከሆነ ነው።

አንድ ተሳታፊ ኤጀንሲ በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) ሥር መረጃዎችን ለመፈለግ እና ለማግኘት ክፍያ ማስከፈል አይችልም።

## በወላጅ በሚቀርብ ጥያቄ በሪከርዶች ላይ ስለሚደረግ ማሻሻያ

**34 CFR §300.618**

በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ስር ልጅዎን አስመልክቶ የተሰበሰበው፣ የተያዘው እና ሥራ ላይ የዋለው መረጃ ስህተት፣ ሊያሳስት የሚችል ወይም የልጅዎን የግል መረጃዎች ጥበቃ መብት የሚጥስ ነው ብለው ካመኑ፣ መረጃውን የያዘው ተሳታፊ ኤጀንሲ መረጃው ላይ ለውጦችን እንዲያደርግ ጥያቄ ሊያቀርቡለት ይችላሉ።

ተሳታፊውም ኤጀንሲ የእርስዎ ጥያቄ በደረሰው ምክንያታዊ በሆነ ጊዜ ውስጥ በጥያቄዎ መሠረት በመረጃው ላይ ለውጥ ስለማድረግ ውሳኔ ማሳለፍ አለበት።

ተሳታፊው ኤጀንሲ በእርስዎ ጥያቄ መሠረት በመረጃዎቹ ላይ ለውጥ ለማድረግ ፈቃደኛ ካልሆነ፣ ይህንን ውሳኔውን ለእርስዎ ማሳወቅ እና ***የአቤቱታ መሰማት ዕድል*** በሚለው ርዕስ ስር አቤቱታ የማሰማት መብት ያለዎት መሆኑን መግለጽ አለበት።

## የአቤቱታ መሰማት ዕድል

### 34 CFR §300.619

በእስዎ በሚቀርብለት ጥያቄ መሠረት ተሳታፊው ኤጀንሲ በትምሕርት ሪከርዶች ውስጥ ያለው የልጅዎ መረጃ ስህተት እንዳልሆነ፣ የሚያሳስትም አለመሆኑን ወይም በሌላ መልኩ የልጅዎን የግላዊ መረጃ ሙብት የሚጥስ አለመሆኑን ለማስረዳት የአቤቱታ መሰማት ዕድል ሊሰጥዎ ይገባል።

## የአቤቱታ መሰማት ሂደት

### 34 CFR §300.621

የትምሕርት ሪከርዶች ውስጥ በተካተተ መረጃ ላይ የሚቀርብ አቤቱታ መሰማት ያለበት በቤተሰብ ትምሕርት ሙብት እና የግል መረጃ ጥበቃ ሕግ (FERPA) ስለእንደዚህ ዓይነት የአቤቱታ ሂደቶች በተደነገገው መሠረት ሊሆን ይገባል።

## የአቤቱታ መሰማት ውጤት

### 34 CFR §300.620

በአቤቱታ መሰማቱ ሂደት ተሳታፊው ኤጀንሲ የልጅዎ መረጃ ስህተት መሆኑን፣ ሊያሳስት እንደሚችል ወይም በሌላ መልኩ የልጅዎን የግል መረጃ ጥበቃ ወይም ሌላ ሙብት የሚጥስ መሆኑን ከወሰነ፣ መረጃውን መቀየር እና ይህንኑ ለእርስዎ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት።

ተሳታፊው ኤጀንሲ በአቤቱታ መሰማት ሂደት አማካኝነት መረጃው ስህተት አለመሆኑን፣ ሊያሳስት እንደማይችል ወይም በሌላ መልኩ የልጅዎን የግል መረጃ ጥበቃ ወይም ሌላ ሙብት የሚጥስ አለመሆኑን ከወሰነ፣ በኤጀንሲው ዘንድ በሚገኘው የልጅዎ መረጃ በተካተተበት ሪከርድ ውስጥ በመረጃው ላይ ያለዎትን አስተያየት ማስፈር ወይም በተሳታፊው ኤጀንሲ ውሳኔ የማይስማሙበትን ማንኛውንም ምክንያት ማስቀመጥ እንደሚችሉ ሊግልጽልዎ ይገባል።

እንዲህ ያለው ማብራሪያ፡

- በተሳታፊው ኤጀንሲ ዘንድ ለልጅዎ ሪከርዶች ጋር በአንድነት መቀመጥ አለበት፤ ይህም ተፈጻሚ የሚሆነው ኤጀንሲው መረጃውን ወይም ተቃውሞ ያነሱበትን የመረጃውን ክፍል ይዞ እስከሚቆይበት ጊዜ ድረስ ነው፤ <u>እንዲሁም</u>
- ተሳታፊው ኤጀንሲ የልጅዎን ሪከርዶች ወይም ተቃውሞ የተነሳበትን መረጃ ለማንኛውም ሦስተኛ ወገን በሚገልጽበት ጊዜ በእርስዎ የተነሳውም ተቃውሞ አብሮ መገለጽ አለበት።

## ግላዊ ማንነትን የሚመለከቱ መረጃዎች እንዲገለጹ ስለሚሰጥ ፈቃድ

### 34 CFR §300.622

መረጃው በትምሕርት ሪከርዶች ውስጥ ሚካተት ከሆነ እና የመረጃው መገለጽ በቤተሰብ ትምሕርት ሙብት እና የግል መረጃ ጥበቃ ሕግ ስር ለመረጃው መገለጽ የወላጅ ፈቃድ የማይጠየቅ ካልሆነ በቀር፣ ከተሳታፊ ኤጀንሲዎች ኃላፊዎች ውጪ ለሌሎች ወገኖች ግላዊ ማንነትን የሚገልጹ መረጃዎች ከመሰጠታቸው በፊት የወላጅ ፈቃድ መገኘት አለበት። ከዚህ በማስከተል በተጠቀሱት ሁኔታዎች ካልሆነ በስተቀር፣ በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ የተቀመጡትን ዓላማዎች ለማሳካት ሲባል ለተሳታፊ ኤጀንሲዎች ኃላፊነዎች ግላዊ ማንነትን የሚገልጹ መረጃዎች ከመገለጻቸው በፊት የእርስዎን ፈቃድ መጠየቅ አስፈላጊ አይሆንም።

ግላዊ ማንነትን የሚገልጹ መረጃዎች የዝውውር አገልግሎት ለሚሰጡ ወይም ለዚህ አገልግሎት ክፍያ ለሚፈጽሙ ኤጀንሲዎች ኃላፊዎች ከመገለጻቸው በፊት የእርስዎ ወይም በዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ ሕግ መሠረት በአዋቂነት የዕድሜ ደረጃ ላይ የደረሰ ብቁ ልጅ (አስራ ስምንት (18) ዓመት የሞላው) ፈቃድ መገኘት አለበት።

ልጅዎ በሚኖሩበት የትምሕርት ቤቶች ኤጀንሲ ውስጥ በማይገኝ የግል ትምሕርት ቤት ውስጥ የሚማር/የምትማር ከሆነ፣ የግል ትምሕርት ቤቱ በሚገኝበት አካባቢ በሚመለከተው የትምሕርት ኤጀንሲ እና በሚኖሩበት አካባቢ የትምሕርት ኤጀንሲ መካከል ግላዊ ማንነትን የሚገልጹ መረጃዎች ልውውጥ ከመደረጉ በፊት የእርስዎ ፈቃድ መጠየቅ አለበት።

## ሴፍጋርድስ

### 34 CFR §300.623

እያንዳንዱ ተሳታፊ ኤጀንሲ ግላዊ ማንነትን የሚገልጹ መረጃዎችን በሚሰበስብበት፣ በሚያስቀምጥበት፣ በሚገልጽበት እና በሚያስወግድበት ጊዜ የእነዚህም መረጃዎች ምስጢራዊነት መጠበቅ አለበት። በእያንዳንዱ ተሳታፊ ኤጀንሲ ዘንድ ግላዊ ማንነትን የሚገልጹ መረጃዎች በምስጢር መያዛቸውን የሚከታተል አንድ ኃላፊ ሊመድብ ይገባል። ግላዊ ማንነትን የሚገልጹ መረጃዎችን የሚሰበስቡ ወይም የሚጠቀሙ ሰዎች ሁሉ በአካል ጉዳተኞች ትምሕርት ሕግ በክፍል ቢ እና በቤተሰብ ትምሕርታዊ ሙብቶች እና

የግል መረጃ ጥበቃ ሕግ ሥር ስለዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ ፖሊሲዎች እና አሠራሮች ሥልጠና እና መምሪያ ሊሰጣቸው ይገባል። እያንዳንዱ ተሳታፊ ኤጀንሲ ግላዊ ማንነትን የሚገልጹ መረጃዎችን ሊያገኙ የሚችሉ ሠራተኞችን ሥሞች እና የሥራ መደቦች ወቅታዊ ዝርዝር መያዝ አለበት፤ በዚህ መልኩ ዝርዝሩ መያዙም መንግሥት/ሕዝቡ ክትትል እንዲያደርግ የሚያደርገው ነው።

### *መረጃን ስለማስወገድ*

**34 CFR §300.624**

በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ስር የተሰበሰቡ፣ ተይዘው የቆዩ ወይም ሥራ ላይ የዋሉ ግላዊ ማንነትን የሚገልጹ መረጃዎች ለልጅዎ ትምሕርታዊ አገልግሎቶች ለመስጠት አስፈላጊነታቸው በሚያበቃበት ጊዜ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ይህንኑ ለእርስዎ ማሳወቅ አለበት።

*መረጃዎቹ በእርስዎ ጥያቄ መሠረት እንዲወገዱ መደረግ አለባቸው። ሆኖም ግን የልጅዎ ቋሚ ሪከርዶች፣ ማለትም የልጅዎ ሥም፣ አድራሻ እና ስልክ ቁጥር፣ የትምሕርት ውጤቶች፣ የቀሪ ሪከርድ፣ የተማረባቸው/የተማረችባቸው የትምሕርት ክፍሎች፣ ያጠናቀቀው/ያጠናቀቀችው የትምሕርት ደረጃ እና ትምሕርት የተጠናቀቀበት ዓመት የጊዜ ገደብ ሳይኖራቸው ተመዝግበው ይቆያሉ።*

## የአቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

### የዳኝነት አቤቱታ መስማት እና በክፍለ ግዛት የአቤታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት መካከል ያለው ልዩነት

በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) ክፍል ቢ፣ ስለክፍለ ግዛት የአቤቱታ አቀራረብ እና ለዳኝነት አቤቱታ መስማት የተለያዩ ሥነ-ሥርዓቶች ተቀምጠዋል። ከዚህ በታች እንደተዘረዘረው፣ ማንኛውም አንድ ግለሰብ ወይም ድርጅት የአካባቢ የትምሕርት ኤጀንሲ፣ የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ወይም ማናቸውም ሌላ የመንግሥት ኤጀንሲ ልዩ ትምሕርትን አስመልክቶ በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ እና/ወይም በዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ ሕግ መስፈርት ላይ ጥሰት ፈጽሟል የሚል የክፍለ ግዛት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል። ነገር ግን አንድን የአካል ጉዳት ያለበት ልጅ የትምሕርት ፍላጎት መለየት፣ ግምገማ እና ምደባን ከማስጀመር ወይም ከመለወጥ ጋር በተያያዘ በቀረበ ሃሳብ ወይም ጉዳዩ ውድቅ ስለመደረጉ ወይም ነጻ አግባብነት ያለው የሕዝብ ትምሕርት (FAPE) ከመስጠት ጋር በተያያዘ የዳኝነት አቤቱታ ማቅረብ የሚችሉት የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ወይም እርስዎ ብቻ ናችሁ። የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ሠራተኞች የጊዜ ገደቡ በአግባቡ ካልተራዘመ በቀር በስልሳ (60) ቀናት ጊዜ ውስጥ ለቀረበው የክፍለ ግዛት አቤቱታ መፍትሔ መስጠት ያለባቸው ሲሆን፣ ዳኝነትን ለመጠየቅ ለሚቀርብ አቤቱታ ደግሞ ገለልተኛ ኦፊሰር አቤቱታውን መስማት አለበት (ይህም የሚሆነው ጉዳዩ በውይይት ወይም በሽምግልና ሊፈታ ካልቻለ ነው)። በዚህ ሰነድ መፍትሔ የመስጠት ሒደት በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው የመፍትሔ መስጫው ጊዜ ባለፈ በአርባ አምስት (45) ተከታታይ ቀናት ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ ውሳኔውን መስጠት አለበት፤ ሆኖም ግን በእርሰዎ ወይም በአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ ጥያቄ አቤቱታውን የሚሰሙት ኦፊሰር ተጨማሪ ጊዜ ሊሰጡ ይችላሉ። የክፍለ ግዛት እና የዳኝነት አቤቱታ፣ መፍትሔ የመስጠት እና የአቤቱታ መስማት ሂደቶች በይበልጥ በዝርዝር ከዚህ በታች ተገልጸው ይገኛሉ። ***ምዴል ቅጾች*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተብራራው የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) የዳኝነት አቤቱታ ለማቅረብ እና እርስዎ ወይም ሌሎች አካላት የክፍለ ግዛት አቤቱታ ለማቅረብ የሚያግዟችሁን ቅጾችን ማጎልበት አለበት።

### የክፍለ ግዛት አቤቱታ ሥነ-ሥርዓትን ተግባራዊ ስለማድረግ

**34 CFR §300.151**

የክፍለ ግዛቱ የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ከዚህ ለሚከተሉት በጽሁፍ የተቀመጠ የአካሄድ ሥነ-ሥርዓት ሊኖረው የገባል፡
-

- በሌላ ክፍለ ግዛት የሚገኝ ድርጅት ወይም ግለሰብን አካትቶ ለማንኛውም አቤቱታ መፍትሔ የሚሰጥበት አሠራር፤
- በክፍለ ግዛቱ የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) አቤቱታ ስለሚቀርብበት ሁኔታ፤ <u>እንዲሁም</u>
- የክፍለ ግዛቱ የአቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት ለወላጆች እና ሌሎች ፈላጎቱ ላላቸው ግለሰቦች እንዲሁም ለወላጆች ሥልጠና እና መረጃ ማዕከላት፣ ለጥበቃ እና የሙብት ተከራካሪ ኤጀንሲዎች፣ ገለልተኛ የመኖሪያ ማዕከላት እና ሌሎች አግባብነት ላላቸው አካላት በሰፊው ማሠራጨት፤

#### አግባብነት ያላቸው አገልግሎት ውድቅ በሚደረግ ጊዜ ተፈጻሚነት ያላቸው መፍትሄዎች

የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) አግባብነት ያላቸውን አገልግሎቶች ሳይሰጥ መቅረቱ በተረጋገጠበት የክፍለ ግዛት አቤቱታ፣ የክፍለ ግዛቱ የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) አግባብነት ያለውን አገልግሎት ለመስጠት የተፈጸመውን ስህተት ማረም እና የሚመለከተውን/የሚመለከታትን ልጅ ፍላጎት ለማሟላት ተገቢ የሆነውን እርምጃ መውሰድ (ለምሳሌ ማካካሻ

አገልግሎቶችን ማቅረብ ወይም የገንዘብ ክፍያ መስጠት) እና ለሁሉም የአካል ጉዳት ላለባቸው ልጆች አግባብነት ያለውን አገልግሎት መስጠት አለበት።

## ለክፍለ ግዛት የአቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት ተፈጻሚ መደረግ ያለባቸው አነስተኛዎቹ ሁኔታዎች

### 34 CFR §300.152 እና የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ይፋዊ የክፍለ ግዛት አቤቱታ ፖሊሲ እና አሠራር

**የጊዜ ገደብ፤ አነስተኛዎቹ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት**

የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) በክፍለ ግዛት የአቤቱታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓቱ ውስጥ አቤቱታው ከቀረበ በኋላ ከዚህ የሚከተሉትን ለመፈጸም የ60 (ስልሳ) ተከታታይ ቀናት የጊዜ ገደብ መስቀመጥ አለበት:-

- የክፍለ ግዛቱ የትምሕርት መሥሪያ ቤት ምርመራ መካሄድ አለበት ብሎ ከወሰነ በአካል በመገኘት ገለልተኛ ምርመራ ለማድረግ፤
- በአቤቱታው ለተጠቀሱት ጉዳዮች አቤቱታ አቅራቢ ተጨማሪ የጽሁፍ ወይም የቃል መረጃ እንዲያቀርቡ ዕድል ለመስጠት፤
- የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ወይም ሌላ የመንግሥት ኤጀንሲ ለቀረበው አቤቱታ ምላሽ እንዲሰጥ ዕድል ለመስጠት፣ በዚህም ሥር ቢያንስ (ሀ) በኤጀንሲው አስተያየት የቀረበውን አቤቱታ ለመፍታት መፍትሔ የሚለውን ሃሳብ እንዲያቀርብ፤ <u>እና</u> (ለ) አቤቱታ ያቀረቡት ወላጅ እና ኤጀንሲው በገዛ ፍቃዳቸው በሽምግልና ጉዳያቸውን እንዲፈቱ ዕድል ለመስጠት፤
- አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ሁሉ ለማየት እና የአካባቢ የትምሕርት ኤጀንሲ ወይም ሌላ የመንግሥት አካል፣ በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ወይም በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የልዩ ትምሕርት ሕግ ሥር የተቀመጠን ማናቸውንም መስፈርት መጣሱን ወይም ያልጣሰ መሆኑን በገለልተኛነት ለመወሰን፤ <u>እንዲሁም</u>
- በአቤቱታው ውስጥ ለተነሳ ለእያንዳንዱ ቅሬታ በጽሁፍ ውሳኔ ለመስጠት። በውሳኔው ውስጥ (ሀ) የፍሬ ነገር ግኝቶች <u>**እና**</u> (ለ) ለክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) የመጨረሻ ውሳኔ ምክንያት የሆኑት ጉዳዮች መካተት አለባቸው።

ውሳኔው ለአቤቱታ አቅራቢ እና ለሚመለከተው የመንግሥት ኤጀንሲ ይላካል።

**የጊዜ ማራዘሚያ፣ የመጨረሻ ውሳኔ እና ውሳኔውን ስለመፈጸም**

ከዚህም በተጨማሪ ከላይ የተጠቀሰው የክፍለ ግዛቱ የትምህርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት የአቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት ከዚህ የሚከተሉትን ማሟላት አለበት:-

- ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቻ የስልሳ (60) ተከታታይ ቀናቱን የጊዜ ገደብ ማራዘም:-
    - ሀ. በአንድ የክፍለ ግዛት አቤቱታ ረገድ ለየት ያሉ ሁኔታዎች ያጋጠሙ እንደሆነ፤ **<u>ወይም</u>**
    - ለ. በክፍለ ግዛቱ የሚሠራበት ከሆነ፣ እርስዎ እና የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ጉዳዩን በሽምግልና ወይም በአማራጭ የአለመግባባት አፈታት ዘዴ ለመፍታት ተጨማሪ ጊዜ እንዲሰጥ በራሳችሁ ፍላጎት ከተስማማችሁ።
- አስፈላጊ በሚሆን ጊዜ የክፍለ ግዛቱን የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) የመጨረሻ ውሳኔ ለማስፈጸም የሚያስችል አሠራር ማስቀመጥ አለበት፤ ከእነርሱም መካከል:-
    - ሀ. የቴክኒክ ድጋፍ ተግባራት፤
    - ለ. ድርድሮች፤ <u>እና</u>
    - ሐ. የውሳኔውን መከበር ለማረጋገጥ የማስተካከያ እርምጃዎች።

**የክፍለ ግዛት አቤቱታዎች እና የዳኝነት ሥነ-ሥርዓት**

***የዳኝነት አቤቱታ ስለማቅረብ*** በሚለው ርዕስ ሥር እንደተብራራው በጽሁፍ የተዘጋጀ አቤቱታ የቀረበ እንደሆነ እና ይህም አቤቱታ በዳኝነት የሚታይ ከሆነ፣ ወይም አንድ የክፍለ ግዛት አቤቱታ በርካታ ጉዳዮችን ያካተተ ከሆነ እና ከእነርሱም መካከል አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑት በዳኝነት ሊታዩ የሚገባቸው ከሆኑ፣ የክፍለ ግዛቱ የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) የዳኝነት ሂደቱ እስኪጠናቀቅ ድረስ በክፍለ ግዛት አቤቱታ ስር የሚካተተውን ጉዳይ ከክርክሩ ውጪ እንዲሆን ማድረግ አለበት። የዳኝነት ሂደት አካል ያልሆነ ማናቸውም በክፍለ ግዛት አቤቱታው ውስጥ የተካተተ ጉዳይ ደግሞ ከላይ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ እና ሥነ-ሥርዓት መሠረት መፈታት አለበት።

በክፍለ ግዛቱ አቤቱታ ውስጥ የተካተተ ማናቸውም ጉዳይ ከዚህ በፊት እነዚሁ ወገኖች (ለምሳሌ እርስዎ እና የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA)) በተሳተፉበት የዳኝነት ሂደት ውሳኔ የተሰጠበት ከሆነ፣ የዳኝነት ሂደቱ ውሳኔ በዚያ ጉዳይ ላይ አስገዳጅነት

ስለሚኖረው፣ ቀደም ሲል የተሰጠው ውሳኔ አስገዳጅነት እንዳለው የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ለአቤቱታ አቅራቢው ማሳወቅ አለበት።

የአካባቢ የትምሕርት ኤጀንሲ ወይም አንድ የመንግሥት ኤጀንሲ በዳኝነት ሥነ-ሥርዓት የተሰጠን ውሳኔ ለማክበር ፈቃድኛ አይደለም በሚል የሚቀርብ አቤቱታ በክፍለ ግዛቱ የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) መፍትሔ ሊሰጥበት የሚገባው ነው። በተጨማሪም፣ በዳኝነት ሊታይ የነበረው ጉዳይ በጋራ ስምምነት የተፈታ ቢሆንም እንኳን ስምምነቱን ለመተግበር እምቢታኛ መሆንን ተከትሎ የሚቀርብ አቤቱታ ታይቶ በክፍለ ግዛት የአቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት ሊፈታ ይችላል፤ ሆኖም ግን ስምምነትን ተግባራዊ ለማድረግ እምቢተኝነት አለ በሚል የቀረበውን አቤቱታ ለመፍታት የክፍለ ግዛት የአቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት መኖሩ አንዱ ወገን ሥምምነት የተደረሰበትን ጉዳይ በትዕዛዝ ለማስፈጸም ሥልጣን ላለው ፍርድ ቤት አቤቱታ ለማቅረብ ያለውን መብት የሚያስቀር አይደለም።

## የክፍለ ግዛት አቤቱታ ስለማቅረብ

### 34 CFR §300.153 እና የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ይፋዊ የክፍለ ግዛት አቤቱታ ፖሊሲ እና አሠራር

አንድ ድርጅት ወይም ግለሰብ ከላይ በተገለጸው ሥርዓት መሠረት በጽሁፍ የተዘጋጀ እና የተፈረመበት የክፍለ ግዛት አቤቱታ ማቅረብ ይችላል፡-

የክፍለ ግዛቱ አቤቱታ ከዚህ የሚከተሉትን ያካተተ መሆን አለበት፡-

- የአካባቢ የትምሕርት ኤጀንሲ ወይም ሌላ የመንግሥት አካል በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ወይም በማስፈጸሚያ ደንቦቹ CFR ክፍል 300 እና/ወይም ስለልዩ ትምሕርት በዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ ሕግ የተቀመጠን መስፈርት ጥሷል የሚል አቤቱታ፤
- እንዲህ ያለው አቤቱታ የሚመሰረትባቸው ፍሬ ነገሮች ወይም እውነታዎች፤
- አቤቱታውን ያቀረበው ሰው ፊርማ እና አድራሻ፤ <u>እና</u>
- አንድን ልጅ በተመለከተ ጥሰት ተፈጽሟል የሚል አቤቱታ የቀረበ ከሆነ ደግሞ፣ አቤቱታው ከዚህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-
    - ሀ. የሕጻኑ/ኗ ሥም እና የመኖሪያ አድራሻ፤
    - ለ. ሕጻኑ/ኗ የሚማርበት/የምትማርበት ትምሕርት ቤት ሥም፤
    - ሐ. ቤት አልባ ሕጻን ወይም ወጣት በሚሆን/በምትሆን ጊዜ ደግሞ (ማክኪኔ-ቬንቶ የቤት አልባነት ሕግ)፣ ሊገኝ የቻለው የልጁ አድራሻ እና የሚማርበት ትምሕርት ቤት ሥም፤
    - መ. ሕጻኑ/ኗ ያጋጠመው ችግር ዓይነት፣ ከችግሩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች አካትቶ፤ <u>እና</u>
    - ሠ. አቤቱታ አቅራቢው አቤቱታውን ባቀረበበት ጊዜ እስከሚያውቀው እና ሊያገኘው እስከቻለው ድረስ ችግሩን ለመፍታት መወሰድ አለበት የሚለው የውሳኔ ሃሳብ።

***የክፍለ ግዛት አቤቱታ ሥነ-ሥርዓትን ተግባራዊ ስለማድረግ*** በሚለው ርዕስ ሥር እንደተጠቀሰው፣ አቤቱታ አቅራቢው ማቅረብ ያለበት አቤቱታው ከሚቀርብበት ቀን በፊት ከአንድ ዓመት ባልበለጠ ጊዜ የተፈጸመን ጥሰት ጥሰት ነው።

የክፍለ ግዛት አቤቱታ የሚያቀረብ አካል፣ የአቤቱታውን ቅጂ አቤቱታው በክፍለ ግዛቱ የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ባቀረበበት ጊዜ ለሕጻኑ አገልግሎት በመስጠት ላይ ለሚገኘው የአካባቢ የትምሕርት ኤጀንሲ ወይም ሌላ የመንግሥት አካል መላክ አለበት።

# የዳኝነት አቤቱታ አቀራረብ ሥነ-ሥርዓት

## የዳኝነት አቤቱታ ስለማቅረብ

### 34 CFR §300.507

የልጅዎን የትምሕርት ፍላጎት መለየት፣ ምዝና እና ምደባን ከማስጀመር ወይም ከመለወጥ ጋር በተያያዘ በቀረበ ሃሳብ ወይም ጉዳዩ ውድቅ ስለመደረጉ ወይም ነጻ አግባብነት ያለው የሕዝብ ትምሕርት (FAPE) ከመስጠት ጋር በተያያዘ በማናቸውምን ጉዳይ ላይ እርስዎ ወይም የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) የዳኝነት አቤቱታ ማቅረብ ትችላላችሁ።

ያስታውሱ፣ የዳኝነት አቤቱታ መሰማት ዕድል ከማግኘትዎ በፊት፣ እርስዎ እና ትምሕርት ቤቱ/የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) የመፍትሔ ስብሰባ ላማካሄድ ያላችሁን መብት ካልተዋችሁ ወይም ወደ ሽምግልና ለመሄድ ካልወሰናችሁ በስተቀር በአቤቱታው ውስጥ ለተጠቀሱ ጉዳዮች መፍትሔ ለመሻት ከትምሕርት ቤቱ/ከአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ ጋር ውይይት በማድረግ ይጠበቅብዎታል።

በዳኘነት እንዲታይ የሚቀርበው አቤቱታ፣ የዳኝነት ጥያቄ የቀረበበት ተግባር መፈጸሙን እርስዎ ወይም የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ካወቃችሁ ወይም ማወቅ ከሚገባችሁ ጊዜ አንስቶ በሚቆጠር ከሁለት (2) አመት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ የተፈጸመን ጥሰት የያዘ ሊሆን ይገባል።

ከዚህ በሚከተሉት ምክንያቶች የዳኝነት ጥያቄ አቤቱታውን በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ማቅረብ ያልቻሉ እንደሆነ፣ የተቀመጠው የጊዜ ገደብ በእርስዎ ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡-

- የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በአቤቱታው ለተጠቀሱት ጉዳዮች መፍትሄ ሰጥቻለሁ ቢልም ትክክለኛ መፍትሄ ያልሰጠ እንደሆነ፤
- በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍለ ለ ሥር የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ለእርስዎ መስጠት ያለበትን መረጃ የያዘብዎ እንደሆነ።

### *መረጃ ለወላጆች*

ጥያቄ ሲያቀርቡ ወይም እርስዎ ወይም የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) የዳኝነት አቤቱታ የምታቀርቡ ከሆነ፣ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በአካባቢው ያለውን ማንኛውም ነጻ ወይም አነስተኛ ዋጋ የሚያስከፍል የሕግ ወይም አግባብነት ያለውን አገልግሎት ሊያሳውቅዎ ይገባል።

## የዳኝነት አቤቱታ

### 34 CFR §300.508

የዳኝነት አቤቱታ ለማቅረብ እርስዎ ወይም የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) (ወይም የእርስዎ ጠበቃ ወይም የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ጠበቃ) ለሌላው ወገን የዳኝነት አቤቱታ ማቅብ አለባችሁ። እንዲህ ባለው አቤቱታ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን በሙሉ ማካተት አለበት፤ በምስጢር ሊያዝም ይገባል። አቤቱታውን የሚያቀርበው ወገን ከላይ ከተጠቀሰውም በተጨማሪ የአቤቱታውን ቅጂ ለክፍለ ግዛቱ የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ማቅረብ አለበት።

### የአቤቱታው ይዘት

የዳኝነት አቤቱታው ከዚህ የሚከተሉትን ማካተት አለበት፡-

- የሕጻኑ/ኗን ሥም፤
- የሕጻኑ/ኗን የመኖሪያ አድራሻ፤
- የሕጻኑ/ኗን የትምሕርት ቤት ሥም፤
- ቤት አልባ ሕጻን ወይም ወጣት በሚሆን/በምትሆን ጊዜ ደግሞ የሕጻኑ/ኗ መገኛ መረጃ እና የትምሕርት ቤቱ/ቷ ሥም፤
- ከቀረበው ሃሳብ ወይም ውድቅ ከተደረገው ተግባር ጋር በተያያዘ የሕጻኑ/ኗ ችግር፣ ከችግሩ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ፍሬ ነገሮች አካትቶ፤ <u>እና</u>
- አቤቱታ አቅራቢው (እርስዎ ወይም የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA)) አቤቱታውን ባቀረበበት ጊዜ እስከሚያውቀው እና ሊያገኘው እስከቻለው ድረስ ችግሩን ለመፍታት መወሰድ አለበት የሚለው እርምጃ የውሳኔ ሃሳብ።

### ለዳኝነት የቀረበው አቤቱታ ከመሰማቱ በፊት ማስጠንቀቂያ መስጠት አስፈላጊ ስለመሆኑ

እርስዎ ወይም የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) (ወይም የእርስዎ ጠበቃ ወይም የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ጠበቃ) ከላይ የተገለጹትን መረጃዎች የሚያካትት አቤቱታ እስካላቀረባችሁ ድረስ የእርስዎም ሆነ የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) አቤቱታ በዳኝነት አይታይም።

### የአቤቱታ በቂ መሆን

የዳኝነት አቤቱታ ሂደት እንዲጀምር፣ አቤቱታ መቅረቡ በራሱ በቂ ሆኖ ሊታይ ይገባል። የዳኝነት አቤቱታ የደረሰው ወገን (እርስዎ ወይም የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA)) ለዳኝነት <u>ኦፊሰር</u> እና ለሌላው ወገን የቀረበው አቤቱታ ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች አሟልቷል ብሎ እንደማያምን አቤቱታው ከደረሰው ቀን አንስቶ በአስራ አምስት (15) ተከታታይ ቀናት ጊዜ ውስጥ በጽሁፍ ያላሳወቀ እንደሆነ፣ አቤቱታው የተሟላ (ከላይ የተጠቀሱትን መስፈርቶች ያሟላ) ተደርጎ ይቆጠራል።

የዳኝነት ኦፊሰሩ አቤቱታው የደረሰው ወገን አቤቱታው ማሟላት የሚገባውን መስፈርት አላሟላም ብሎ እንደሚያምን የገለጸበት ማሳወቂያ በደረሳቸው በአምስት (5) ተከታታይ ቀናት ጊዜ ውስጥ የቀረበው የዳኝነት አቤቱታ ከላይ የተዘረዘሩትን መስፈርቶች የሚያሟላ ወይም የማያሟላ መሆኑን መወሰን እና ለእርስዎ እና ለአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ ወዲያው በጽሁፍ ማሳወቅ አለባቸው።

**አቤቱታን ስለማሻሻል**

እርስዎ ወይም የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎቸ ብቻ አቤቱታ ማሻሻል ትችላላችሁ፡-

- ሌላው ወገን ለውጦቹን በጽሁፍ የተቀበለ እንደሆነ እና ከዚህ በታች ***አለመግባባትን መፍታት*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተብራራው አለመግባባትን በውይይት በመፍታት ዳኝነት ለተጠየቀበት ጉዳይ መፍትሔ ለማግኘት ዕድል የተሰጠው ከሆነ፤ <u>ወይም</u>
- የዳኝነት ሒደቱ ከመጀመሩ ቢያንስ ቢያንስ ከአምስት (5) ተከታታይ ቀናት በፊት የዳኝነት ኦፊሰሩ ለለውጦቹ ፈቃድ የሰጡ እንደሆነ፤

አቤቱታውን ያቀረበው ወገን (እርስዎ ወይም የአካባቢዎ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA)) በዳኝነት አቤቱታው ላይ ለውጥ ያደረጋችሁ እንደሆነ፣ አለመግባባትን በውይይት ለመፍታት ለመገናኘት ወይም ለስብሰብ የተቀመጠው ጊዜ (አቤቱታው በደረሰ ባሉት አስራ አምስት (15) ቀናት ውስጥ) ወይም ለጉዳዩ መፍትሔ ለመስጠት የተቀመጠው የጊዜ ገደብ (አቤቱታው ከደረሰ ጀምሮ ባሉት ሰላሣ (30) ቀናት ውስጥ) አቤቱታው ከተሻሻለበት ቀን ጀምሮ እንደአዲስ መቆጠር ይጀምራሉ።

**ለቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ምላሽ**

የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ***ቅድመ የጽሁፍ ማስታወቂያ*** በሚለው ንዑስ ርዕስ ሥር እንደተብራራው በአቤቱታው በተጠቀሰው ጉዳይ ላይ ቅድመ የጽሁፍ ማሳወቂያ ያልሰጠዎ እንደሆነ፣ የዳኝነት አቤቱታው ከደረሰው ጀምሮ ባሉት አስር (10) ቀናት ጊዜ ውስጥ ከዚህ የሚከተሉትን የያዘ መልስ መላክ አለበት፡-

- የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በዳኝነት አቤታው ውስጥ የተጠቀሰውን ተግባር በውሳኔ ሃሳብነት ያቀረበበትን ምክንያት ወይም ይህንን ተግባር ከመፈጸም እምቢተኛ የሆነበትን ምክንያት፤
- የግላዊ ትምሕርት ፕሮግራም ቡድን ከግምት ውስጥ ያስገባቸው ሌሎች አማራጮች እና እነዚህ አማራጮች ውድቅ የተደረጉባቸው ምክንያቶች፤
- የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ላቀረበው ሃሳብ ወይም ውድቅ ላደረገው አማራጭ መሠረት የሆነው እያንዳንዱ የምዘና ሂደት፣ ግምገማ፣ ሪከርድ እና ሪፖርት፤ <u>እና</u>
- የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ላቀረበው ሃሳብ ወይም ውድቅ ለማድረግ ምክንያት የሆኑትን ሌሎች ጉዳዮች ሁሉ መዘርዘር አለበት።

ከላይ የተጠቀሱት መረጃዎች በማቅረቡ የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ያቀረቡት የዳኝነት አቤቱታ ማሟላት የሚገባውን አላሟላም የሚል መቃወሚያ ከማቅረብ ሚያግደው አይሆንም።

**ለዳኝነት አቤቱታ በሌላ አካል የሚቀርብ መልስ**

*ለቀረበው የዳኝነት ጥያቄ አካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ምላሽ* በሚለው ክፍል በተጠቀሰው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር፣ የዳኝነት አቤቱታ የደረሰው ወገን ለሌላው ወገን በአስር (10) ተከታታይ ቀናት ጊዜ ውስጥ በአቤቱታው ውስጥ የተጠቀሱትን ጉዳዮች በሚገባ የሚዳስስ መልስ መስጠት አለበት።

## ሞዴል ቅጾች

### 34 CFR §300.509

የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) እርስዎ የዳኝነት እቤቱታ እንዲያቀርቡ እና እርስዎ እና ሌሎች የክፍለ ግዛት አቤቱታዎች የሚያቀርቡ ወገኖችን የሚያግዙ ሞዴል ቅጾች አዘጋጅቷል፤ ሆኖም ግን የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE)ም ሆነ የአካባቢ የትምሕርት ኤጀንሲ እነዚህን ሞዴል ቅጾች እንዲጠቀሙ ማስገደድ አይችሉም። የሚያቀርቡት የክፍለ ግዛት አቤቱታም ሆነ የዳኝነት አቤቱታ የሚፈለጉትን መረጃዎች እስከያዙ ድረስ እነዚህን እና ሌሎች አመቺ ቅጾችን መጠቀም ይችላሉ።

## ሽምግልና

### 34 CFR §300.506

በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ሥር በማናቸውም ጉዳይ ላይ በእርስዎ እና በየአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) መካከል የሚነሱ ማናቸውንም አለመግባባቶች፣ የዳኝነት አቤቱታ ከማቅረብ በፊት የሚነሱ ጉዳዮችን አካትቶ አለመግባባቱን በስምምነት ለመፍታት የሚያስችል የሽምግልና አማራጭ ሊኖር ይገባል። ስለሆነም፣ የዳኝነት አቤቱታ አቀረቡም አላቀረቡም፣ በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ስር የሚከሰቱ አለመግባባቦቶችን ለመፍታት የሽምግልና አማራጭ አለ ማለት ነው።

**መስፈርቶች**

የሽምግልናውን ሂደት አስመልክቶ ሂደቱ ከዚህ የሚከተሉትን አማረጋገጥ አለበት፡-

- በእርስዎም ከሆነ በአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በኩል በነጻ ፍላጎት ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይገባል፤
- የዳኝነት አቤቱታ የማቅረብ መብትዎን ለመከልከል ወይም ለማዘግየት ወይም በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ሥር ያሉዎትን ማናቸውንም መብት ለመከልከል ተብሎ የሚተገበር ሊሆን አይገባም፤ <u>እንዲሁም</u>
- ውጤታማ በሆነ፣ በሽምግልና ቴክኒክ በሰለጠነ ብቃት ባለው እና በገለልተኛ ሽማግሌ ወይም ገላጋይ የሚመራ ሊሆን ይገባል።

የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ወላጆች እና ትምሕርት ቤቶች የሽምግልና አማራጭን መጠቀም በማይፈልጉ ጊዜ፣ ለእርስዎ አመቺ በሆነ ጊዜ እና ቦታ ከገለልተኛ ወገን ጋር ለመገናኘት የምትችሉበትን ሁኔታ ሊያመቻች ይችላል። ገለልተኛው ወገንም፡-

- አለመግባባትን በአማራጭ ዘዴዎች ከሚፈታ ተቋም ጋር ውል ያለው ወይም በዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ የሚገኝ የወላጆች ስልጠና ወይም መረጃ ማዕከል ወይም የማሕበረሰብ የወላጅ አገልግሎቶች ማዕከል ሊሆን፤ <u>እና</u>
- የሽምግልና አማራጭን ጥቅሞች ለእርስዎ የሚያብራራ እና እንዲጠቀሙበትም የሚያበረታታዎ ሊሆን ይገባል።

የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ብቃት ያላቸውን እና የልዩ ትምሕርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ሕግጋትን እና ደንቦችን የሚያውቁ የሽምግልና ግልግል ባለሙያዎች ዝርዝር ይይዛል። የክፍለ ግዛቱ የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) የሽምግልና ግልግል ባለሙያዎችን የተለየ የመምረጫ ሁኔታ በሌለበት፣ በተራ ወይም በሌላ ገለልተኛ በሆነ መንገድ መምረጥ አለበት። የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ለሽምግልናው ሂደት የሚወጣውን ወጪ፣ ወገኖቹ በሚገናኙበት ጊዜ የሚወጣውንም አካትቶ፣ የመሸፈን ኃላፊነት የለበትም። እያንዳንዱ የምትገናኙበት ጊዜ መያዝ ያለበት ለእርስዎ እና ለአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በሚያመች ሁኔታ እና ቦታ መሆን አለበት።

እርስዎ እና የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) አለመግባባቱን በሽምግልና ሒደት መፍታት ከቻላችሁ፣ ሁለቱም ወገኖች መፍትሔውን የሚገልጽ በሕግ አስገዳጅነት የሚኖረው ስምምነት መፈራረም አለባችሁ። ከዚህም ሌላ ስምምነቱ፡

- በሽምግልናው ሒደት የተደረጉ ውይይቶች ሁሉ ሚስጢራዊ ሆነው እንደሚቆዩ እና ከጊዜ በኋላ በማናቸውም የዳኝነት አቤቱታ በሚሰማ ጊዜ ወይም በፍርድ ቤት ክርክር ወቅት በማስጃነት ሊቀርብ እንደማይችል መደንገግ፤ <u>እና</u>
- በስምምነቱ ላይ እርስዎ እና በአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) የፈራሚነት ሥልጣን በተሰጠው ሰው መፈረም አለበት።

በጽሁፍ የተዘጋጀ፣ የተፈረመ የሽምግልና ስምምነት ሥልጣን ባለው በማናቸውም የክፍለ ግዛት ፍርድ ቤት (በክፍለ ግዛቱ ሕግጋት መሠረት እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮችን ለመስማት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት) ወይም በዩናይትድ ስቴትስ ዲስትሪክት ፍርድ ቤት አስገዳጅነት ሊፈጸም የሚችል ነው።

በሽምግልና ሂደት ወቅት የተካሄዱ ውይይቶች ሁሉ በምስጢር መያዝ አለባቸው። ወደፊት በሚካሄድ ማንኛውም የአቤቱታ ዳኝነት ወይም በማናቸውም የፌዴራል ወይም በአካል ጉዳተኞች ትምሕርት ሕግ በክፍል ቢ ሥር ድጋፍ በሚያገኙ ክፍለ ግዛቶች ፍርድ ቤቶች በሚካሄድ ክርክር እንደማስጃ ሊቀርቡ አይችሉም።

**የሽምግልና ግልግል ባለሙያው ገለልተኛነት**

የሽምግልና ግልግል ባለሙያው፡-

- በእርስዎ ልጅ ትምሕርት እና እንክብካቤ ላይ ተሳትፎ ባለው የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ወይም በአካባቢ የትምሕርት ኤጀንሲ የተቀጠረ መሆን የለበትም፤ <u>እንዲሁም</u>
- በተከሰተው አለመግባባት ላይ የሽምግልና ግልግል ዳኛን ምክንያታዊ አቋም ተጽዕኖ ስር በሚከተት መልኩ የሙያ ወይም ግላዊ የጥቅም ግጭት ሌለው ሊሆን ይገባል።

አንድ የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ሠራተኛ ያልሆነ ነገር ግን በሌሎች ጉዳዮች ሁሉ ብቃት ያለው የሽምግልና ዳኛ በሽምግልና ግልግል ለሰጠው አገልግሎት በክፍለ ግዛቱ የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ስለተከፈለው ብቻ የመሥሪያ ቤቱ ሠራተኛ ነው አያስብለውም።

## 34 CFR §300.510 እና 5E DCMR §§3030.5፣ 3030.6፣ 3030.9፣ እና 3030.10

**አለመግባባትን ለመፍታት ስለሚካሄድ ስብሰባ**

የዳኝነት አቤቱታ በደረሰበው በአስራ አምስት (15) ቀናት ጊዜ ውስጥ እና የዳኝነት ሂደቱ ከመጀመሩ በፊት፣ የሚመለከተው የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በእርስዎ እና ስለእርስዎ የአቤቱታ ሂደት የሚያውቀው ግለዊ ትምሕርት ፕሮግራም ቡድን አባል ወይም አባላት መካከል የሚካሄድ ስብሰባ መጥራት አለበት። በዚህ ስብሰባ፦-

- የአካባቢውን የትምሕርት ኤጀንሲ በመወከል ውሳኔ መስጠት የሚችል ኃላፊ መገኘት አለበት፤ <u>እንዲሁም</u>
- እርስዎ ከጠበቃ ጋር አብረው ካልቀረቡ በስተቀር የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በስብሰባው መገኘት የለበትም።

የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በስብሰባው ላይ መገኘት የሚገባቸውን የግላዊ ትምሕርት ፕሮግራም የሚመለከታቸው ቡድኖች ይወስናል። የዚህ ስብሰባ ዓላማ በዳኝነት አቤቱታዎ እና የአቤቱታው መሠረት በሆኑ ፍሬ ነገሮች ላይ ውይይት ለማድረግ እና፣ በዚህም መልኩ የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) አለመግባባቱን ለመፍታት ዕድል እንዲያገኝ ለማስቻል ነው።

ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች አለመግባባትን የመፍታት ስብሰባ አስፈላጊ አይሆንም፦-

- እርስዎ እና የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ስብሰባውን ለማድረግ ያላችሁን መብት ለመተው በጽሁፍ ስትስማሙ፤
- *የሽምግልና* በሚለው ክፍል ስር እንደተገለጸው እርስዎ እና የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) የሽምግልና ሂደትን ለመጠቀም ስትስማሙ።

**የለመግባባትን የመፍቻ ጊዜ**

የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) የዳኝነት አቤቱታ በደረሰው በኃላ ባሉት ሰላሣ (30) ተከታታይ ቀናት ጊዜ ውስጥ (አለመግባባትን የመፍቻ ሂደት ጊዜ) እርስዎ በቂ ነው ብለው በሚወስዱት መልኩ ለዳኝነት አቤቱታው መፍትሔ ያልሰጠ እንደሆነ፣ የዳኝነት አቤቱታ መሰማት ሂደት ሊካሄድ ይችላል።

የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥበት የአርባ አምስት (45) ተከታታይ ቀናት የዳኝነት አቤቱታ ጊዜ መቆጠር የሚጀምረው የሰላሣ (30) ተከታታይ ቀናቱ አለመግባባትን የመፍቻ ጊዜ ከተጠናቀቀበት ቀን ጀምሮ ነው። ሆኖም ግን ከዚህ በታች እንደተገለጸው፣ አለመግባባትን ለመፍታት በተቀመጠው የሰላሣ (30) ተከታታይ ቀናት የጊዜ ገደብ ላይ አንዳንድ ልዩ ሁኔታዎች ተፈጻሚ ሊሆኑ ይችላሉ።

እርስዎ እና የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) አለመግባባትን የመፍታት ሂደትን ለመጠቀም ያላችሁን መብት ለመተው ካልተስማማችሁ በስተቀር፣ እርስዎ አለመግባባትን ለመፍታት በሚካሄድ ስብሰባ ላይ ሳይሳተፉ የቀሩ እንደሆነ፣ የዳኝነት ኦፊሰሩ ስብሰባው እስኪካሄድ ድረስ አለመግባባትን ለመፍታት እና ለዳኝነት አቤቱታ መሰማት የተቀመጠው ጊዜ መቆጠሩ እንዲቋረጥ ትዕዛዝ እንዲሰጡ የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል። እንዲህ ያለው ጥያቄ በሚቀርብ ጊዜ የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ከወላጅ ጋር አለመግባባትን የመፍታት ስብሰባ ለማካሄድ የሚቻለውን ምክንያታዊ ጥረት ሁሉ እንዳደረገ የሚያስረዳ ማስረጃ ማያያዝ አለበት። ምክንያታዊ ጥረት መደረጉ የሚረጋገጥባቸው ሰነዶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል። የዳኝነት ኦፊሰሩ በዚህ ጉዳይ ላይ ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት በጥያቄው እና ተያያዥ ማስረጃዎች ላይ ምላሽዎን የመስጠት ዕድል ይኖርዎታል።

በተጨማሪም፣ የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ምክንያታዊ ጥረቶች ካደረገ እና ጥረትም ማድረጉን የሚያስረዱትለት ሰነዶች ከያዘ በኋላ፣ እርስዎ አለመግባባትን በመፍታት ስብሰባ ላይ ሊገኙለት ካልቻሉ፣ የሰላሣ (30) ተከታታይ ቀናት አለመግባባትን የመፍታት ጊዜ ካለፈ በኋላ የዳኝነት አቤቱታዎን ውድቅ በማድረግ ውሳኔ እንዲሰጡ ለዳኝነት ኦፊሰሩ ጥያቄ ያቀርባል። የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) የጊዜ ገደቦች መቆጠራቸው እንዲዘገይ ትዕዛዝ እንዲሰጥ በሚጠይቅ ጊዜ እንደሚደረገው ሁሉ፣ እርስዎ አለመግባባትን ለመፍታት በሚካሄድ ስብሰባ እንዲሳተፉ ምክንያታዊ ጥረት ሁሉ ማድረጉን የሚያስረዱ ማስረጃዎች ማቅረብ ይጠበቅበታል። ምክንያታዊ ጥረት መደረጉን የሚያስረዱ ሰነዶች ከዚህ በታች ተገልጸዋል። የዳኝነት ኦፊሰሩ በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ከመስጠታቸው በፊት በጥያቄውም ሆነ በማስረጃዎቹ ላይ መልስ እንዲሰጡ ዕድል ይኖርዎታል።

ከላይ የተጠቀሱት ምክንያታዊ ጥረቶች መደረጋቸውን ከሚያስረዱ ሰነዶች መካከል፣ የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ስምምነት በሚደረግበት ጊዜ እና ቦታ ስብሰባ እንዲካሄድ ሙከራ ያደረገ መሆኑን የሚያስረዱ ሰነዶችም ይካተታሉ፤  ለምሳሌ፡

- የተደረጉ ወይም የተሞከሩ የስልክ ጥሪዎች ዝርዝር መረጃዎች እና የእነዚህ የሥልክ ጥሪዎች ውጤቶች፤
- የተላኩ ደብዳቤዎች እና የደረሱ ምላሾች፤ <u>እና</u>
- ወደ እርስዎ ቤት ወይም ወደ ሥራ ቦታዎ የተደረጉ ጉብኝቶች እና እንዲህ ያሉ ጉብኝቶች ውጤቶች።

የእርስዎ የዳኝነት አቤቱታ በደረሰው በአስራ አምስት (15) ተከታታይ ቀናት ጊዜ ውስጥ አለመግባባትን የመፍታት ስብሰባ ለማካሄድ ያልቻለ እንደሆነ <u>ወይም</u> በዚህ ስብሰባ ላይ ሳይገኝ ከቀረ፣ የአርባ አምስት (45) ተከታታይ ቀናቱ የአቤቱታ ዳኝነት የጊዜ ገደብ መቆጠር እንዲጀምር ለዳኝነት ኦፊሰሩ ጥያቄ ማቅረብ ይችላሉ።

**በሰላሣ (30) ተከታታይ ቀናት አለመግባባትን የመፍታት ጊዜ ላይ ስለሚደረግ ለውጥ**

እርስዎ እና የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) አለመግባባትን የመፍታት ስብሰባ ለማካሄድ ያላችሁን መብት ለመተው ስምምነት ካደረጋችሁ፣ በቀጣዩ ቀን የአርባ አምስት (45) ተከታታይ ቀናት የአቤቱታ ዳኝነት የጊዜ ገደብ መቆጠር ይጀምራል። የሽምግልና ግልግል ወይም አለመግባባትን የመፍታት ስብሰባ የሚካሄድበት የጊዜ ገደብ መቆጠር ከጀመረ በኋላ እና የሰላሣ (30) ተከታታይ ቀናት አለመግባባትን የመፍቻ ጊዜ ከማብቃቱ በፊት እርስዎ እና የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ምንም ዓይነት ስምምነት ላይ መድረስ እንደማይቻል ከተስማማችሁ፣ በቀጣዩ ቀን የአርባ አምስት (45) ተከታታይ ቀናት የአቤቱታ ዳኝነት የጊዜ ገደብ መቆጠር ይጀምራል።

እርስዎ እና የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) የሽምግልና ግልግል ሂደትን ለመጠቀም ከተስማማችሁ እና ወደ አንዳች ስምምነት ግን ለመድረስ ያልቻላችሁ እንደሆነ፣ ሁለቱ ወገኖች የጊዜ ገደቡን ለማራዘም በጽሁፍ እስከተመስማማችሁ ድረስ የሰላሣ (30) ተከታታይ ቀናቱ አለመግባባትን የመፍታት ጊዜ በሁለቱም ወገኖች ከስምምነት እስኪደርሱ ጊዜ ድረስ እንዲራዘም ይደረጋል። ሆኖም ግን እርስዎም ሆኑ የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በዚህ የማራዘሚያ ጊዜው ወቅት ከሽምግልናው የወጣችሁ እንደሆነ፣ በቀጣዩ ቀን የአርባ አምስት (45) ቀናቱ የአቤቱታ ዳኝነት የጊዜ ገደብ መቆጠር ይጀምራል።

**በጽሁፍ የሚደረግ የመፍትሔ *ሥምምነት***

አለመግባባትን በመፍታት ስብሰባው ጊዜ በመፍትሔ ላይ ስምምነት ከተደረገ፣ እርስዎ እና የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በሕግ አስገዳጅ ወደ ሆነ ስምምነት መግባት አለባችሁ። ይህም ስምምነት፡-

- በእርስዎ እና የመፈረም ሥልጣን በተሰጠው በአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ኃላፊ መፈረም አለበት፤ <u>እንዲሁም</u>
- በማናቸውም ሥልጣን ባለው የክፍለ ግዛት ፍርድ ቤት (በክፍለ ግዛቱ ሕግጋት መሠረት እንደዚህ ዓይነት ጉዳዮችን ለመስማት ሥልጣን ያለው ፍርድ ቤት) ወይም በዩናይትድ ስቴትስ ዲስትሪክት ፍርድ ቤት አስገዳጅነት ሊፈጸም የሚችል ነው።

***ሥምምነትን* የመከለስ ጊዜ**

እርስዎ እና የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) አለመግባባትን በመፍታት ስብሰባ ምክንያት ከስምምነት ደርሳችሁ ስምምነት ከፈረማችሁ፣ እርስዎም ሆኑ አካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ስምምነቱን ከፈረማችሁበት ጊዜ አንስቶ በሚቆጠር ሦስት (3) የሥራ ቀናት ጊዜ ውስጥ ስምምነቱን መሰረዝ ትችላላችሁ። ይህ በሚሆንበትም ጊዜ፣ ስምምነቱን የሰረዘው ወገን ለሌሎች አካላት ሁሉ በጽሁፍ ይህንኑ ማሳወቅ

## የዳኝነት አቤቱታ መሰማት ሂደት

### ገለልተኛ የዳኝነት አቤቱታ

**34 CFR §300.511**

የዳኝነት አቤቱታ በሚቀርብበት ጊዜ ሁሉ፣ በአለመግባባቱ ውስጥ ያላችሁት እርስዎ እና የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) የገለልተኛ የአቤቱታ ዳኝነት መሰማት ሂደት ዕድል ሊኖራችሁ ይገባል። የክፍለ ግዛቱ የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) የዳኝነት አቤቱታ ሂደትን የማመቻቸት ኃላፊነት አለበት።

**ገለልተኛ የዳኝነት ኦፊሰር**

ቢያንስ ቢያንስ፣ አንድ የዳኝነት ኦፊሰር፡-

- የእርስዎን ልጅ በማስተማር እና በመንከባከብ ላይ ተሳታፊ የሆነው የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ወይም የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ተቀጣሪ መሆን የለባቸውም፤ ሆኖም ግን አንድ የዳኝነት ኦፊሰር በዳኝነት ኦፊሰርነት ለሚሰጡት አገልግሎት በክፍለ ግዛቱ የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ወይም በአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ክፍያ ስለከፈላቸው ብቻ የእነርሱ ተቀጣሪ ሆነው አይቆጠሩም።
- በተከሰተው አለመግባባት ላይ የዳኝነት ኦፊሰርን ምክንያታዊ አቋም ተጽዕኖ ስር በሚከተት መልኩ የሙያ ወይም ግላዊ የጥቅም ግጭት የሌላቸው ሊሆኑ ይገባል።
- የአካል ጉዳተኞችን የትምሕርት ሕግ እና የሕጉ የፌዴራል እና የክፍለ ግዛት ማስፈጸሚያ ደንቦችን ድንጋጌዎች እና እነርሱም በፌዴራል እና በክፍለ ግዛት ፍርድ ቤት ስለሚሰጣቸው የሕግ ትርጓሜ በሚገባ ሚያውቁ እና የሚገነዘቡ፤ <u>እንዲሁም</u>
- ችሎት ስለማስቻል ዕውቀት ያላቸው እና  ማስቻልም የሚችሉ እና በመደበኛው የሕግ አሠራር ደረጃ ውሳኔ መወሰን እና እርሱንም መጻፍ የሚችሉ ሊሆኑ ይገባል።

የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) በዳኝነት ኦፊሰርነት የሚያገለግሉ ሰዎችን ስም ዝርዝር መያዝ እና ከዚህም ጋር የትምሕርት ደረጃቸውን እና የሥራ ልምዳቸውን የሚገልጽ መግለጫ መያዝ አለበት።

### የዳኝነት አቤቱታ ጉዳይ

የዳኝነት አቤቱታ የሚጠይቀው ወገን (እርስዎ ወይም የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA)) ሌላው ወገን ካልተስማማ በቀር በዳኝነት አቤቱታው ውስጥ ያልተጠቀሰን ጉዳይ በዳኝነት ሂደቱ መካከል ማንሳት አይችልም።

### የዳኝነት አቤቱታ መስማት የጊዜ ሰሌዳ

እርስዎ ወይም የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በአቤቱታው ውስጥ የተጠቀሰውን ጉዳይ ካወቃችሁ ወይም ማወቅ ከሚገባችሁ ጊዜ ጀምሮ ባለው የሁለት (2) ዓመት ጊዜ ውስጥ ጉዳዩ በገለልተኛ ዳኝነት ይታይልን ብላችሁ መጠየቅ ይገባችኋል።

### የጊዜ ሰሌዳው ልዩ ሁኔታ

የዳኝነት አቤቱታውን ከዚህ በሚከተሉት ምክንያቶች ማቅረብ ያልቻሉ እንደሆነ፣ ከላይ የተገለጸው የጊዜ ሰሌዳ ተፈጻሚ አይሆንም፡-

- የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ችግሩን ወይም እርስዎ በአቤቱታዎ ላይ የገለጹትን ጉዳይ ሳይፈታ መፍትሔ ሰጥቻለሁ ያለ እንደሆነ፤
- የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በአካል ጉዳተኞች ሕግ በክፍል ቢ ስር የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ሊሰጥዎ ይገባው የነበረን መረጃ ሳይሰጥዎ የቀረ እንደሆነ፤

### ማስረጃ የማቅረብ እና የማስረዳት ሸክም (ከጁላይ 1 ቀን 2016 በኋላ ለሚቀርቡ አቤቱታዎች)

በጠቅላላው፣ አቤቱታውን ያቀረበው ወገን ማስረጃ የማቅረብ እና የማስረዳት ሸክም አለበት። ማስረጃ የማቅረብ ሸክም ማለት ከመነሻው ማስረጃ የማቅረብ እና በአቤቱታው የተገለጸውን ጉዳይ ለማስረዳት በቂ ማስረጃ የማቅረብ ወይም በአቤቱታው የተገለጸውን ችግር በበቂ ሁኔታ ማብራራት ማለት ነው። በዳኝነት አቤቱታዎች፣ ወሳኝ የሚሆነው የቀረበው ማስረጃ የበላይነት ነው። ይህም ማለት የዳኝነት አቤቱታ ያቀረበው ወገን በማስረጃው ክብደት የአቤቱታውን ትክክለኛነት ማስረዳት አለበት ማለት ነው። አቤቱታውን ያቀረበው ወገን የማስረዳት ሸክሙን ይወስዳል በሚለው ጠቅላላ መርሕ ላይ ሁለት ልዩ ሁኔታዎች ተፈጻሚ ይሆናሉ፤ እነርሱም ከዚህ በታች ተገልጸው ይገኛሉ፡-

- የዳኝነት አቤቱታው ዋና ጉዳይ ስለተማሪው ግላዊ የትምሕርት ፕሮግራም (IEP) ወይም የምደባን አግባብነት በማስመልከት ከሆነ፣ አቤቱታውን ያቀረበው ወገን ማስረጃ የማቅረብ ሸክም ይኖርበታል፤ ይህም ማለት፣ አቤቱታ አቅራቢው የተማሪው ግላዊ የትምሕርት ፕሮግራም (IEP) ወይም ምደባ አግባብነት የለውም በሚል መጀመሪያ ማስረጃ የማቅረብ ኃላፊነት አለበት። የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ደግሞ አሁን ያለውን ግላዊ የትምሕርት ፕሮግራም (IEP) ወይም ምደባ አግባብነት ማስረዳት ይኖርበታል።
- ተማሪው በአንድ ወገን ውሳኔ ብቻ ከሕዝብ ትምህርት ቤት ውጪ በሌላ ትምሕርት ቤት የተመደበ በመሆኑ ለዚህ የወጣው ወጪ ይመለስልኝ የሚል ከሆነ፣ ይህ ወገን በራሱ ውሳኔ ተማሪውን በዚህ ትምሕርት ቤት ማስገባቱ ተገቢ ነው በሚል ማስረጃ መቅረብ እና ማስረዳት አለበት። የዳኝነት ኦፊሰሩ በአንዱ ወገን ውሳኔ ተማሪው በአንድ ትምሕርት ቤት እንዲገባ የተደረገበትን ሁኔታ በሁለት በመከፈል ለማየት ሊወስኑ ይችላሉ። የዳኝነት ኦፊሰሩ በአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በራሱ በኩል ብቻ የተወሰነው ምደባ አግባብነት ያለው ነው ብለው ከወሰኑ፣ በዚህ መልኩ የተደረገው ምደባ አግባብ ነው ወይስ አይደለም ወደሚለው ማጣራት መግባት አስፈላጊ አይሆንም።

## የዳኝነት ሂደት መብቶች

### 34 CFR §300.512 እና 5E DCMR §3029.5

በዳኝነት አቤቱታ መስማት ሂደቱ ራስዎን ወክለው መከራከር ይችላሉ። በተጨማሪም፣ በዳኝነት አቤቱታ መስማት ሂደት ተከራካሪ የሆነ ማንኛውም ወገን (የሥነ-ሥርዓት እርምጃን አካትቶ) ከዚህ የሚከተሉት መብቶች ይኖሩታል፡-

- ከጠበቃ እና/ወይም የአካል ጉዳት ያለባቸው ልጆች ስለሚያጋጥሟቸው ችግሮች ልዩ ዕውቀት ወይም ሥልጠና ካለው ሰው ጋር በአንድነት መቅረብ ይችላሉ፤
- በዳኝነት አቤቱታ መስማት ሂደት በጠበቃ መወከል፤
- ማስረጃ ማቅረብ፣ ምስክሮችን ማፋጠጥ፣ ለምስክሮች መስቀለኛ ጥያቄ ማቅረብ እና ምሥክሮች እንዲቀርቡ እንዲታዘዝ መጠየቅ ይችላል፤
- ችሎቱ ከሚካሄድበት ቀን ቢያንስ ከአምስት (5) የሥራ ቀናት በፊት እንዲያውቀው ያልተደረገው ማናቸውም ማስረጃ በችሎቱ እንዳይቀርብ ተቃውሞ የማቅረብ፤
- የችሎቱ ሂደት በጽሁፍ ወይም በእርስዎ ምርጫ በኤሌክትሮኒክ ወይም ቃል በቃል ተመዝግቦ እንዲሰጥዎ መጠየቅ፤
- የፍሬ ነገር ዝርዝር እና ውሳኔ በጽሁፍ ወይም በእርስዎ ምርጫ በኤሌክትሮኒክ ወይም ቃል በቃል ተመዝግቦ እንዲሰጥዎ መጠየቅ፤

### ተጨማሪ መረጃ ስለመስጠት

የዳኝነት አቤቱታው ከሚሰማበት ቀን ቢያንስ ከአምስት (5) የሥራ ቀናት ቀደም ብሎ፣ እርስዎ እና የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) እስከ እዚያ ቀን ድረስ የተጠናቀቁ ምዘናዎችን እና እርስዎ እና የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በአቤቱታው መሰማት ሂደት ወቅት ልትጠቀሙባቸው የምትፈልጓቸውን በእነዚህ ምዘናዎች ላይ ተመስርተው የተሰጡ የውሳኔ ሃሳቦች አንዳችሁ ለሌላው መግለጽ አለባችሁ።

ይህንን መስፈርት የማያሟላ ማንኛውም ወገን ሌላው ወገን ሳይፈቅድለት በዳኝነት መሰማት ሂደቱ ውስጥ አንድን አግባብነት ያለውን ምዘና እና የውሳኔ ሃሳብ እንዳያቀርብ የዳኝነት ኦፊሰሩ ክልከላ ሊጥሉበት ይችላሉ።

ከዚህም በተጨማሪ፣ በችሎቱ ላይ በጠበቃ የሚወከሉ ከሆነ፣ ጠበቃው በዚህ ሂደት ውስጥ ተሳትፎ ያለው እና ክርክሩ የሚመለከተው የመንግሥት አካል ያልሆነ አገልግሎት ሰጪ የገንዘብ ጥቅም ያለው መሆኑን የሚያውቅ/የምታውቅ ከሆነ፣ ይህንኑ መግለጽ ይገባዋል/ይገባታል።

### በዳኝነት ሂደት ውስጥ የወላጅ መብቶች

ከዚህ የሚከተሉት መብቶች ሊኖሩዎ ይገባል፡-

- ልጅዎ እንዲቀርብ የማድረግ፤
- ችሎቱ ክፍት እንዲሆን የማድረግ፤ <u>እና</u>
- የችሎቱን፣ የግኝቶቹን እና የውሳኔዎቹን ሪከርድ ያለወጪ የማግኘት።

## የዳኝነት ውሳኔዎች

### 34 CFR §300.513

### የዳኝነት ኦፊሰሩ ውሳኔ

የዳኝነት ኦፊሰሩ የእርስዎ ልጅ ነጻ አግባብነት ያለው የሕዝብ ትምሕርት (FAPE) አግኝቷል በሚለው ጉዳይ ላይ ውሳኔ መስጠት ያለባቸው ከነጻ እና አግባብነት ያለው የሕዝብ ትምሕርት ጋር ተያያዥነት ባላቸው ማስረጃዎች እና ክርክሮች ላይ በመመስረት ነው።

የአካሄድ ጥሰት ተፈጽሟል በሚል ለሚቀርቡ አቤቱታዎች (ለምሳሌ "ያልተሟላ የግላዊ ትምሕርት ፕሮግራም ቡድን")፣ የአካሄድ ጥሰቱ ከዚህ በሚከተለው አኳኋን ከሆነ፣ የዳኝነት ኦፊሰሩ ልጅዎ ነጻ አግባብነት ያለው የሕዝብ ትምሕርት (FAPE) አላገኘም ብለው ሊወስኑ ይችላሉ፡-

- ልጅዎ ነጻ አግባብነት ያለው የሕዝብ ትምሕርት (FAPE) ለማግበት ባለው/ባለት መብት ለይ ጣልቃ የገባ እንደሆነ፤
- ለልጅዎ ነጻ አግባብነት ያለው የሕዝብ ትምሕርት (FAPE) በመሰጠቱ ጉዳይ ላይ ውሳኔ በመስጠቱ ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ ባለዎት ዕድል ላይ ከፍተኛ ጣልቃ ገብነት ካስከተለ፤
- ልጅዎ የትምሕርት ጥቅም እንዳያገኝ/እንዳታገኝ ያደርገ እንደሆነ።

ከላይ የተገለጹት ማናቸውም ድንጋጌዎች ቢሆኑ፣ የዳኝነት ኦፊሰሩ በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ስር በፌዴራል ደንቦች ፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ በሚለው ስር ያሉትን መስፈርቶች የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) እንዲያከብር ትዕዛዝ ከመስጠት አያግዳቸውም (34 CFR §§300.500 እስከ 300.536)።

### ራሱን የቻለ የዳኝነት አቤቱታ ስለማቅረብ

በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ሥር በፌዴራል ደንቦች ስለፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ በሚደነግገው ክፍል (34 CFR §§300.500 እስከ 300.536) የተጻፈ ማናቸውም ቢሆን ባቀረቡት የዳኝነት አቤቱታ ውስጥ ባልተካተተ ራሱን የቻለ ጉዳይ ላይ የተለየ የዳኝነት አቤቱታ ማቅረብን እንደሚከለክል ድንጋጌ ተደርጎ ሊተረጎም አይችልም።

### ለአማካሪ ጉባዔ እና ለሕዝብ ስለሚገለጹ ግንኝቶች እና ውሳኔዎች

የክልሉ የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ማናቸውንም ግላዊ ማንነትን የሚገለጹ መረጃዎችን ካስወገደ በኋላ፡

- የዳኝነት አቤቱታ መሰማት ሂደቱን ግኝቶች እና ውሳኔዎቹን ለክልሉ ልዩ የትምሕርት አማካሪ ጉባዔ ማቅረብ አለበት፤ <u>እንዲሁም</u>
- እነዚህን ግኝቶች እና ውሳኔዎች በሕዝብ እንዲታወቅ ማድረግ አለበት።

## የውሳኔ መጨረሻ መሆን፤ ይግባኝ

### 34 CFR §300.514

በዳኝነት አቤቱታ መስማት ሂደት የተሰጠ ውሳኔ (የሥነ-ሥርዓት ማስጠበቅ ሂደቶችን አካትቶ) የሚሰጥ ውሳኔ የመጨረሻ ሲሆን፣ በሂደቱ ተሳታፊ የነበረ ተከራካሪ ወገን (እርስዎ ወይም የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA)) ከዚህ በሚከተለው አኳኋን በፍርድ ቤት የፍትሐ ብሔር የይግባኝ አቤቱታ ሊያቀርብ ይችላል።

## የዳኝነት ሂደት የጊዜ ሰሌዳ እና የችሎቱ አሰያየም

### 34 CFR §300.515 እና 5E DCMR §§3030.11 እና 3030.12

የክፍለ ግዛቱ የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) አለመግባባትን የመፍታት የሰላሣ (30) ተከታታይ ቀናት ካበቃ በኋላ ከአርባ አምስት (45) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ <u>ወይም</u> ***በሰላሣ (30) ተከታታይ ቀናት አለመግባባትን የመፍታት ጊዜ ላይ ስለሚደረግ ለውጥ*** በሚለው ክፍል ስር እንደተገለጸው የተሻሻለው የጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀ በኋላ ከአርባ አምስት (45) ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፡-

- በዳኝነት ሂደት የመጨረሻ ውሳኔ መስጠቱን፤ <u>እና</u>
- የውሳኔው ቅጂ ለእያንዳንዱ ተዋዋይ ወገን መድረሱን ወይም በአማራጭነት በኤሌክትሮኒክ ዘዴ ወይም የሚመለከተው አካል ከተስማማ በፋሲሜል አማካኝነት በዳኝነት አቤቱታ መስማት ሂደቱ ውስጥ ተሳታፊ ለሆኑ አካላት ሁሉ መላኩን ማረጋገጥ አለበት።

የዳኝነት ኦፊሰሩ በቂ ምክንያት መኖሩን በማሳየት ከተከራካሪ ወገኖች መካከል በአንዱ በሚቀርብ ጥያቄ መሠረት ከላይ የተገለጸውን የአርባ አምስት (45) ተከታታይ ቀናቱን የጊዜ ገደብ ሊያራዝሙ ይችላሉ።

እያንዳንዱ የዳኝነት መስማት ጊዜ መካሄድ ያለበት ለእርስዎ እና ለልጅዎ አመቺ በሆነ ጊዜ እና ቦታ ነው።

## የፍትሐ ብሔር ክስ እና ክሱ የሚመሰረትበት የጊዜ ገደብ

### 34 CFR §300.516

በዳኝነት አቤቱታው ጊዜ በነበረው ግኝት እና በውሳኔው (የሥነ-ሥርዓት ማስጠበቂያ አካሄድንም ጨምሮ) ያልተስማማ ማንኛውም ወገን (እርስዎ ወይም የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA)) የዳኝነት አቤቱታ በቀረበበት ጉዳይ ላይ የፍትሐ ብሔር ክስ መመስረት ይችላል። ክርክሩ የያዘው የገንዘብ መጠን ከግምት ውስጥ ሳይገባ፣ ክሱ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ላዕላይ ፍርድ ቤት (ወይም በማናቸውም እንደዚህ ዓይነት ክስ የመስማት ሥልጣን ባለው የክፍለ ግዛት ፍርድ ቤት) ወይም በዩናይትድ ስቴትስ ዲስትሪክት ፍርድ ቤት ሊቀርብ ይችላል።

#### የይርጋ ጊዜ

ክሱን የሚመሰርተው ወገን (እርስዎ ወይም አካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA)) የፍትሐ ብሔሩን ክስ ለመመስረት የዳኝነት ኦፊሰር ውሳኔ ከሰጡበት ቀን አንስቶ የሚቆጠር የ90 ተከታታይ ቀናት ጊዜ አለው።

#### ተጨማሪ የሥነ-ሥርዓት አካሄድ

በማናቸውም የፍትሐ ብሔር ክስ፣ ፍርድ ቤቱ፡-

- የአስተዳደር ሂደቶች ሪከርዶች እንዲቀርቡለት ያደርጋል፤
- በእርስዎ ወይም በአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ጥያቄ ተጨማሪ ማስረጃዎችን ይሰማል፤
- በይበልጥ ሚዛን በሚደፋው ማስረጃ ላይ በመመስረት ውሳኔውን የሚሰጥ ሲሆን፣ አግባብነት አለው ብሎ የሚያምንበትን የዳኝነት ውሳኔ ይሰጣል።

አግባብነት ባላቸው ሁኔታዎች፣ በፍርድ ቤት የሚሰጥ ውሳኔ ለግል ትምሕርት ቤት የተከፈለ ክፍያ እንዲካስ ማድረግ እና ማካካሻ የትምሕርት አገልግሎቶች እንዲሰጡ ማድረግን ሊያካትት ይችላል።

#### የዲስትሪክት ፍርድ ቤቶች ሥልጣን

የዩናይትድ ስቴትስ ዲስትሪክት ፍርድ ቤቶች በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ስር ክ ሲቀርብላቸው፣ ክሱ የያዘው የገንዘብ መጠን ከግምት ወስጥ ሳይገባ በክሱ ላይ ውሳኔ የመስጠት ሥልጣን አላቸው።

### የሕግ አተረጓጎም

በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ የተጻፈ ማናቸውም ቢሆን፣ በዩናይትድ ስቴትስ ሕገ-መንግሥት፣ በ1990 በወጣው አሜሪካንስ ዊዝ ዲዝአቢሊቲስ ሕግ፣ በ1973 በወጣው ሪሐቢሊቴሽን ሕግ በክፍል V (ክፍል 504) ወይም የአካል ጉዳተኛ ሕጻናትን መብቶች ለማስጠበቅ በወጡ የፌዴራል ሕጎጋት ሥር ያሉ መብቶችን፣ አካሄድን እና መፍትሔዎችን ከመጠቀም የሚያግድ ወይም የሚገድብ አይሆን፤ ሆኖም ግን በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ስር የዳኝነት ውሳኔ ሊሰጥበት በሚችል ጉዳይ ላይ የፍትሐ ብሔር ክስ ከመመስረት በፊት፣ በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ መፍትሔ ሊገኝ እስከሚችልበት መጠን ከላይ የተለገጹት የዳኝነት አቤቱታ ሂደቶች ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ መደረግ አለባቸው። ይህም ማለት በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) ስር በሌሎች ሕጎች ከተጻፉ መፍትሔዎች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ውሳኔዎች ሊሰጡ ይችላሉ፤ ሆኖም ግን በጠቅላላው በሌሎች ሕጎች ሥር የዳኝነት መፍትሔ ለማግኘት በቀጥታ ወደ ፍርድ ቤት ከማምራትዎ በፊት በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) ስር ያሉ የአስተዳደር አማራጮችን (ማለትም የዳኝነት አቤቱታ፤ አለመግባባትን የመፍታት ሒደት፣ አለመግባባትን የመፍታት ስብሰባ ማካሄድ፣ እና የገለልተኛ ዳኝነት አቤቱታ ሂደቶች) መጠቀም ይገባዎታል።

## የዳኝነት አቤቱታ እና የአቤቱታ መስማት ሂደት በመካሄድ ላይ ሳለ የልጅዎ ምደባ

### 34 CFR §300.518

*የአካል ጉዳተኛ ሕጻናት የሥነ-ሥርዓት ማስጠበቅ አካሄድ* በሚለው ክፍል በተጻፈው መሠረት ካልተፈቀደ በቀር፣ የዳኝነት ቤቱታ ለሌላው ወገን ከተላከ፣ አለመግባባትን በመፍታት የጊዜ ገደብ ውስጥ እና በማናቸውም የገለልተኛ ዳኝነት ሂደት ወይም በፍትሐ ብሔር ክስ ውሳኔ በመጠበቅ ላይ ሳሉ፣ እርስዎ እና የክፍለ ግዛቱ የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ወይም የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በሌላ መልኩ ካልተስማማችሁ በስተቀር፣ ልጅዎ አሁን የሚገኝበት/በምትገኝበት የትምሕርት ምደባ መቆየት አለበት/አለባት።

የዳኝነት አቤቱታው ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ሕዝብ ትምሕርት ቤት የመግቢያ ማመልከቻን የሚያካትት ከሆነ፣ ልጅዎ በእርስዎ ፈቃድ እንደዚህ ያሉት ሂደቶች በሙሉ እስኪጠናቀቁ ድረስ በመደበኛ የሕዝብ ትምሕርት ቤት ፕሮግራም ውስጥ መመደብ አለበት/አለባት።

የቀረበው የዳኝነት አቤቱታ፣ በ IDEA ክፍል ሲ ወደ IDEA ክፍል ቢ በመሸጋገር ላይ ላለ/ች ልጅ፣ በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ መሠረት የመጀመሪያ አገልግሎቶች ማመልከቻን የሚያካትት ከሆነ እና ልጅዎ የሦስት ዓመት ዕድሜ የሞላው/የሞላት በመሆኑ በክፍል ሲ ስር አገልግሎቶች ለማግኝ ብቁ ካልሆነ/ች፣የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ሕጻኑ/ኗ በማግኘት ላይ የነበረውን/የነበረችውን በክፍል ሲ ስር የሚሰጡ አገልግሎቶች ለመስጠት አይገደድም። ልጅዎ በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ስር አገልግሎቶች ለማግበት ብቁ ነው/ናት ከተባለ እና ልጅዎ ለመጀመሪያ ጊዜ ልዩ ትምሕርት እና ተያያዥ አገልግሎቶችን እንዲያገኝ/እንድታገኝ ፈቃድዎን ከፈለጹ፣ በመካሄድ ላይ ያሉት ሂደቶች እስኪጠናቀቁ ድረስ፣ የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ክርክር ያልተነሳባቸውን የልዩ ትምሕርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች (እርስዎ እና LEA በጋራ የምትስማሙባቸውን አገልግሎቶች) መስጠቱን መቀጠል አለበት።

የዳኝነት አቤቱታው በ( OSSE) የሚካሄደው ዳኛ ውሳኔ ከእርስዎ ጋር ከተስማማ የምደባው መቀየር ተገቢ ነው ሲል፥ ይህ ምደባ የልጅዎ ምደባ ሆኖ ለጊዜው መቆጠር ይኖርበታል፤ ልጅዎ የገለልተኛ ዳኝነት ሂደት ወይም በፍትሐ ብሔር ክስ ውሳኔ እስከሚያገኝ ድረስ።

## ለጠበቃ እና ለሙያተኛ ምሥክሮች ስለሚከፈል ክፍያ

### 34 CFR §300.517 እና 5E DCMR §3032.4፤ የዲ.ሲ. ኦፊሺያል ኮድ §38-2571.03(7)(A)

### የጠበቃ ክፍያ

በማናቸውም በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ስር ለቀረበ ክስ ወይም የአቤቱታ መስማት ሂደት፣ እርስዎ የክርክሩ አሸናፊ ከሆኑ፣ ያወጧቸው ወጪዎች እንዲመለሱልዎ ትዕዛዝ በሚሰጥ ጊዜ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው እንደሚለው ምክንያታዊ የሆነ የጠበቃ ክፍያ ሊወስንልዎም ይችላል።

በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ስር ለቀረበ ማናቸውም ክስ፣ የእርስዎ ጠበቃ ከዚህ የሚከተሉትን የፈጸመ እንደሆነ፣ ክርክሩን ላሸነፈው የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ወይም ሌላ የመንግሥት ኤጀንሲ የሚተካውን የወጪ ዝርዝር ትዕዛዝ በሚሰጠበት ጊዜ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው እንደሚለው የእርስዎ ጠበቃ ለኤጀንሲው የሚከፍለውን ምክንያታዊ የጥብቅና ክፍያ አብሮ ሊወስን ይችላል፡-

- የእርስዎ ጠበቃ ያቀረበው አቤቱታ ወይም ክስ ቁም ነገር የሌለው፣ ምንያታዊ ያልሆነ ወይም መሠረት የሌለው ነው ብሎ ፍርድ ቤቱ ከወሰነ፤ ወይም
- ክርክሩ ቁም ነገር የሌለው፣ ምክንያታዊ ያልሆነ ወይም መሠረት የሌለው መሆኑ በግልጽ እየታየ እንኳን የእርስዎ ጠበቃ በክርክሩ ከቀጠለ፤ ወይም
- በማናቸውም የአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ መሠረት በቀረበ ክስ ወይም የዳኝነት አቤቱታ፣ የዳኝነት አቤቱታውን ወይም ከዚያ በኋላ ደግሞ የፍርድ ቤት ክስ ያቀረቡት ለማናቸውም አግባብነት ለሌለው ዓላማ፣ ለምሳሌ

አላስፈላጊ ጫና ለመፍጠር፣ አላፈላጊ መዘግየትን ለመፍጠር ወይም የክሱን ወይም የአቤቱታ መሰማቱን ሂደት (ችሎት) ወጪ ከፍ ለማድረግ በሚሆንበት ጊዜ፣ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው እንደሚለው እርስዎ ወይም የእርስዎ ጠበቃ በክርክሩ አሸናፊ ለሆነው የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ወይም የመንግሥት ኤጀንሲ የምትከፍሉትን የጠበቃ ክፍያ ሊወስንባችሁ ይችላል።

***የሙያተኛ ምስክር ክፍያ***

በማናቸውም በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ስር ከጁላይ 1 ቀን 2016 ዓ.ም. በኋላ ለሚመሰረት ክስ ወይም የአቤቱታ መሰማት ሂደት፣ እርስዎ የክርክሩ አሸናፊ ሆነው ከተገኙ፣ ፍርድ ቤቱ ተገቢ ነው ብሎ እንደሚወስነው ከሚተኩልዎ ወጪዎች ጋር በአንድነት ምክንያታዊ የሙያተኛ ምሥክር ክፍያ ሊወስንልዎ ይችላል።

በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ስር የእርስዎ ጠበቃ ቁም ነገር የሌለው፣ ምክንያታዊ ያልሆነ ወይም መሠረት የሌለው የዳኝነት አቤቱታ እና ከዚያ በኋላ ደግሞ ክስ አቅርቦ የነበረ ከሆነ፣ ፍርድ ቤቱ በራሱ ውሳኔ በክርክሩ አሸናፊ ለሆነው የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ወይም የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) የእርስዎ ጠበቃ የሚከፍለውን ምክንያታዊ የሆነ የጠበቃ ክፍያ ሊወስን ይችላል፤ ይህም ውሳኔ ለአሸናፊው ወገን የሚተካለት ወጪ አካል ይሆናል።

በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ስር ክስ ያቀረቡት ለማናቸውም አግባብነት ለሌለው ዓላማ፣ ለምሳሌ አላስፈላጊ ጫና ለመፍጠር፣ አላፈላጊ መዘግየትን ለመፍጠር ወይም የክሱን ወይም የአቤቱታ መሰማቱን ሂደት (ችሎት) ወጪ ከፍ ለማድረግ በሚሆንበት ጊዜ፣ ፍርድ ቤቱ በራሱ ውሳኔ በክርክሩ አሸናፊ ለሆነው የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ወይም የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) እርስዎ ወይም የእርስዎ ጠበቃ የምትከፍሉትን ምክንያታዊ የሆነ የጠበቃ ክፍያ ሊወስንባችሁ ይችላል፤ ይህም ውሳኔ ለአሸናፊው ወገን የሚተካለት ወጪ አካል ይሆናል።

***የጠበቃ እና የሙያተኛ ምሥክር ክፍያ***

ፍርድ ቤቱ ከዚህ በሚከተለው መልኩ የጠበቃ እና/ወይም የሙያተኛ ክፍያን ይወስናል፡-

- የክፍያዎች መጠን ክሱ ወይም የአቤቱታ መሰማቱ ሂደት በተመሰረበት ማሕበረሰብ ውስጥ በተለመደው ዋጋ እና በአገልግሎቱ ዓይነት እና ጥራት መሠረት ሊወሰኑ ይገባል ነው።
- የሙያተኛ ምሥክር ክፍያ በእያንዳንዱ ክስ ወይም የዳኝነት አቤቱታ ከ$6,000 በላይ ሊሆን አይችልም።
- ለገለልተኛ የትምሕርት ምዘና፣ የሚመለከተው ወገን በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) ስር ለሚያካሂደው ምዘና ማካካሻ ክፍያ የማግኘት መብት ያለው ካልሆነ በቀር (ለተጨማሪ መረጃ ***ገለልተኛ ትምሕርታዊ ግምገማዎች*** የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ)፣ ለተንቀሳቃሽ ወገን የሙያተኛ ምሥክር ክፍያ ሊወሰን አይገባም።
- በጽሁፍ የተዘጋጀ የክፍያ ሃሳብ ለእርስዎ ከቀረበልዎ በኋላ በማናቸውም ክስ ወይም የዳኝነት አቤቱታ ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች የክፍያ ውሳኔ ወይም የወጪ መተካት ትዕዛዝ አይሰጥም፡-

  ሀ. የክፍያው ሃሳብ የቀረበው በፌዴራል የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕግ፣ በደንብ 68 በተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከሆነ ወይም ጉዳዩ የዳኝነት አቤቱታ በሚሆን ጊዜ ደግሞ፣ የአቤቱታ መሰማት ሂደት ከመጀመሩ በፊት ከአስር (10) ተከታታይ ቀናት በላይ ሲቀረው በማናቸውም ጊዜ የቀረበልዎት እንደሆነ፤

  ለ. የቀረበው ሃሳብ በአስር (10) ተከታታይ ቀናት ጊዜ ውስጥ ተቀባይነት ያላገኘ እንደሆነ፤ <u>እና</u>

  ሐ. እርስዎ መጨረሻ ላይ የሚያገኙት የዳኝነት ውሳኔ ከቀረበልዎ የክፍያ ሃሳብ በላይ ሊሆን አይችልም በማለት ፍርድ ቤቱ ወይም የአስተዳደር አካሉ የወሰነ እንደሆነ።

  እነዚህ ገደቦች እንደተጠበቁ ሆነው፣ በክርክሩ አሸናፊ ከሆኑ እና ከዚህ ቀደም የቀረበልዎትን ሃሳብ አለመቀበልዎ አግባብ እንደነበረ በሚገባ ከተረጋገጠ፣ የጠበቃ ክፍያ እና ተያያዥ ወጪዎች እና/ወይም የሙያ ምሥክሮች ክፍያዎች እንዲከፈልዎ ሊወሰን ይችላል።

- ከግላዊ የትምሕርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ጋር ለተካሄደ ማናቸውም ስብሰባ፣ ስብሰባው የተካሄደው በአስተዳደር የአቤቱታ መሰማት ሂደት ወይም በፍርድ ቤት በተመሠረተ ክስ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር ክፍያዎች እንዲከፈሉ ውሳኔ አይሰጥም።

***አለመግባባትን የመፍታት ሂደት*** በሚለው ርዕስ ስር እንደተብራራው፣ ክፍያን በሚመለከት ከላይ ለተጻፉት ድንጋጌዎች አፈጻጸም፣ አለመግባባትን ለመፍታት የሚካሄድ ስብሰባ በአስተዳደራዊ አግባብ ለዳኝነት አቤቱታ ወይም በፍርድ ቤት ለሚመሰረት ክስ ሲባል የተካሄደ ስብሰባ ተደርጎ አይቆጠርም፤ ራሱም ቢሆን አስተዳደራዊ የዳኝነት አቤቱታ ወይም የፍርድ ቤት ክስ ሂደት ተደርጎ አይወሰድም።

ፍርድ ቤቱ ከዚህ የሚከተሉትን ሲያረጋግጥ፣ በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ስር የሚወስነውን የጠበቃ ክፍያ እና/ወይም የሙያተኛ ምሥክር ክፍያ እንደአግባብነቱ መጠኑ እንዲቀንስ ሊያደርግ ይችላል፡-

- እርስዎ ወይም ጠበቃዎ የክሱ ክርክር ወይም የዳኝነት አቤቱታው መሰማት በመካሄድ ላይ ባለበት ጊዜ፣ አለመግባባቱ ለመጨረሻ መፍትሄ የማግኘቱን ነገር ምክንያታዊ ባልሆነ ሁኔታ ያዘገያችሁ እንደሆነ፤

- በሌላ መልኩ የክፍያው መጠን በማሕበረሰቡ ተመሳሳይ ክህሎት፣ ዝና እና ልምድ ኖሯቸው ተመሳሳይ አገልግሎት ለሚሰጡ ጠበቆች ወይም የሙያ ምሥክሮች ከሚከፈለው የሰዓት ክፍያ ምክንያታዊነት በጎደለው ሁኔታ ከፍተኛ ጭማሪ የታየበት እንደሆነ፤
- የክሱን እና የክሱን ሂደት ባሕርይ ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ የተሰጠው አገልግሎት እና ይህም የወሰደው ጊዜ ከሚገባው በላይ ሆኖ ከተገኘ፤ <u>ወይም</u>
- እርስዎን የሚወክለው ጠበቃ *የዳኝነት አቤቱታ መሰማት* በሚለው ርዕስ ስር እንደተገለጸው የዳኝነት አቤቱታ ማሳወቂያው ወይም ማስጠንቀቂያው ውስጥ ለአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) አግባብነት ያለውን መረጃ ሳይሰጥ የቀረ እንደሆነ።

ሆኖም ግን የክፍለ ግዛት የትምሕርት ኃላፊ መሥሪያ ቤት (OSSE) ወይም የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ምክንያታዊነት በጐደለው ሁኔታ የክሱን ወይም የአቤቱታ መሰማቱን ሂደት አጓቷል ወይም በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) በክፍል ቢ ስር የፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ድንጋጌዎችን ጥሷል በማለት ፍርድ ቤቱ የወሰነ እንደሆነ፣ የክፍያውን መጠን አይቀንስም።

እርስዎ በክርክሩ በአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ላይ አሸናፊነትን ከተቀዳጁ፣ የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) እርስዎ የፈጸሙትን የጠበቃ ክፍያ ተመላሽ እንዲያደርግልዎ የሚያቀርቡት ጥያቄ ሁሉ በችሎቱ ውሳኔ በተሰጠ ወይም እንዲህ ያለውን ክፍያ ለመክፈል ስምምነት በተደረገ በአርባ አምስት (45) ቀናት ጊዜ ውስጥ መቅረብ አለበት። ይህንን ሳያደርጉ የቀሩ እንደሆነ፣ የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) የክፍያውን ሂደት ሲያከናውን ጊዜው ሊራዘም ይችላል።

## የአካል ጉዳት ላለባቸው ልጆች *ሥነ-ሥርዓት* ለማስጠበቅ *ሥራ* ላይ የሚውል አካሄድ

**[ማስታወሻ፡- የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምሕርት ቤቶች (DCPS) የአካል ጉዳት ላለባቸው ልጆች *ሥነ-ሥርዓት* ማስጠበቂያ የተለዩ ሂደቶችን ተግባራዊ አድርጓል። ልጅዎ በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምሕርት ቤቶች (DCPS) ወይም ዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምሕርት ቤቶች (DCPS) የእርሱ አስፈጻሚ እንደሆን በመረጠው የሕዝብ ቻርተር ትምሕርት ቤት ውስጥ በመማር ላይ ከሆነ/ች፣ በአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) እንደተደነገገው፣ *ሥነ-ሥርዓት* ማስጠበቅን በተመለከተ የዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ የሕዝብ ትምሕርት ቤቶች (DCPS) ፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ቅጂ ሊደርስዎ ይገባል።]**

### የትምሕርት ቤት ሠራተኞች ሥልጣን

**34 CFR §300.530**

#### እያንዳንዱን ጉዳይ በማየት ስለመወሰን

አንድ/አንዲት የአካል ጉዳት ያለበት/ያለባት ልጅ፣ የትምሕርት ቤቱን የተማሪዎች *ሥነ-ሥርዓት* ደንብ የጣሰ/ች እንደሆነ፣ *ሥነ-ሥርዓት* ለማስጠበቅ በተቀመጡት መስፈርቶች መሠረት የተማሪውን/ዋን ምደባ መቀየር አግባብነት ያለው ስለመሆኑ ለመወሰን የትምሕርት ቤቱ ሠራተኞች እያንዳንዱን የሥነ-ሥርዓት ጥሰት በየራሱ በማየት ውሳኔ ሊሰጡ ይችላሉ።

#### ጠቅላላ

የአካል ጉዳት በሌለባቸውም ልጆች ላይ የሚወስዱት ዕርምጃ እስከሆነ ድረስ፣ የትምሕርት ቤት ሠራተኞች የሥነ-ሥርዓት ደንብን የጣሰ አንድ ተማሪ በወቅቱ ከተመደበበት/ከተመደበችበት ተቋም (ሴቲንግ) ከ**አስር (10) ተከታታይ የትምሕርት ቀናት** ላልበለጠ ጊዜ ወደ ሌላ ጊዜያዊ አማራጭ የትምሕርት ሴቲንግ ሊያዘዋውሩ፣ ሊቀይሩ ወይም ሊያግዱ ይችላሉ። በዚያው የትምሕርት ዘመን ሌሎች የሥነ-ሥርዓት ጥሰቶች በሚፈጸሙበት ጊዜ፣ የትምሕርት ቤቱ ሠራተኞች ከአስር (10) ተከታታይ ትምሕርት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ተመሳሳይ እርምጃ ሊወስዱ ይችላሉ። ይህ ዘዴ ተፈጻሚነት የሚኖረው ተማሪው/ዋ ከመደበኛው የትምሕርት ሴቲንግ የምደባ ለውጥ እስካላስከተለ ድረስ ነው (***በሥነ-ሥርዓት እርምጃ ምክንያት ስለሚሆን የምደባ ለውጥ*** በሚለው ርዕስ ስር ትርጓሜውን ይመልከቱ)።

አንድ የአካል ጉዳት ያለበት/ባት ልጅ በአንድ የትምሕርት ዘመን ከወቅታዊው ምደባው በድምሩ **ለአስር (10) የትምሕርት ቀናት** እንዲለይ በሚረግበት ጊዜ፣ የአካባቢው የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA)፣ በማናቸውም በዚያው የትምሕርት ዓመት በሚወሰድ ተመሳሳይ እርምጃ ወቅት፣ ከዚህ በማስከተል ***አገልግሎቶች*** በሚለው ርዕስ ስር የተጠቀሱትን አገልግሎቶች መስጠት አለበት።

#### ተጨማሪ ሥልጣን

የተማሪዎችን የሥነ-ሥርዓት ደንብ የጣሰው ባሕርይ የሕጻኑ/ኗ የአካል ጉዳት ነጸብራቅ ካልሆነ (ከዚህ በታች ***የመገለጫ ውሳኔ*** የሚለውን ክፍል ይመልከቱ) እና ሥነ-ሥርዓትን ለማስጠበቅ ሲባል ተግባራዊ የሚደረገው የምደባ ለውጥ ከአስር (10) ተከታታይ የትምሕርት ቀናት በላይ የሆነ ጊዜ የሚወስድ ከሆነ፣ ትምሕርት ቤቱ ***አገልግሎቶች*** በሚለው ክፍል የተጠቀሱትን አገልግሎቶች መስጠት ያለበት መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የትምሕርት ቤቱ ሠራተኞች በሌሎች የአካል ጉዳት በሌለባቸው ልጆች ላይ በሚወስዱት ዕርምጃ መሠረት

እና ለተመሳሳይ ጊዜ የሥነ-ሥርዓት ሂደቶችን ተፈጻሚ ማድረግ አለባቸው። የሕጻኑ/ኗ የግላዊ ትምሕርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን እንዲህ ላሉት አገልግሎቶች ጊዜያዊ የትምሕርት አሰጣጥ ሁኔታን ይወስናል።

**አገልግሎቶች**

የአካባቢያ የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) በዚያው የትምሕርት ዘመን **ለአስር (10) *የትምሕርት ቀናት ወይም ከዚያ በታች*** ለሆነ ጊዜ ከወቅቱ ምደባው/ዋ እንዲገለል ለተደረገ/ች፣ የአካል ጉዳት ላለበት/ላለባት ወይም ለሌለበት/ለሌለባት ልጅ አገልግሎቶች ሊሰጥ የሚችል ቢሆንም፣ አገልግሎቶቹን የመስጠት ግዴታ ግን የለበትም። እንዲህ ያሉት አገልግሎቶች የሚሰጡ ስመሆኑ ለማረጋገጥ የአካባቢዎን የትምሕርት ኤጀንሲ (LEA) ያነጋግሩ።

የአካል ጉዳት ያለበት/ያለባት እና ከወቅቱ ምደባ ከ**አስር (10) *የትምሕርት ቀናት*** በላይ እንዲገለል/እንድትገለል ከተደረገ እና የታየውም ባሕርይ የሕጻኑ/ኗ የአካል ጉዳት ነጸብራቅ ካልሆነ (***የመገለጫ ውሳኔ*** የሚለውን ክፍል ይመልከቱ) ወይም በልዩ ሁኔታ (***ልዩ ሁኔታዎች*** የሚለው ክፍል ይመልከቱ) እንዲገለል/እንድትገለል ከተደረገ፣ ከዚህ የሚከተሉት መፈጸም አለባቸው፡-

- ሕጻኑ/ኗ በሌላም የትምሕርት አሰጣጥ ሁቤታ ቢሆን (አማራጭ የትምሕርት አሰጣጥ ሁኔታ ሊሆን ይችላል) በጠቅላላ ትምሕርት ሥርዓተ-ትምሕርት ውስጥ በተሳትፎው/ዋ እንዲቀጥል/እንድትቀጥል እንዲሁም በሕጻኑ ግላዊ የትምሕርት ፕሮግራም (IEP) ውስጥ የተጠቀሱትን ግቦች ለማሳካት አግባብነት ያለው የሕዝብ ትምሕርት (FAPE) አገልግሎትን መስጠት አለበት፤ ***<u>እንዲሁም</u>***
- የባህርይ ጉድለት ያለ እንደሆነ፣ ባህርይውን ለማረቅ እና ተመልሶ እንዳይደገም አግባብነት ያለው የባህርይ ግምገማ እና የባህርይ ኢንተርቬንሽን አገልግሎቶች እና ማስተካከያዎች ማግኘት።

የአካል ጉድለት ያለበት ልጅ ከወቅታዊው ምደባ በተመሳሳይ የትምህርት ዘመን ለአስር (10) ተከታታይ የትምህርት ቀናት እንዲገለል ከተደረገ እና ተማሪው የተገለለው ለአስር (10) ተከታታይ ቀናት ወይም ከዚያ በታች ***<u>ከሆነ</u>*** እንዲሁም ተማሪው መታገዱ/ዷ የምደባ ለውጥ ካልሆነ (ከዚህ በታች የሚገኘውን ትርጓሜ ይመልከቱ)፣ የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ከህፃኑ/ኗ ቢያንስ አንድ መምህር ጋር በመነጋገር ተማሪው/ዋ በጠቅላላ የትምህርት ስርዓት ትምህርት ውስጥ እንዲሳተፍ/እንድትሳተፍ ምን ዓይነት አገልግሎቶች እንደሚያስፈልጉ መወሰን ይገባቸዋል፤ በእርግጥ ህፃኑ/ኗ በጠቅላላ የትምህርት ስርዓት ትምህርት የሚሳተፈው/የምትሳተፈው በተለየ የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ ሊሆን ይችላል፤ የዚህም ዓላማ በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት ነው።

*ተማሪው/ዋ መታገዱ/ዷ የምደባ ለውጥ ከሆነ* ***(በስነ ስርዓት እርምጃ ምክንያት የምደባ ለውጥ የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ)*** የህፃኑ/ኗ የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም ቡድን ህፃኑ/ኗ በጠቅላላ ትምህርት ስርዓት ትምህርት (በሌላ የትምህርት አኳኋን ቢሆንም) እንዲሳተፍ/እንድትሳተፍ የሚያስፈልጉ አግባብነት ያላቸውን አገልግሎቶች ይወስናል፤ በሌላ የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ የሚለው አገላለፅ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት አሰጣጥ ሊሆን ይችላል፤ የዚህም አላማ በግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) የተቀመጡትን ግቦች ለማሳካት ነው።

***የመገለጫ ውሳኔ***

የአካል ጉዳት ያለበት/ባት ህፃን በተማሪዎች የስነ ስርዓት ደንብ የተቀመጠውን በመጣሱ/ሷ ምክንያት የምደባ ለውጥ የሚደረግ ከሆነ፣ የምደባው ለውጥ እንዲደረግ የሚወሰን ማናቸውም ውሳኔ ከመስጠቱ ከአስር (10) የትምህርት ቀናት በፊት የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA)፣ እርስዎ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን አባላት (በእርስዎ እና በአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ እንደሚወሰነው) በተማሪው/ዋ ማህደር ውስጥ የሚገኙ አግባብነት ያላቸውን መረጃዎች ሁሉ፣ የተማሪውን/ዋን ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም፣ ማናቸውም የመምህር አስተያየት እና እርስዎ የሰጧቸውን መረጃዎች መፈተሽ ይገባችኋል። የዚህም ምክንያት፡-

- የተማሪው/ዋ ባህርይ በቀጥታ እና ከፍተኛ የሚባል ግንኙነት ከአካል ጉዳተኝነቱ/ቷ ጋር ያለው መሆኑ ወይም በዚህ ምክንያት የመጣ ስለመሆኑ፤ ***<u>ወይም</u>***
- የታየው ባህርይ የተከሰተው የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) የህፃኑን/ኗን ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) በአግባቡ ተግባራዊ ባለመድረጉ ምክንያት ስለመሆኑ ውሳኔ ይሰጣል።

የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA)፣ እርስዎ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን አባላት ከላይ ከተጠቀሱት ሁኔታዎች አንዱም ቢሆን ተከስቷል ብለው የወሰናችሁ እንደሆነ፤ እንዲህ ያለው የባህርይ ጉድለት የህፃኑ/ኗ የአካል ጉዳት መገለጫ ነው ተብሎ መወሰን አለበት።

የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA)፣ እርስዎ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን አባላት የታየው ባህርይ በአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) በኩል የህፃኑን/ኗን ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) በአግባቡ ተግባራዊ ባለመድረጉ ምክንያት መሆኑን ከወሰናችሁ፣ የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) እነዚህን ጉድለቶች ለማረም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ አለባችሁ።



1050 First Street NE, Fifth Floor, Washington, DC 20002 • Phone: (202) 727-6436 TTY: 711 • osse.dc.gov

**የታየው ባህርይ የህፃኑ/ኗ የአካል ጉድለት መገለጫ ነው የሚል ውሳኔ መሰጠቱ፡-**

የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA)፣ እርስዎ እና ሌሎች አግባብነት ያላቸው የግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን አባላት የታየው ባህርይ የህፃኑ/ኗ የአካል ጉድለት መገለጫ ነው ብለው ከወሰኑ፣ የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድኑ ከዚህ ከሚከተሉት አንዱን መፈፀም አለበት፡-

- የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ቀደም ብሎ የባህርይ ግምገማ አድርጐ ከነበረ በስተቀር፣ የምደባ ለውጥ ያስከተለውን ባህርይ በተመለከተ የባህርይ ግምገማ ማካሄድ እና ለህፃኑ/ኗ የባህርይ ኢንተርቬንሽን እቅድ ተግባራዊ ማድረግ፤ **ወይም**
- የባህርይ ኢንተርቬንሽን እቅድ ቀደም ብሎ ተዘጋጅቶ ከነበረ አሁን የታየውን ባህርይ ለማረቅ ይህንን እቅድ መገምገም እና እንደአስፈላጊነቱ መለወጥ .

***ልዩ ሁኔታዎች*** በሚል ከታች በተብራራው አኳኋን ካልሆነ በቀር፣ የባህርይ ኢንተርቬንሽን እቅዱ አካል በሆነ መልኩ የምደባ ለውጥ እንዲደረግ እርስዎ እና የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ካልተስማማችሁ በቀር ህፃኑ/ኗ ቀደም ሲል ወደነበረበት/ወደነበረችበት ምደባ መመለስ አለበት/ባት።

**ልዩ ሁኔታዎች**

የታየው ባህርይ የልጅዎ የአካል ጉዳት መገለጫ መሆኑ ወይም አለመሆኑ ከግምት ሳይገባ፣ የትምህርት ቤቱ ሠራተኞች ልጅዎን ወደ ጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ (በልጅዎ ግላዊ የትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን እንደሚወሰነው) ከአርባ አምስት (45) የትምህርት ቀናት በላይ ላልሆነ ጊዜ ሊያዘዋውሩ ይችላሉ፤ ይህም የሚሆነው ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች ነው፡-

- ወደ ትምህርት ቤት የጦር መሣሪያ ይዞ/ዛ ከመጣ/ች (ከዚህ በታች የተሰጠውን ትርጓሜ ይመልከቱ) ወይም በትምህርት ቤት፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ወይም በክፍለ ግዛቱ የትምህርት ኤጀንሲ ወይም በአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) በሚተዳደር የመማሪያ ቦታ መሣሪያ ይዞ የተገኘ/ች እንደሆነ፤
- ሆን ብሎ ሕገወጥ ዕፅ (ከዚህ በታች የተሰጠውን ትርጓሜ ይመልከቱ) ይዞ ከተገኘ ወይም የሚጠቀም ከሆነ ወይም ቁጥጥር የሚደረግባቸውን ንጥረ ነገሮች የሚሸጥ ወይም ለመሸጥ የሚፈልግ ከሆነ (ከዚህ በታች የተሰጠውን ትርጓሜ ይመልከቱ) ይህንንም የሚፈፅመው በትምህርት ቤቱ ቅጥር ግቢ፣ በትምህርት ቤት ወይም በክፍለ ግዛቱ የትምህርት ኤጀንሲ ወይም በአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) በሚተዳደር የመማሪያ ቦታ በሚሆንበት ጊዜ፤ **ወይም**
- በትምህርት ቤት፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ግቢ ወይምበክፍለ ግዛቱ የትምህርት ኤጀንሲ ወይም በአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) በሚተዳደር የመማሪያ ቦታ በሌላ ሰው ላይ ከፍተኛ የአካል ጉዳት (ትርጓሜውን ከዚህ በታች ይመልከቱ) ያስከተለ እንደሆነ።

**ትርጓሜዎች**

*ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ ነገር* ማለት ቁጥጥር በሚደረግባቸው ንጥረ ነገሮች ሕግ (21 U.S.C. 812(c)) በክፍል 202(c) በሰንጠረዦች I፣ II፣ III፣ IV፣ ወይም V ስር የተካተተ መድሃኒት ወይም ሌላ ንጥረ ነገር ማለት ነው።

*ሕገወጥ እፅ* ማለት ቁጥጥር የሚደረግበት ንጥረ ነገር ሲሆን ነገር ግን ይህ ትርጓሜ ፈቃድ ባለው የጤና እንክብካቤ ባለሙያ ቁጥጥር ስር ጥቅም ላይ የሚውል ወይም በሕግ በሚፈቀድ መልኩ በይዞታ ያለ ወይም በሕጉ ወይም በሌላ ማናቸውም የፌዴራል ሕግ ድንጋጌ ስር በማናቸውም ሌላ ባለስልጣን ወይም ስልጣን በተሰጠው አካል በሕጋዊ አግባብ የተያዘ ወይም ጥቅም ላይ የሚውል ንጥረ ነገርን አያካትትም።

*ከፍተኛ አካላዊ ጉዳት ማለት* በዩናይትድ ስቴትስ ኮድ በርዕስ 18፣ በክፍል 1365፣ በንዑስ ክፍል (ኤች)፣ በ3ኛው አንቀጽ የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል።

*የጦር መሣሪያ ማለት* በዩናይትድ ስቴትስ ኮድ በርዕስ 18፣ በክፍል 930፣ በንዑስ ክፍል (ጂ)፣ በ2ኛው አንቀጽ የተሰጠውን ትርጓሜ ይይዛል።

**ማሳወቂያ**

የአካባቢዎ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) የትምህርት ቤቱን የተማሪዎች የስነ ምግባር ደንብ በመጣሱ ምክንያት የልጅዎን ምደባ ለመቀየር ወሳኔ በሰጠበት ቀን ይህንን ውሳኔ ለእርስዎ ማሳወቅ እና የፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ ኖቲስ ሊሰጥዎ ይገባል።

**በስነ ስርዓት ጉድለት ምክንያት ስለሚሆን የምደባ ለውጥ**

**34 CFR §300.536**

የአካል ጉዳት ያለበት/ባት ልጅዎ አሁን ከሚገኝበት/ከምትገኝበት የትምህርት ምደባ መገለል ማለት የምደባ ለውጥ ማለት ነው። የምደባ ለውጥ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟላ ነው፡-

- ልጅዎ ከአስር (10) ተከታታይ የትምህርት ቀናት በላይ ታግዶ/ዳ የቆየ/ች እንደሆነ፤ <u>ወይም</u>
- ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች ልጅዎ በተደጋጋሚ እንዲገለል ተደርጐ/ጋ ከሆን፡-

  ሀ. በአንድ የትምህርት ዘመን ከአስር (10) ቀናት በላይ በተደጋጋሚ የተገለለ/ች እንደሆነ፤

  ለ. የልጅዎ ባህርይ በተደጋጋሚ እንዲገለል/እንድትገለል ከተደረገበት/ከተደረገችበት ባህርይ ጋር እጅጉን ተመሳሳይ ከሆነ፤ እና

  ሐ. ሌሎች ተጨማሪ ነገሮች፣ ለምሳሌ ልጅዎ ታግዶ/ዳ የቆየችበት ጊዜ፣ ልጅዎ በዚህ መልኩ የቆየበት/የቆየችበት ጠቅላላ ጊዜ እና እንዲህ ዓይነት እርምጃዎች የሚወሰዱት በቅርብ ድግግሞች ከሆነ፤

እነዚህ ሁኔታዎች የምደባ ለውጥ የሚያስከትሉ መሆናቸው ወይም አለመሆናቸው እንደነገሩ ሁኔታ እያንዳንዱን ክስተት በማለት በአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) የሚወሰን ሲሆን፣ በዚህ ላይ ተቃውሞ የቀረበ እንደሆነ፣ ጉዳዩ በአቤቱታ መሰማት ሂደት ወይም በፍርድ ቤት ክርክር ይታያል።

## የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ አወሳሰን

**34 CFR §300.531**

የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድን ***የምደባ ለውጥ*** ሲደረግ እና ***ተጨማሪ ስልጣን*** እና ***ልዩ ሁኔታዎች*** በሚሉት ክፍሎች መሰረት ተማሪዎች ሲገለሉ ጊዜያዊ የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታን ይወስናል።

## ይግባኝ

**34 CFR §300.532**

### ጠቅላላ

ከዚህ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ተቃውሞ ካለዎት የዳኝነት አቤቱታ በማቅረብ ጉዳዩ እንዲታይልዎ መጠየቅ ይችላሉ ***(የዳኝነት አቤቱታ ስነ ስርዓት*** የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ)፡-

- በእነዚህ ስነ ስርዓትን በሚመለከቱ ድንጋጌዎች ስር የሚሰጥን ማናቸውንም ውሳኔ የሚቃወሙ ከሆነ፤ <u>ወይም</u>
- ከላይ የተገለፀው የመገለጫ ውሳኔ ላይ ተቃውሞ ካለዎት

የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) በወቅቱ ያለውን ምደባ ይዞ መቀጠል በልጅዎ ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት ሊያስከትል ይችላል ብሎ በእጅጉ ካመነ የዳኝነት አቤቱታ (ከላይ ያለውን ይመልከቱ) ሊያቀርብ ይችላል።

### የዳኝነት ኦፊሰር ስልጣን

የዳኝነት ኦፊሰሩ ***በገለልተኛ የዳኝነት መሰማት ሂደት*** በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር የተቀመጡትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ሆነው ጉዳዩን ሰምተው ውሳኔ መስጠት አለባቸው። የዳኝነት ኦፊሰሩ ከዚህ የሚከተሉትን ሊያደርጉ ይችላሉ፡-

- የዳኝነት ኦፊሰሩ ልጅዎ እንዲገለል/እንድትገለል የተደረገው ***የትምህርት ቤት ሠራተኞች ስልጣን፡*** በሚለው ንዑስ ርዕስ ስር የተቀመጡትን መስፈርቶች በመጣስ ነው ብለው ከወሰኑ ወይም የልጅዎ ባህርይ ያለበት/ያለባት የአካል ጉዳተኝነት መገለጫ ነው ወደሚል ድምዳሜ ከደረሱ የአካል ጉዳተኝነት ያለበትን/ያለባትን ልጅዎን ወደነበረው ምደባ ሊመልሱ ይችላሉ፤ <u>ወይም</u>
- የዳኝነት ኦፊሰሩ አሁን ያለውን ምደባ ይዞ መቆየት በልጅዎም ሆነ በሌሎች ላይ ጉዳት የሚያደርስበት ዕድል ከፍተኛ ነው ብለው ከወሰኑ የአካል ጉዳተኝነት ያለበት/ባት ልጅዎ ከአርባ አምስት (45) የትምህርት ቀናት ላልበለጠ ጊዜ ወደ ጊዜያዊ የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ እንዲዘዋወር/እንድትዘዋወር ትዕዛዝ ሊሰጡ ይችላሉ።

የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ልጅዎ አሁን ባለበት/ባለችበት ምደባ ቢቀጥል/ብትቀጥል በልጅዎም ሆነ በሌሎች ላይ ጉዳት የሚደርስበት ዕድል ሰፊ ነው በሚለው እምነቱ ከፀና እነዚህ የአቤቱታ መሰማት ሂደቶች ሊደገሙ ይችላሉ።
እርስዎም ሆኑ የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) እንዲህ ያለው ዳኝነት እንዲታይ ጥያቄ ካቀረባችሁ፣ ***ሂደቱ የዳኝነት አቤቱታ ስነ ስርዓት እና የዳኝነት አቤቱታ መሰማት ሂደት*** በሚሉት አርዕስት ስር የተቀመጡትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት፤ በልዩ ሁኔታ የሚታዩ ሁኔታዎች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፡-

- የክፍለ ግዛቱ የትምህርት ኤጀንሲ ወይም የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) የዳኝነት አቤቱታ እንዲታይ ጥያቄ ከቀረበ በ**ሃያ (20)** የትምህርት ቀናት ጊዜ ውስጥ የተፋጠነ የአቤቱታ መሰማት ችሎት ማመቻቸት እና አቤቱታው ከተሰማ በኋላ **በአስር (10)** የትምህርት ቀናት ጊዜ ውስጥ ውሳኔ ሊያገኝ ይገባል።
- እርስዎ እና የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) አለመግባባትን የመፍታት ውይይት ስብሰባ እንዳይካሄድ በፅሑፍ ካልተስማማችሁ በስተቀር የዳኝነት አቤቱታ ማሳወቂያ በደረሰ በ**ሰባት (7)** ተከታታይ ቀናት ውስጥ አለመግባባትን የመፍታት

ውይይት ስብሰባ መካሄድ አለበት። የዳኝነት አቤቱታ በደረሰ በ**አስር አምስት** (15) ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለሁለቱም ወገኖች አመርቂ በሆነ ሁኔታ ጉዳዩ ካልተፈታ የዳኝነት መሰማት ሂደቱ ሊቀጥል ይችላል።

- ክፍለ ግዛቱ ለሌሎች የዳኝነት አቤቱታ መሰሚያ ሂደቶች ካስቀመጠው ስነ ስርዓት ይልቅ የተፋጠነ ስረ ስርዓት ደንብ ሊያስቀምጥ ይችላል፤ ሆኖም ግን የግዜ ሰሌዳዎቹ ስለ ዳኝነት አቤቱታ መሰማት በዚህ ሰነድ ከተቀመጡት ደንቦች ጋር የሚጣጣሙ መሆን አለባቸው።

እርስዎም ሆኑ የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) እንደማናቸውም ሌሎች የዳኝነት ሂደቶች ሁሉ በዚህ የአቤቱታ መሰማት ሂደት የተሰጠውን ውሳኔ በመቃወም ይግባኝ ልትሉ ትችላላችሁ (***ይግባኝ*** የሚለውን ርዕስ ይመልከቱ)።

## በይግባኝ ወቅት ስለሚኖር ምደባ

**34 CFR §300.533**

ከላይ እንደተገለፀው ሁሉ እርስዎ ወይም የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ከስነ ስርዓት ጉዳዮች ጋር በተያያዘ የአቤቱታ መሰማት ጥያቄ ያቀረባችሁ እንደሆነ (እርስዎ እና የክፍለ ግዛቱ የትምህርት ኤጀንሲ ወይም የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) በሌላ አኳኋን ካልተስማማችሁ በቀር) ልጅዎ የዳኝነት አፈሰሩ ውሳኔ እስኪሰጡ ወይም የመገለል ጊዜ በተቀመጠው መልኩ እስኪጠናቀቅ እና ***የትምህርት ቤት ሠራተኞች ስልጣን*** በሚለው ስር የተቀመጠው ጊዜ እስኪያበቃ (ከሁለቱ የቀደመው) ልጅዎ በጊዜያዊ አማራጭ የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታ መመደብ አለበት/አለባት።

## ለልዩ ትምህርት እና ተያያዥ ለሆኑ አገልግሎቶች ለጊዜው ብቁ ላልሆኑ ልጆች ስለሚደረግ ጥበቃ

**34 CFR §300.534**

### ጠቅላላ

ልጅዎ ለልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ብቁ አይደለም/አይደለችም ተብሎ ከተወሰነ እና ልጅዎ የትምህርት ቤት የተማሪዎች ስነ ምግባር ደንብን የጣሰ/ች እንደሆነ ነገር ግን የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) (ከዚህ በታች እንደተመለከተው) የስነ ስርዓት እርምጃ እንዲወሰድ ያደረገው ባህርይ ከመከሰቱ በፊት ልጅዎ የአካል ጉዳት ያለበት/ባት መሆኑን ያውቅ ከነበረ ልጅዎ በዚህ ማሳወቂያ የተገለፁትን ማናቸውንም ጥበቃዎች ሊያነሳ/ልታነሳ ትችላለች።

### የስነ ስርዓት ጉዳዮች ግንዛቤ ምንጭ

ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) የስነ ስርዓት እርምጃ እንዲወሰድ ያደረገው ባህርይ ከመከሰቱ በፊት ልጅዎ የአካል ጉዳተኝነት እንዳለበት/ባት ያውቅ ነበር ተብሎ ሊወሰድ ይችላሉ፡-

- አግባብነት ላለው የትምህርት ኤጀንሲ የአመራር ወይም የአስተዳደር ሠራተኞች ወይም ለልጅዎ መምህር ልጅዎ ልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ሳያስፈልገው/ጋት አይቀርም ብለው እንደሚያምኑ በጽሑፍ ካሳወቁ፤
- በ IDEA በክፍል ቢ ስር ልጅዎ ለልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ብቁ መሆኑን/ኗን አስመልክቶ ምዘና እንዲካሄድ ጥያቄ አቅርበው ከነበረ፤ ***<u>ወይም</u>***
- የልጅዎ መምህር ወይም ሌሎች የአካባቢ የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ሠራተኞች ልጅዎ ስለሚያሳየው/ስለምታሳየው ባህርይ የሚያሳስባቸው ግልፅ የሆነ ነገር እንዳለ ለአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA's) የልዩ ትምህርት ኤጀንሲ ወይም ለሌላ የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) የአመራር ሠራተኛ የገለፁ እንደሆነ.

### ልዩ ሁኔታ

ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ከላይ የተገለፀውን ያውቅ ነበር ለማለት አይቻልም፡-

- ለልጅዎ ምዘና እንዲካሄድ ወይም የልዩ ትምህርት አገልግሎቶች እንዲሰጡ እርስዎ ፈቃደኛ ካልሆኑ፤ ***<u>ወይም</u>***
- ለልጅዎ ግምገማ ተካሂዶ በIDEA በክፍል ቢ ስር የአካል ጉዳተኝነት የለበትም/የለባትም ተብሎ ከተወሰነ።

***መሠረታዊ ግንዛቤ በሌለበት ሁኔታ ተፈፃሚ የሚሆኑ ሁኔታዎች***

በልጅዎ ላይ የስነ ስርዓት እርምጃዎች ከመውሰድ በፊት የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ከላይ በክፍል ***የስነ ስርዓት ጉዳዮች ግንዛቤ ምንጭ*** እና ***ልዩ ሁኔታዎች*** በሚሉት ክፍሎች ስር እንደተብራራው ስለ ልጅዎ የአካል ጉዳተኝነት ግንዛቤ ካልነበረው፣ ልጅዎ የአካል ጉዳተኝነት ሳይኖርባቸው ተመጣጣኝ የሆነ ባህርይ በሚያሳዩ ልጆች ላይ ተፈፃሚ የሚደረጉ የስነ ስርዓት እርምጃዎች ሊወሰዱበት/ባት ይችላሉ።

ሆኖም ግን፣ ልጅዎ የስነ ስርዓት እርምጃ ተወስዶበት/ባት ባለበት/ችበት ጊዜ ውስጥ ግምገማ እንዲካሄድ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ፣ እንዲህ ያለው ግምገማ በአፋጣኝ መካሄድ አለበት።
ግምገማው እስኪጠናቀቅ ድረስ፣ ልጅዎ በትምህርት ቤት ኃላፊዎች በሚወሰን የትምህርት ምደባ ላይ ይቆያል/ትቆያለች፤ ይህም የትምህርት አገልግሎቶች በሌሉበት እገዳ እና ከትምህርት ቤት ማሰናበትን ሊያካትት ይችላል። ልጅዎ የአካል ጉዳተኝነት አለበት ተብሎ በአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) በተከናወነው ግምገማ እና ከእርስዎ በተገኘ መረጃ መሠረት የአካል ጉዳተኝነት አለበት/አለባት ከተባለ፣ የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) በIDEA በክፍል ቢ ስር ልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች መስጠት አለበት፤ ከላይ የተቀመጡት የስነ ስርዓት መስፈርቶች ተፈፃሚ ይሆናሉ።

**ጉዳዩን ለሕግ አስከባሪ እና ለፍርድ ቤት አካላት መላክ እና በእነርሱ የሚወሰዱ እርምጃዎች**

**34 CFR §300.535**

የIDEA ክፍል ቢ ከዚህ የሚከተሉትን አይከለክልም:-

- አንድ ኤጀንሲ የአካል ጉዳተኝነት ባለበት ልጅ የተፈፀመን የወንጀል ድርጊት ለሚመለከታቸው ባለስልጣናት ሪፖርት ማድረግ፤ **<u>ወይም</u>**
- የክፍለ ግዛት የሕግ አስከባሪ እና የፍርድ ቤት ኃላፊዎች የአካል ጉዳት ያለበት/ባት ልጅ በፈፀመው የወንጀል ድርጊት ጉዳይ የፌዴራል እና የክፍለ ግዛት ሕግጋትን ተፈፃሚ ለማድረግ ያሉባቸውን ኃላፊነቶች ተግባራዊ ማድረግ።

***ሪከርዶችን ስለማስተላለፍ***

የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) የአካል ጉዳት ባለበት/ባት ልጅ የተፈፀመን የወንጀል ድርጊት ሪፖርት ያደረገ እንደሆነ፣ ኤጀንሲው (LEA):-

- የልጁ/የልጅቷ የልዩ ትምህርት እና የስነ ስርዓት ሪከርዶች ቅጂዎች እነዚህ ኤጀንሲዎች ሪፖርቱን በሚያቀርቡላቸው ኃላፊዎች እንዲታዩ ቅጂዎቻቸው ለእነርሱ መድረሱን ማረጋገጥ፤ **<u>እና</u>**
- የልጁን/የልጅቷን የልዩ ትምህርት እና የስነ ስርዓት ሪከርዶች ቅጂዎች ሲያስተላልፉ ይህ መሆን ያለበት በቤተሰብ የትምህርት መብቶች እና የግል መረጃ ጥበቃ ሕግ በሚፈቅደው አኳኋን መሆን አለበት (FERPA).

## በመንግስት ወጪ ልጆችን በራሳቸው ውሳኔ በግል ትምህርት ቤቶች ለማስገባት ተፈፃሚነት ያላቸው መስፈርቶች

**ጠቅላላ**

**34 CFR §300.148 and 5E DCMR §3018.5**

የአካባቢው የትምህርት ኤጀንስ (LEA) የአካል ጉዳተኝነት ላለበት/ላለባት ልጅዎ ነፃ አግባብነት ያለው የህዝብ ትምህርት (FAPE) የሚያገኝበትን/የምታገኝበትን ዕድል አመቻችቶ እያለ እርስዎ በራስዎ ፍላጐት በአንድ የግል ትምህርት ቤት ወይም ተቋም ለማስገባት ከወሰኑ የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) የልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶችን ጨምሮ ለእነዚህ የሚያስፈልገውን ወጪ እንዲሸፍን የIDEA ክፍል ቢ አያስገድደውም። ሆኖም DCPS (ከመልካ ምድራዊ አቀማመጥ አንፃር በዲስትሪክት ኦፍ ኮሎምቢያ ያለ ብቸኛው የአካባቢው ትምህርት ኤጀንሲ (LEA) እንደመሆኑ 34 CFR §§300.131 እስከ 300.144 ስር በወላጆቻቸው በግል ትምህርት ቤት እንዲገቡ የተደረጉ ልጆችን አስመልክቶ የክፍል ቢ ድንጋጌዎች ስር ፍላጐቶቻቸው ሊሟሉላቸው ከሚገባ ልጆች ጋር ማካተት አለበት።

**በግል ትምህርት ቤት የሚፈፀምን ክፍያ ስለመመለስ**

ልጅዎ በአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ስልጣን ስር ቀደም ብሎ ልዩ ትምህርት እና ተያያዥ አገልግሎቶች ያገኘ/ች እንደሆነ እና ልጅዎን በግል ትምህርት ቤት፣ በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ወይም በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያለ አካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ ፈቃድ ወይም እርሱ ባልመደበበት ሁኔታ ያስገቡ እንደሆነ፣ ፍርድ ቤት ወይም የዳኝነት ኦፊሰር ይህ ኤጀንሲ በትምህርት ቤቱ ያወጡትን ወጪ ተመላሽ እንዲያደርግልዎ ኤጀንሲውን ሊያዝዙ ይችላሉ፤ ይህ የሚሆነው ፍርድ ቤቱ ወይም የዳኝነት ኦፊሰሩ ልጅዎ በተገለፀው ተቋም ከመግባቱ/ቷ በፊት የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ነፃ አግባብነት ያለው የሕዝብ ትምህርት (FAPE) እድልን አላመቻቸም በሚል ውሳኔ ከሰጡ እና በግል ትምህርት ቤት መግባቱ/ቷ አግባብነት ያለው ከሆነ ነው። የዳኝነት ኦፊሰሩ ወይም ፍርድ በክፍለ ግዛቱ የትምህርት ኃላፊ መ/ቤት (OSSE) እና በአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) በሚሰጡ ትምህርቶች ላይ ተፈፃሚነት

ያላቸውን ስታንዳርዶች የማያሟላ ቢሆን እንኳን ልጅዎ በግል ትምህርት ቤት ወይም ተቋም መማሩ/ሯ ተገቢ ነው ብለው ሊወስኑ ይችላሉ።

***ወጪ በመመለስ ላይ ተፈፃሚነት ያለው ገደብ***

ከላይ በሚገኘው አንቀጽ ላይ የተገለፀው ወጪን ተመላሽ የማድረግ ጉዳይ ላይ መጠኑ ሊቀነስ ወይም ውድቅ ሊደረግ ይችላል፤ እርሱም እንደሚከተለው ነው፦

- ልጅዎ ከሕዝብ ትምህርት ቤት እንዲገለል/እንድትገለል ከመደረጉ በፊት እርስዎ በተሳተፉበት የግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ስብሰባ እርስዎ የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ለልጅዎ ነፃ አግባብነት ያለው የሕዝብ ትምህርት (FAPE) እድል አቅርቦልዎት የነበረ ቢሆንም ይህንን እንዳልተቀበሉት ለግላዊ ትምህርት ፕሮግራም (IEP) ቡድኑ ያልገለፁ እንደሆን፣ የሚያሳስቡዎትን ነገሮች እና ልጅዎን በግል ትምህርት ቤት በመንግስት ወጪ ማስተማር ስለመፈለግዎ ለቡድኑ ካልገለፁ፤
- ልጅዎ በስነ ስርዓት ጉድለት ምክንያት ከሕዝብ ትምህርት ቤት እንዲገለል/እንድትገለል ከመደረጉ በፊት ባሉት ቢያንስ አስር (10) የሥራ ቀናት (በሥራ ቀን የሚውሉ ማናቸውንም የበዓላት ቀናት አካትቶ) ይህንን መረጃ በፅሑፍ አማካኝነት ለአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ያልሰጡ እንደሆነ፤
- ልጅዎ ከሕዝብ ትምህርት ቤት ከመታገዱ/ዷ በፊት የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ለልጅዎ ግምገማ ለማድረግ ሐሳብ ያለው መሆኑን አስቀድሞ የጽሑፍ ማሳወቂያ የሰጠዎ እንደሆነ እና (አግባብነት ያለው እና ምክንያታዊ ግምገማ ስለሚካሄድበት ምክንያት በመግለጽም ጭምር)፣ ነገር ግን እርስዎ ለልጅዎ ግምገማ እንዲካሄድ ፈቃደኛ ካልሆኑ፤ <u>ወይም</u>
- ፍርድ ቤት የእርስዎ ተግባራት ምክንያታዊነት የጐደላቸው ናቸው የሚል ውሳኔ ከወሰነ።

ሆኖም ግን ተመላሽ የሚደረገው ወጪ፦

- ከዚህ በሚከተሉት ሁኔታዎች ማሳወቂያ አልተሰጠም በሚል ምክንያት መቀነስ ወይም ውድቅ መደረግ የለበትም፦
  - ሀ. ወላጅ ማንበብ እና መፃፍ የማይችሉ ከሆኑ እና እንግሊዝኛ የማይፅፉ ከሆኑ፤
  - ለ. የአካባቢው የትምህርት ኤጀንሲ (LEA) ወይም ትምህርት ቤቱ ማሳወቂያውን እንዳይሰጡ ካደረገ፤
  - ሐ. ከላይ የተገለፀውን ማሳወቂያ ለመስጠት ያለብዎትን ኃላፊነት በማስመልከት ማሳወቂያ ካልደረሰዎ፤ <u>ወይም</u>
  - መ. ከላይ የተገለፁትን መስፈርቶች ተቀብለው ቢያሟሉ በልጅዎ ላይ ከፍተኛ አካላዊ ወይም የስነ ልቦና ጉዳት የሚከተል ከሆነ።

**ለተጨማሪ መረጃ፣ እባክዎን ከዚህ የሚከተለውን መሥሪያ ቤት ያግኙ፡-**

**Office of the State Superintendent of Education**
**Office of Special Education**
1050 First Street, NE, 5th Floor
Washington, DC 20002
(202) 478-5947

ይህ ሰነድ ከዚህ በሚከተለው ድረ-ገጽ በኤሌክትሮኒካል አግባብ ሊገኝ ይችላል፡-
http://www.osse.dc.gov

**ዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ**
**የአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ (IDEA) የክፍል ቢ**
**የአካል ጉዳተኛ ልጆች ወላጆች የፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ መብቶች**
**(የመብት ማስጠበቂያ ሥነ-ሥርዓት) ማሳወቂያ**

ደረሰኝ

እኔ_______________________________________________
(የወላጅ/የአሳዳጊ ሥም)

የዲስትሪክት ኦፍ ኮሉምቢያ የአካል ጉዳተኞች የትምሕርት ሕግ ክፍል ቢ ፕሮሲጀራል ሴፍጋርድስ (የመብት መስጠበቂያ ሥነ-ሥርዓት)፡- የአካል ጉዳተኛ ልጆች ወላጆች መብቶች ማሳወቂያ የደረሰኝ መሆኑን አረጋግጣለሁ።

ከ፡-_______________________________________________
(ሰነዱን የሰጠው ሰው ሥም እና ማዕረግ)

ቦታ፡-_______________________________________________
(የትምሕርት ቤቱ ሥም)

________/________/________
(ቀን)

______________________________
(የወላጅ/የአሳዳጊ ፊርማ)

(ይህ ደረሰኝ በትምሕርት ቤቱ በሚገኝ አግባብነት ባለው ምሕደር ውስጥ እንዲቀመጥ የሚደረግ ሲሆን፣ ጥያቄ በሚቀርብ ጊዜ ለወላጅ ወይም ለአሳዳጊ ይሰጣል።)